# የደቡብ ብሔሮች፣ ብሔረሰቦችና ሕዝቦች ክልል መንግስት
## ደቡብ ነጋሪት ጋዜጣ
## DEBUB NEGARIT GAZETA
## OF THE SOUTHERN NATIONS, NATIONALITEIS AND PEOPLE’S REGIONAL STATE

፲፰ ዓመት ቁጥር ፳
ሀዋሳ ሀምሌ ፳፩ ቀን ፪፻፻፬ዓ.ም

በደቡብ ብሔሮች፣ብሔረሰቦችና ሕዝቦች ክልል ምክር ቤት ጠባቂነት የወጣ

18 Year No ፳
Hawassa July 28/2012


## አዋጅ ቁጥር ፩፻፵፮/፪፻፻፬

## PROCLAMATION NO. 146/2012

### የደቡብ ብሔሮች፣ ብሔረሰቦችና ሕዝቦች ክልል መንግሥት የግዥ እና ንብረት አስተዳደር አዋጅ

### THE SOUTHERN NATIONS, NATIONALITIES AND PEOPLE’S REGIONAL STATE PROCUREMENT AND PROPERTYADMINISTRATION PROCLAMATION

## መግቢያ

የክልሉ መንግሥት የግዥ አፈጻጸም ሥርዓት ይበልጥ ግልጽ፣ ቀልጣፋ፣ ፍትሃዊና አድልዎ የሌለበት እንዲሁም ለግዥ የሚውለው ከፍተኛ የመንግስት ገንዘብ በተሻለ ሁኔታ ቁጠባንና ውጤታማነትን ለማረጋገጥ በሚያስችል ስርዓት ጥቅም ላይ እንዲውል ማድረግ አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ፣

ከጥቅል ግዥ የሚገኘው ኢኮኖሚያዊ ጠቀሜታ እና ቀልጣፋ አሰራር ማረጋገጥ የሚያስችል አደረጃጀት እንዲኖር ማድረግ አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ፣

ከፍተኛ ሀብት የሚፈስበት የመንግሥት ንብረት ለመንግሥት የተሻለ ጥቅም በሚያስገኝ አኳኋን ጥቅም ላይ እንዲውል እና አስተዳደሩም ዘመናዊ እንዲሆን ለማድረግ የሚያስችል የተቀናጀ ሥርዓት ሊዘረጋ እንደሚገባ የታመነበት ስለሆነ፣

## Preamble

**Where as,** it is become necessary to introduce a more transparent, effective, fair and impartial public procurement system and as well as, to enable a large sum of public money spent on procurement to be utilized in a manner that ensures greater economy and efficiency;

**Where as,** it is necessary to establish an organization that enable to realize economic benefit and effective working system where bulk purchase is in place;

**Where as,** it is necessary to introduce a harmonized public property administration thereby public property in which a significant amount of public money is invested to be utilized in such a manner that enable the state to device maximum benefit there from and the administration to be modernized thereof.

በክልሉ መንግስት ግዥና ንብረት አስተዳደር ሥርዓት ላይ በተከናወነው የአሰራር ሥርዓት ለውጥ የተገኙ እና የክልሉን መንግሥት ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ የልማት እንቅስቃሴዎች የሚያግዙ አዳዲስ አሰራሮች እና አደረጃጀቶች ተግባራዊ ማድረግ በማስፈለጉ፣

ከዚህ በፊት በነበረው የክልሉ መንግስት ግዥና ንብረት አስተዳደር አዋጅ ቁጥር ፻፳፱/፪፻፻፪ ያልተካተቱና በአፈፃፀም ሂደት አስፈላጊ ሆነው የተገኙ አንቀጾች በዚህ አዋጅ ቢካተቱ ክልሉ የበለጠ ተጠቃሚ እንደሚሆን በመታመኑ፣

ሀገራችን እንደ ሀገር አንድ ወጥ የሆነ የኢኮኖሚ ማህበረሰብ ለመፍጠር የምታደርገውን ጥረት ለማገዝና ክልሉንም የበለጠ ተጠቃሚ ለማድረግ የክልሉ መንግስት የግዥና ንብረት አስተዳደር አዋጅ ቁጥር ፻፳፱/፪፻፻፪ ከፌድራል መንግስት የግዥና ንብረት አስተዳደር አዋጅ ቁጥር ፮፻፵፱/፪፻፻፩ ያለውን መሰረታዊ ልዩነቶች ማጥበብ አስፈላጊ ሆኖ መገኘቱ፣

በተሻሻለው የደቡብ ብሔሮች፣ ብሔረሰቦችና ሕዝቦች ክልል መንግሥት ሕገ-መንግሥት አንቀጽ ፶፩/፫/ሀ መሠረት የሚከተለው ታውጇል፡፡

## ምዕራፍ አንድ

## ጠቅላላ

### ፩ አጭር ርዕስ

ይህ አዋጅ "የደቡብ ብሔሮች፣ ብሔረሰቦችና ሕዝቦች ክልል መንግሥት የግዥ እና የንብረት አስተዳደር አዋጅ ቁጥር **፩፻፵፮/፪፻፻፬** ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

**Where as,** it is become necessary to implement new working system that has been introduced during the reengineering of public procurement and property administration system of the region and matters helpful to enhance economic and social development activities of regional state.

**Where as,** it is believed beneficiary to the regional state to incorporate a new provisions that are not cover under the former proclamation No 129/2002 and other matters identified through the process of implementation;

**Where as,** it is found necessary to truncate the fundamental discrepancies between the region procurement and property administration proclamation No 129/2002 with that of the federal proclamation No 649/2001, so as to assist the struggle towards the formation of uniform economic community and has to made the region better beneficiary;

**Now therefore,** in accordance with article 51/3/(A) of the revised constitution of the Southern Nations, Nationalities and Peoples Regional State; it is hereby proclaimed as follows,

## CHAPTER ONE

## GENERAL

### 1. Short Title

This Proclamation may be cited as "**The Southern Nations, Nationalities and Peoples Regional State Procurement and Property Administration Proclamation No.146/2012**".

## ፪ ትርጓሜ

**የቃሉ አገባብ ሌላ ትርጉም የሚያሰጠው ካልሆነ በስተቀር በዚህ አዋጅ ውስጥ ፡-**

፩ " ዕቃ" ማለት በጠጣር፣በፈሣሽ ወይም በጋዝ መልክ የሚገኝ ጥሬ ዕቃ፣ ምርት፣ መሣሪያ፣ሸቀጥ፣ ለገበያ የተዘጋጀ ሶፍትዌርና እንስሳ ሲሆን ከሚገዛው ዕቃ ጋር ግንኙነት ያለው እና ከዕቃቹ ዋጋ ያልበለጠ ዋጋ ያለው የተከላ፣ የትራንስፖርት፣ የጥገናና ሌላ ተመሳሳይ አገልግሎትን ይጨምራል፡፡

፪ " **አገልግሎት**" ማለት ከዕቃ፣ከግንባታ ዘርፍ ሥራ እና ከምክር አገልግሎት ውጪ ያለ ሲሆን የጥገና ፣ የጥበቃ፣ የጽዳት አገልግሎት፣ የኤሌትሪክ ኃይል፣ የቴሌኮሚኒኬሽን እና የውሃ አቅርቦት የመሣሠሉትን ይጨምራል፡፡

፫ " **የግንባታ ዘርፍ ሥራ**" ማለት ከሕንፃ፣ ከመንገድ ወይም ከመሠረተ ልማት ስራ ጋር በተያያዘ የሚከናወን አዲስ የግንባታ፣ የመልሶ ግንባታ፣የማፍረስ፣ የጥገና፣ የማደስ ሥራ እንዲሁም ተጓዳኝ የሆነና ከዋናው ሥራ ያልበለጠ ዋጋ ያለው አገልግሎት ሲሆን የመገንባት፣ በባለቤትነት የመያዝ፣ ሥራውን የማንቀሳቀስ እና የማስተላለፍ ውሎችን ይጨምራል፡፡

## 2. Definitions

In this Proclamation unless the context otherwise requires:

1/ **«Goods»** means raw material, product, equipment and commodities in solid, liquid or gaseous form, marketable software and live animals as well as installation, transport, maintenance or similar obligations related to the supply of the goods if their value does not exceed that of the goods themselves;

2/ **«Service»** means any type of procurement other than goods, works and consultancy services: such as maintenance, security, janitorial, electricity, telecommunication and water supply services;

3/ **«Works»** means the construction, reconstruction, demolition, repair or renovation of a building, road, or infra structure, as well as services incidental to works, if the value of those services does not exceed that of the works themselves and includes building, holding, operating, and transfering contracts;

፬ "የምክር አገልግሎት " ማለት አማካሪዎች ያላቸውን ሙያዊ ክህሎት በመጠቀም የሚሰጡት የጥናት፣ የዲዛይን፣የቁጥጥር፣ የተለዩ ፕሮጀክቶችን የማደራጀት፣ ለደንበኞች ምክር የመስጠት፣ ሥልጠና የመስጠት እና ዕውቀትን የማስተላለፍ የአማካሪነት ባህሪ ያለው የአእምሮ አገልግሎት ነው፡፡

፭ " ግዥ" ማለት ዕቃዎችን፣የግንባታ ዘርፍ ሥራዎችን የምክር እና ሌሎች አገልግሎቶችን በግዥ፣ በኪራይ ወይም በማናቸውም ሌላ ተመሳሳይ ውል ማግኘት ነው፡፡

፮ "የመንግሥት መስሪያ ቤት "ማለት ሙሉ በሙሉ ወይም በከፊል በክልሉ መንግሥት በጀት የሚተዳደር የመንግሥት መስሪያ ቤት እና ተመሳሳይ አቋም ያለው አካል ነው፡፡

፯ "የመንግሥት ገንዘብ " ማለት ከክልሉ መንግሥት ገቢ ወይም ከፌደራል መንግስት ድጎማ ወይም ክልሉ በፌደራል መንግስት በኩል ከውጭ ዕርዳታና ብድር ለግዥ ፈፃሚ አካላት የተመደበ ገንዘብ ወይም የመንግሥት መስሪያ ቤት የውስጥ ገቢ ነው፡፡

፰ " የመንግሥት ግዥ" ማለት በመንግሥት መስሪያ ቤት በመንግሥት ገንዘብ የሚከናወን ግዥ ነው፡፡

4/ **«Consultancy Service»** means a service of an intellectual and advisory nature provided by consultants using their professional skills to study, design and organize specific projects, advice clients, conduct training and transfer knowledge;

5/ **«Procurement »** means obtaining goods, works, consultancy or other services through purchasing, hiring or obtaining by any other contractual means;

6/ **«Public Body »** mean any public body, or any other similar body which is partly or wholly financed by the state budget;

7/ **«Public Fund »** mean any monetary resource appropriated to a public body from the state revenue or subsidy from the Federal Government or aid grants and credits put at the disposal of the public bodies by foreign donors through the Federal Government or internal revenue of the public body;

8/ **«Public Procurement »** means procurement by a public body using public fund;

፱ " **አቅራቢ**" ማለት ለመንግሥት መስሪያ ቤት ዕቃ ወይም አገልግሎት ለማቅረብ ወይም የግንባታ ዘርፍ ሥራ ወይም የምክር አገልግሎት ለማከናወን ውል የገባ ሰው ወይም ድርጅት ነው፡፡

፲ "**ዕጩ ተወዳዳሪ**" ማለት በመንግሥት ግዥ እንዲሳተፍ የተጋበዘ ወይም ለመካፈል ያመለከተ ሰው ወይም ድርጅት ነው፡፡

፲፩ "**ተጫራች**" ማለት የመጫረቻ ሃሣብ ያቀረበ ሰው ወይም ድርጅት ነው፡፡

፲፪ "**የጨረታ ሠነድ**" ማለት ዕጩ ተወዳዳሪዎች የመጫረቻ ሰነድ ለማዘጋጀት እንዲችሉ በመንግስት መስሪያቤቱ የሚዘጋጅ ዝርዝር የግዥ ፍላጎትን የሚገልጽ ሰነድ ነው፡፡

፲፫ "**የመጫረቻ ሠነድ**" ማለት የመንግስት መስሪያ ቤቱ ለግዥው ባዘጋጀው የጨረታ ሠነድ መነሻነት ተጫራች በግዥው ለመሳተፍ የሚያቀርበው ሰነድ ነው፡፡

፲፬ " **የግዥ መመሪያ**" ማለት በዚህ አዋጅ መሠረት በፋይናንስና ኢኮኖሚ ልማት ቢሮ የሚወጣ መመሪያ ነው፡፡

፲፭ "**የቢሮ ኃላፊ እና ቢሮው**" ማለት እንደቅደም ተከተሉ የክልሉ ፋይናንስና ኢኮኖሚ ልማት ቢሮ ኃላፊና የክልሉ ፋይናንስና ኦኮኖሚ ልማት ቢሮ ነው፡፡

፲፮ "**ሰው**" ማለት የተፈጥሮ ሰው ወይም በህግ የሰውነት መብት የተሰጠው አካል ነው፡፡

9/ **«Supplier »** means a person or an organization who enter into a contract with a public body to supply goods or services or works or consultancy services;

10/ **«Candidate »** means a person or an organization invited or applied to take part in public procurement;

11/ **«Bidder »** means a person or an organization who propose for a bid;

12/ **« Bidding Documents »** means a document prepared by the public body as a basis for preparation of bids; which contains a specificationof the desired object of procurement;

13/ **«Bid Proposal»** means a document submitted by bidders to participate in a bid on the basis of the bid document prepared by a public body in respect of that procurement;

14/ **«Procurement Directive »** means the directive to be issued by the Bureau of Finance and Economic Development in accordance with this Proclamation;

15/ «**Head of Bureau and Bureau »** means the Bureau head and the Bureau of Finance and Economic Development respectively;

16/ **«Person »** means a natural or juridical person;

፲፯ "ልዩ ግዥ" ማለት ክልልዊ ጠቀሜታ ያላቸው በመሆኑ ምክንያት በቢሮው ውሣኔ በጥቅል የሚፈጸሙ ከፍተኛ ግዥዎች ወይም የመንግስት መስሪያ ቤቶች ያላቸውን ተመሳሳይ የግዥ ፍላጎት እንዲሁም አንድ የመንግስት መስሪያ ቤት በተወሰነ ጊዜ ውስጥ በተደጋጋሚ የሚኖረውን የግዥ ፍላጎት ለሚሟላት የሚፈጸም ግዥ ነው፡፡

፲፰ "የማዕቀፍ ስምምነት" ማለት ወደፊት በሚፈጸም ዝርዝር ውል ለሚከናወን አቅርቦት መሠረት በመሆን የሚያገለግል፣ በነጠላና በሌሎች የውል ሁኔታዎች ላይ በመመስረት የተፈጸመ አጠቃለይ የሆነ የግዥ ስምምነት ነው፡፡

፲፱ "የማዕቀፍ ስምምነት አቅራቢ" ማለት በማዕቀፍ ስምምነት ዕቃ ወይም ሌሎች አገልግሎቶችን ለማቅረብ ውል የገባ አቅራቢ ነው፡፡

፳ «ቦርድ» ማለት በመንግስት የግዥ አፈጻጸም እና የንብረት አወጋገድ ሂደት ላይ በዕጩ ተወዳዳሪዎች የሚቀርቡለትን አቤቱታዎች መርምሮ ውሳኔ እንዲሠጥ በዚህ አዋጅ የተቋቋመ አካል ነው፡፡

፳፩ «ኤጀንሲ» ማለት በዚህ አዋጅ መሠረት የሚቋቋመው የክልሉ ግዥና ንብረት አስተዳደር ኤጀንሲ ነው፡፡

፳፪ «የመንግስት ንብረት» ማለት ከመንግስት ገንዘብ እና መሬት በስተቀር የክልሉ መንግስት ሀብት የሆነ ማናቸውም ንብረት ነው፡፡

17. **«Special Procurement»** meanss a procurement of sizable volume carried out in bulk by a decision of the bureau on account of the regional significance of that procurement or a procurement carried out to fulfill similar requirements of various public bodies or requirements of a public body within a given period of time;

18. «**Framework Contract»** means a general agreement of procurement establishing unit price and other terms and conditions of contract which serves as a basis for supplies to be delivered under future specific contract;

19. **«Framework Contract Supplier»** means a supplier who has entered in to a contractual obligation to supply goods or services under a framework contract;

20. **«Board»** means an entity established under this Proclamation to review and decide on complaints from candidates with regard to the conduct of procurements and disposal of property of the state;

21. **«Agency»** means the Region procurement and property administration agency established by this proclamation;

22. **«Public Property»** means any property of the Regional state other than public fund and land;

፳፫ **«የጥበቃ ኃላፊነት» ማለት** በመንግስት መስሪያ ቤት የበላይ ኃላፊ ወይም ሀላፊው በወከለው የሥራ መሪ፣ የመንግስት ንብረት እስከሚወገድ ወይም ከመዝገብ እስከሚሠረዝ ወይም በሌላ ሠራተኛ ወይም በመስሪያ ቤት ጥበቃ ሥር እንዲውል እስከሚተላለፍ ድረስ የመንግስት ንብረት ለመያዝና ለመጠበቅ ለመንግስት ሠራተኛ የሚሰጥ ኃላፊነት ነው፡፡

፳፬ **«ቋሚ ንብረት» ማለት** ግዙፋዊ አቋም ያለው፣ የተናጠል ዋጋው ቢሮው በሚወጣው መመሪያ የሚወሰን ከአንድ ዓመት በላይ ለሆነ ጊዜ የጠቀሜታ እሴት የሚኖረው እና አገልግሎት በመስጠት ላይ የሚገኝ ንብረት ሲሆን፣ እንደ የቢሮ ዕቃ፣ ኮምፒዩተር፣ ከባድ መሣሪያ፣ ተሽከርካሪ፣ መርከብ፣ አውሮፕላን፣ ሕንጻ፣ መንገድ፣ የፍሳሽ መስመር፣ ድልድይ፣ መስኖ እና ግድብ የመሳሰሉትን ይጨምራል፡፡

፳፭ **«የሕይወት ዘመን ሥርዓት» ማለት** ከመንግሥት ንብረት ጋር የተያያዙ ተግባሮች እና ወጪዎችን የማቀድ፣ የመያዝ፣ የመረከብ፣ የመጠቀም፣ የጥገና፣ የፍጆታ፣ ወይም የማስወገድ ወይም ከመዝገብ የመሠረዝ ተግባራትን ከግምት ውስጥ በማስገባት የመንግሥት ንብረት አስተዳደር እና ቁጥጥር ብቃት ባለው መንገድ እንዲመራ ለማድረግ የሚያስችል ሥርዓት ነው፡፡

23. **«Custodial Responsibility»** means the responsibility conferred on a civil servant by the head of a public body or by a person delegated by him to protect and maintain public property until it is disposed or written off, or transferred to the custody of another civil servant or public body;

24. **«Fixed Asset»** means tangible asset the value of which is determined by a directive to be issued by the bureau, that is in operational use and that has a useful economic life of more than one year, such as furniture, computers, heavy equipment, vehicles, ships and aircraft, buildings, roads, sewers, bridges, irrigation systems, dam and the like;

25. **«Life- Time Approach»** means a system of effective management and control of public property which takes in to account all associated activities and costs, namely, planning,acquisition,receipt,use,maintenance, consumption or disposal or deletion of public property;

፳፮ **«አላቂ ዕቃ»** ማለት ከቋሚ ዕቃ ውጪ የሆነ ማናቸውም የመንግሥት ንብረት ሲሆን ጥቅም ላይ መዋል ከጀመረበት ጊዜ አንስቶ እስከ አንድ ዓመት አገልግሎት ሊሰጥ የሚችልና ዋጋው ቢሮው በሚያወጣው መመሪያ የሚወሰን ንብረት ነው፡፡

፳፯ «**ማስወገድ**» ማለት የመንግሥት ንብረት በሽያጭ ወይም በዝውውር ለሌላ ወገን ማስተላለፍ ወይም መቅበር ወይም ማቃጠል ነው፡፡

፳፰ **«የመንግሥትና የግል ሽርክና»** ማለት በመንግሥት መሥሪያ ቤት እና በግል ባለሀብት መካከል በሚደረግ ውል በግሉ ባለሀብት ተሳትፎ የሚደረግ ኢንቨስትመንት ሲሆን ኮንሴሽነር ተብሎ የሚታወቀው የግል ባለሀብት፡-

ሀ. የግንባታ ፕሮጀክቶችን ወይም አገልግሎቶችን ወይም በኮንሴሽን ኪራይ የሚሰጡ ሥራዎችን ለማከናወን ግዴታ የሚገባበት፤

ለ. የመንግሥት ተግባር የሆኑ ሥራዎች ከማከናወን ወይም የመንግሥትን ንብረት ሥራ ላይ ከማዋል ጋር በተያያዘ በፋይናንስ፣ በቴክኒክ እና በሥራ እንቅስቃሴ ረገድ የሚኖሩ ኃላፊነቶችን በአመዛኙ የሚወስድበት፤

ሐ. የመንግሥት ተግባር የሆኑ ሥራዎች በማከናወን ወይም የመንግሥትን ንብረት ሥራ ላይ በማዋል ለሚሰጠው አገልግሎት ከመንግሥት ክፍያ የሚያገኝበት ወይም በተጠቃሚዎች ላይ ከሚጣል ክፍያ ገቢ የሚሰበስብበት ወይም በሁለቱም መንገዶች ለአገልግሎቱ ክፍያ የሚያገኝበት፣ ውል ነው፡፡

26. **«Supplies»** meanss any public property other than fixed assets, which can be consumed within one year of use and the value of which is determined by a directive to be issued by the bureau;

27. **«Disposal»** means the transfer of public property to another person by sale or other means or the act of getting rid of public property by burning or burying;

28. **«Public Private Partnership»** means investment conducted through the participation of private a contractual arrangement between a public body and a private investor; and the investor in which known as the concessionnaire:

a) enter in to obligation to perform or undertake any construction project or service or lease concession;

b) assumes to take substantial financial, technical and operational risks in connection with the performance of a public function or use of state property;

c) receives consideration for performing a public function or utilizing state property, by way of fees from any public funds, user levies collected by the concessionnaire from users or customers for a service provided by it, or a combination of such consideration.

፳፱ «ኮንሴሽነር» ማለት ከመንግሥት መሥሪያ ቤት ጋር የመንግሥትና የግል ሽርክና ውል የሚገባ ሰው ነው፡፡

፴ "የግዥና ንብረት አስተዳደር ሥራ ሂደት" ማለት የክልሉ መንግስት መስሪያ ቤቶች እንደመስሪያ ቤታቸው ተጨባጭ ሁኔታ የሚያደራጁትና የግዥና ንብረት አስተዳደር ተግባርን እንዲያከናውን ሀላፊነት የሚሰጡት ወይም በግዥ ፋይናንስና ንብረት አስተዳደር ሥራ ሂደት ውስጥ የግዥና ንብረት አስተዳደር ተግባርን እንዲያከናውን ሀላፊነት የሚሰጡት አካል ነው፡፡

## ፫ የፆታ አገላለጽ

በዚህ አዋጅ ውስጥ ለወንድ ፆታ የተደነገገው ለሴቷም ፆታ ያገለግላል፡፡

## ፬ የተፈፃሚነት ወሰን

፩ ይህ አዋጅ በማናቸውም የክልሉ መንግሥት ግዥና ንብረት አስተዳደር ላይ ተፈፃሚ ይሆናል፡፡

፪ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ ፩ የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ የመንግሥት መሥሪያ ቤቶች ዕቃዎችን፣ የግንባታ ዘርፍ ሥራዎችን፣ የምክርና ሌሎች አገልግሎቶችን ወጪ በመሸፈን ከሌሎች መንግሥት መስሪያ ቤቶች ለማግኘት በሚያደርጉት ውል ላይ ይህ አዋጅ ተፈጻሚ አይሆንም፡፡

29. **«Concessionaire»** means a person who enters into a contract with a public body under a public private partnership;

30. **"Procurement and Property Administration Work Process"** means a department organized by the public body of the regional state through taking in to account the objective reality of their institution and responsible to carry out the functions of procuremmt and property administration or a body responsible to carry out the same functions within the procurement and property administration work process;

## 3. Gender Reference

In this Proclamation, the Provisions set out in masculine gender shall also apply to the feminine gender.

## 4. Scope of Application

1. This Proclamation shall apply to all procurement and property administration of the regional state.

2. Without prejudice to the provisions of sub-article 1 of this Article: this Proclamation does not apply to contracts a public body enters into with another public body for the provision of goods, works, consultancy or other services at cost.

## ፭ የመንግስት ግዢ እና ንብረት አስተዳደር መርሆዎች

የመንግሥት ግዥ አፈጻጸም የሚ¸ከተሉትን መርሆዎች መሠረት ማድረግ ይኖርበታል፡-

፩ በግዥ አፈጻጸም ረገድ የመንግሥት ገንዘብ ሊያስገኝ የሚችለውን ጥቅም ማስገኘቱን፤

፪ በዚህ አዋጅ በተፈቀደው ልዩ አሰተያየት ካልሆነ በስተቀር በዜግነት ወይም በዘር ወይም ከመወዳደሪያ መስፈርቶች ጋር ባልተያያዙ ሌሎች ምክንያቶች በዕጩ ተወዳዳሪዎች መካከል አድልዎ ያለመደረጉን፤

፫ ማናቸውም የግዥ ውሳኔ የሚሰጥበት መስፈርት እና በእያንዳንዱ ግዥ ላይ የሚሰጠው ውሣኔ ጉዳዩ ለሚመለከታቸው ሁሉ ግልፅ እና ፍትሐዊ መሆኑን፤

፬ ውሣኔዎች እና የተወሰዱ እርምጃዎች ተጠያቂነት የሚያስከትሉ መሆኑን፤

፭ የመንግሥት ንብረት በጥንቃቄ መያዝኑና ለታለመለት ዓላማ መዋሉን፡፡

## ፮ ዓለም አቀፍ ግዴታዎች

፩ ይህ አዋጅ የፌዴራል መንግስት ከአንድ ወይም ከአንድ በላይ ከሆኑ መንግስታት ወይም ዓለም ዓቀፍ ድርጅቶች ጋር ባደረገው ወይም በሚያደርገው ስምምነት ወይም ከስምምነቱ ከመነጨ ግዴታ ጋር የማይጣጣም ከሆነ በስምምነቱ የተመለከተው ይፀናል፡፡

## 5. Principles of Public Procurement and Property Administration

Public procurement and property administration shall have to comply with the following principles:

1/ ensure value for money in the use of public fund for procurement;

2/ non discrimination among candidates on grounds of nationality or race or any other criteria not having to do with their qualification, except in cases of preference specifically provided for in this Proclamation;

3/ transparency and fairness of the criteria on the basis of which decisions are given in public procurement as well as of decisions in each procurement;

4/ accountability for decisions made and measures taken with regard to public procurement and property administration;

5/ careful handling and proper use of public property.

## 6. International Obligations

1. To the extent that this Proclamation conflicts with an obligation of the Federal Government under or arising out of an agreement with one or more other states or with an international organization, the provisions of the agreement shall prevail thereof.

፪ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ ፩ ላይ የተመለከተው ስምምነት ለኢትዮጵያ ወይም በኢትዮጵያ ነዋሪ ለሆኑ ተጫራቾች ልዩ አስተያየት የሚፈቅድ በሚሆንበት ጊዜ የመንግስት መስሪያ ቤቱ ተፈፃሚ የሚሆነውን ልዩ አስተያየት በጨረታ ሰነድ ውስጥ በግልጽ ማመልከት አለበት፡፡

**፯ የግዥና ንብረት አስተዳደር መመሪያዎችና ሰነዶችን ሕዝቡ እንዲያውቅ ስለማድረግ**

ይህ አዋጅ እና በዚህ አዋጅ መሠረት በቢሮው የሚወጡ የግዥ እና የንብረት አስተዳደር መመሪያዎች እና ሌሎች የግዥ እና ንብረት አስተዳደር ሰነዶች ሕዝቡ እንዲያውቋቸው ማድረግ እና ለአጠቃቀም አመቺ በሆነ መንገድ በሥርዓት መያዝ አለባቸው፡፡

**፰ የመንግስት መስሪያ ቤት የበላይ ኃላፊ ኃላፊነት**

፩ የመንግስት መስሪያ ቤቶች ስለሚያከናውኑት ግዥ እና ለሚያስተዳድሩት ንብረት ጠቅላላ ኃላፊነት ያለባቸው ሲሆን፣ በተለይም የመንግሥት መስሪያ ቤት የበላይ ኃላፊ ቢሮው በሚያወጣው መመሪያ ላይ ከሚገለጹት ዝርዝር ኃላፊነትና ተግባራት በተጨማሪ የሚከተሉት አጠቃላይ ኃላፊነትና ተግባራት ይኖሩታል፡-

2. Where an agreement referred to in sub-article (1) of this Article contains a preference or preferences in favour of national and resident bidders, the public body shall ensure that the applicable preference or preferences are clearly stated in the bidding documents.

**7. Public Accessibility of Legal Texts**

This Proclamation and the procurement and property administration directives to be issued by the bureau as well as other documents pertaining to public procurement and property administration shall be made accessible to the public and retained in a convenient manner.

**8. Responsibilities of Heads of Public Body**

1. Public bodies shall have overall responsibility for procurements they carry out and the property they administer. In particular, the head of a public body shall, apart from those detailed responsibility and duties, specified in the directives to be issued by the bureau, have the following general responsibilities:

ሀ. በተገቢው የሰው ኃይል የተሟላ የግዥና ንብረት አስተዳደር ተግባርን የሚያከናውን የሥራ ሂደት ያደራጃል፤

ለ. ከፍተኛ የገንዘብ መጠን ያላቸውን ግዥዎች መርምሮ የሚያፀድቅ ኮሚቴ ያቋቁማል፤ውስብስብ ለሆኑ ግዥዎች ጊዜያዊ የግዥ ኮሚቴ ሊያቋቁም ይችላል፤

ሐ. በግዥና ንብረት አስተዳደር ሥራ ላይ የሚመደቡ ወይም የተመደቡ ሠራተኞች እንዲሁም የግዥ አጽዳቂ ኮሚቴ አባላት፣ ይህንን አዋጅ፣ የአፈጻጸም መመሪያውን፣ የግዥ ማንዋል፣ መደበኛ የጨረታ ሰነድ እና ሌሎች ተገቢ ቅፆች ይዘት እና አጠቃቀም እንዲያውቁ ማድረግ የሚያስችል ስልጠና ማግኘታቸውን እና የመንግስት ግዥ እና ንብረት አስተዳደርን ለመፈፀም በቂ ክህሎት ያላቸው መሆኑን ያረጋግጣል፤

መ. የመንግስት ግዥ በእቅድ ላይ የተመሠረተ እና በዚህ አዋጅ የተመለከቱ የግዥ መርሆዎችን የጠበቀ መሆኑን ይከታተላል፣ ይቆጣጠራል፤

ሠ. የግዥና ንብረት አስተዳደር የሥራ ሂደት፣ የግዥ አጽዳቂ ኮሚቴ እና ሌሎች ግዥን የመፈጸም ኃላፊነት የተሰጣቸው አካላት ተግባራቸውን በተገቢው ሁኔታ መወጣታቸውን ያረጋግጣል፤

ረ እንደ አስፈላጊነቱ የግዥ ሥርዓት የሚያስፈ ፅሙ ሦስተኛ ወገኖችን ይቀጥራል፡፡

a) Organize an adequately staffed work process for procurement and property administration;

b) setup a procurement endorsing committee which approves procurements of higher value; it may also setup ad hoc procurement committee for complex procurement;

c) ensure that staff and employees assigned in the procurement and property administration and those assigned asmembers of the procurement endorsing committee receive training to enable them acquire knowledge of the content and application ofthis Proclamation, the directives to be issued in accordance with this Proclamati on, the procurement and property administration manuals, the standard bidding documents and other relevant forms;

d) ensure that the procurement of the public body is preplanned and complies with procurement principles enshrined in this Proclamation;

e) ensure that the the proper functioning of procurement and property administration department, the procurement endorsing committee and other sections of the public body involved in procurement ;

f) where necessary, assign third parties which execute the system of procurement;

ሰ የመንግሥት ንብረት ኢኮኖሚያዊ እና ውጤታማ በሆነ መንገድ አገልግሎት ላይ መዋሉን ያረጋግጣል፤

ሸ በመስሪያ ቤቱ ሥር የሚገኘው የመንግሥት ንብረት በሚገባ የተመዘገበ እና የክትትል ሥርዓት የተዘረጋለት፣ ተገቢው ጥበቃና እንክብካቤ የተደረገለት፣ አገልግሎት የማይሰጥ ሆኖ ሲገኝ በወቅቱ እንዲወገድ መደረጉን ያረጋግጣል፡፡

## ፱ የግዥና ንብረት አስተዳደር ሥራ ሂደት ተግባር እና ኃላፊነት

በመንግሥት መሥሪያ ቤቶች ውስጥ የሚቋቋመው የግዥና ንብረት አስተዳደር የሥራ ሂደት በግዥ መመሪያና በመሥሪያ ቤቱ በሚዘጋጀው የሥራ ዝርዝር ከሚሰጡት ኃላፊነቶች በተጨማሪ የሚከተሉት አጠቃላይ ተግባራት ይኖሩታል፡-

፩ የመንግሥት ግዥን በተሟላ የሙያ ስነ ምግባር እና ክህሎት ይፈጽማል፤

፪ ይህንን አዋጅ፣ የአፈፃፀም መመሪያውን፣ የግዢ ማኑዋል፣ መደበኛ የጨረታ ሰነድ ፣የአፈጻጸም ቅጾችን እና የግዥ ውሉን መሠረት በማድረግ የመንግሥት ግዥን ይፈፅማል፤

፫ በዚህ አዋጅ አንቀፅ ፳፫ በተደነገገው መሰረት ለግዢው የተሟላ መረጃ ይይዛል፣ በተጠየቀ ጊዜም ያቀርባል፡፡

g) ensure that property at the disposal of the public body is used in such a manner as to achieve economy and efficiency;

h) ensure that property at the disposal of the public body is duly registered and traceable, properly handled and looked after and disposed off when it is no longer useful.

## 9. Duties and Responsibility of Procurement and Property Administration Work process

The procurement and property administration work process established in a public body shall, apart from the responsibilities assigned to it by the procurement directives and the job description prepared by the public body, have the following duties and responsibilities**:**

a) Execute public procurement in a perfectly ethical and skillful manner;

b) carry out public procurement in accordance with this Proclamation, the procurement directives, the procurement manual , the standard bid documents, the forms and the procurement contract;

c) maintain complete record for each procurement in accordance with Article 23 of this Proclamation.

## ፲ የግዥ አጽዳቂ ኮሚቴ ተግባርና ኃላፊነት

የግዥ አጽዳቂ ኮሚቴ የሚከተሉት ተግባርና ኃላፊነቶች ይኖሩታል፡-

፩ በግዥ መመሪያው ላይ የተቀመጠው የገንዘብ ገደብ እንደተጠበቀ ሆኖ የመንግሥት ግዥ ይህን አዋጅ፣ የአፈጻጸም መመሪያውን፣ የግዥ ማኑዋል፣ መደበኛ የጨረታ ሰነድ እና ሌሎች ቅፆችን መሠረት በማድረግ የተፈፀመ መሆኑን ያረጋግጣል፤

፪ በግዥ መመሪያው ላይ የተቀመጠው የገንዘብ ገደብ እንደ ተጠበቀ ሆኖ የጨረታ ወይም የግዥ ግምገማ ሪፖርቶችን መርምሮ ያፀድቃል፤

፫ የመንግሥት ግዥን ውጤታማ ለማድረግ በሚያስችሉ ዘዴዎች ላይ የመስሪያ ቤቱን የበላይ ኃላፊ ያማክራል፡፡

## ፲፩ ተጠያቂነት

በመንግሥት መሥሪያ ቤቶች ለግዥና ንብረት አስተዳደር ሥራ የተመደቡ ሠራተኞች ወይም የመንግሥት ግዥን እና ንብረትን ለማስተዳደር የተሾሙ ኃላፊዎች እና የግዥ አጽዳቂ ኮሚቴ አባሎች በዚህ አዋጅ እና ቢሮው በሚያወጣቸው መመሪያዎች መሠረት ስለሚያከናውኗቸው ተግባሮች ተጠያቂ ይሆናሉ፡፡

## 10. Duties and Responsibility of Procurement Endorsing Committee

The procurement endorsing committee shall have the following responsibilities:

1. Without prejudice to the financial limits specified under procurement directive, ensure that public procurement is executed in compliance with this Proclamation, the procurement directives, the procurement manual, the standard bid document and other forms;
2. Without prejudice to the financial limits specified under procurement directive, review and endorse bid and procurements report;
3. Advise the head of public office on methods of achieving effective procurement.

## 11. Accountability

Procurement and property administration staff or head appointed to lead procurement and property administration units and members of the procurement endorsing committee in public bodies shall be accountable for their actions in accordance with this Proclamation and the directives to be issued by the Bureau.

## ምዕራፍ ሁለት

## የክልሉ መንግስት ግዥና ንብረት አስተዳደር ኤጀንሲ

### ፲፪ የኤጀንሲው መቋቋም

፩ የክልሉ መንግስት ግዥና ንብረት አስተዳደር ኤጀንሲ ከዚህ በኃላ "ኤጀንሲ" እየተባለ የሚጠራው ራሱን የቻለና የሕግ ሰውነት ያለው የክልሉ መንግስት መስሪያ ቤት ሆኖ በዚህ አዋጅ ተቋቁሟል ፡፡

፪ ኤጀንሲው ተጠሪነቱ ለቢሮው ይሆናል፡፡

### ፲፫ ዋና መስሪያ ቤት

የኤጀንሲው ዋና መስሪያ ቤት በሀዋሳ ከተማ ሆኖ እንደአስፈላጊነቱ በክልሉ በማናቸውም ስፍራ ቅርንጫፍ መስሪያ ቤቶች ሊኖሩት ይችላል፡፡

### ፲፬ የኤጀንሲው ዓላማዎች

ኤጀንሲው የሚከተሉት ዓላማዎች ይኖሩታል፡-

፩ ፍትሃዊ፣ በውድድር ላይ የተመሰረተ፣ ግልጽ፣አድልዎ የሌለበት፣ለመንግስት ገንዘብ ተመጣጣኙን ዋጋ ማስገኘት የሚያስችል የግዥ አፈጻፀምና ዘመናዊ የመንግስት ንብረት አስተዳደር መኖሩን ማረጋገጥ፤

፪ የክልሉ መንግስት መስሪያ ቤቶች በዚህ አዋጅ የተዘረዘሩትን ጠብቀው መሥራታቸውን መከታተል፤

## CHAPTER WO

## THE PUBLIC PROCUREMENT AND PROPERTY ADMINISTRATION AGENCY

### 12. Establishment

1. The region Public Procurement and Property Administration Agency (hereinafter referred to as the “Agency") is hereby established as an autonomous state organ having its own juridical personality.

2. The Agency shall be accountable to the Bureau.

### 13. Head Office

The head office of the Agency shall be situated in Hawassa and may have branch offices else where in the region as may be necessary.

### 14. Objectives of the Agency

The Agency shall have the following objectives

1. ensure the application of fair, competitive, transparent, non-discriminatory and value for money procurement and modern public property administration;

2. follow up the compliance of public bodies of the region with the provisions of this Proclamation in conducting their function ;

፫ በክልሉ ውስጥ ያለውን የግዥ አፈጻፀም እና የንብረት አስተዳደር አቅም ማሳደግ፤

፬ የክልሉ የግዥና ንብረት አስተዳደር ስርዓት ተቀባይነት ካላቸው ከሀገሪቱ እና አለም አቀፍ ስርዓቶች ጋር የተጣጣመ እንዲሆን ጥረት ማድረግ ናቸው።

## ፲፭ የኤጀንሲው ተግባሮች

ኤጀንሲው ከዚህ በታች የተዘረዘሩትን ተግባሮች ያከናውናል፦

፩ በመንግስት ግዥ እና ንብረት አስተዳደር ፖሊሲዎች፣መርሆዎችና አፈጻፀሞች ላይ የክልሉን መንግስት ማማከር፣ለክልል ሴክተር ቢሮዎች፣ለዞኖች ፣ለልዩ ወረዳዎችና ለከተማ አስተዳደሮች የቴክኒክ ድጋፍ መስጠት፤

፪ በክልሉ ውስጥ ያለውን የመንግስት ግዥ አፈጻፀም እና የንብረት አስተዳደር ስርዓት ተግባራዊነት መከታተል፣ ለቢሮው ሪፖርት ማድረግ እና በህግና በአፈጻፀም ስርዓቱ ላይ የማሻሻያ ሀሳቦች ማቅረብ፤

፫ አግባብነት ካላቸው አካላት ጋር በመተባበር የግዥ እና ንብረት አስተዳደር ስልጠና እንዲሁም የግዥ እና ንብረት አስተዳደር አፈፃፀምን ለመምራት የሚያስፈልገው ችሎታ፣ በሙያው ለመሰማራት ተፈላጊ የሆነው ማስረጃ አይነት እና የሙያው እድገት ሊከተል የሚገባውን ሂደት መወሰኑን ማረጋገጥ፤

3. build the capacity of procurement and property administration execution of the Region ;
4. strive public procurement and property administration system to be consistent with national and with the internationally recognized standards;

## 15. Functions of the Agency

The Agency shall perform the following functions:

1) advise the Regional state on all public procurement and property administration policies, principles and implementation and provide technical assistance to the sector bureaus,zones,special woredas, and city administrations;
2) monitor the performance of the public procurement and property administration systems of the Region,report to the bureau thereon, initiate amendments on laws and implementation system improvements;
3) in collaboration with competent authorities ensure the setting of training standards, competence levels, certification requirements and professional development paths of public procurement and property administration;

፬ መደበኛ የግዥ ሰነዶች ፣አሰራሩን የሚመሩ ቅጾች እና ሌሎች ለግዥና ንብረት አስተዳደር አግባብነት ያላቸውን ሰነዶች በማዘጋጀት ስራ ላይ እንዲውሉና ወቅታዊ እንዲሆኑ ማድረግ፤

፭ ከተፈቀዱ መደበኛ የግዥ ዘዴዎች፣ ሰነዶች፣ አሰራሩን ከሚመሩ ቅጾች እና ሌሎች ለግዥ አፈጻፀም አግባብነት ካላቸው ሰነዶች ውጭ ግዥ ለመፈፀም ወይም ከተፈቀዱ የንብረት አወጋገድ ስርዓቶችና ስልቶች ውጭ ንብረት ለማስወገድ በመንግስት መስሪያ ቤቶች ጥያቄ ሲቀርብለት ጥያቄውን መርምሮ ውሳኔ መስጠት፤

፮ በመንግስት ግዥ ለመሳተፍ ፍላጎት ያላቸውን አቅራቢዎች ድርጅቶቻቸው በሚገኙበት የዞንና ልዩ ወረዳ ፋይናንስና ኢኮኖሚ ልማት መምሪያ ወይም ጽ/ቤት የሚመዘገቡበት የተቀላጠፈ ሥርዓት እንዲኖር ማድረግ፣ በየዞንና ልዩ ወረዳ ፋይናንስና ኢኮኖሚ ልማት መምሪያዎች ወይም ጽ/ቤቶች በአቅራቢዎች ዝርዝር ውስጥ የተመዘገቡበትን ዝርዝር ከየዞኑና ልዩ ወረዳዎች እንዲላክልት በማድረግ አንድ ላይ አጠናክሮ ለክልሉ መንግስት ግዥ ፈፃሚ መስሪያ ቤቶች ማሰራጨት፤

፯ በእጩ ተወዳዳሪዎችና በአቅራቢዎች ላይ የመንግስት መስሪያ ቤቶች የሚያቀርቧቸውን አቤቱታዎች መርምሮ ውሳኔ መስጠት፣ የውሳኔውን ቅጅ ለሚመለከታቸው ማሰራጨት፤

4. Prepare,utilize and update and issue authorized versions of the standard bidding documents, procedural forms and any other attendant documents pertaining to procurement and property administration;
5. Review and decide on request from public offices to deviate from the prescribed methods of procurement, the standard bidding documents, procedural forms and any other attendant documents in effecting procurement or use other systems or methods of disposing of public property than those authorized by law;
6. Cause to be introduce an efficient system of listing across zone and special woreda finance and econonomic development department or office under which suppliers who are interested to participate in public procurement are to be registered in their vicinity;cause the list of suppliers registered across zone and special wored finance and economic development department or office to be sent and compile and dissiminate to public procurement bodies of the region.

7/ Review and decide on complaints submitted by public bodies on the conduct of bidders or suppliers, and send copies of such decision to the concerned organs;

፰ ከመንግስትመስሪያ ቤቶች ጋር ባደረጉት የግዥ ውል መሰረት ግዴታቸውን አለመወጣታቸው ፣ ስለብቃታቸው ሀሰተኛ መረጃ በማቅረባቸው ወይም በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፲፮(፫) እና ፴፪(፪) ላይ የተዘረዘሩት ድርጊቶች በመፈጸማቸው ምክንያት በመንግስት ግዥ አፈጻፀም እንዳይሳተፉ ያገዳቸውን አቅራቢዎች ዝርዝር መያዝና ለክልሉ ግዥ ፈፃሚ መ/ቤቶችና ለፌዴራል ግዥና ንብረት አስተዳደር ኤጀንሲ ማሰራጨት፤

፱ የግዥ አፈጻፀም እና የንብረት አስተዳደር ተግባራት ይህንን አዋጅ እና ሌሎች የመንግስት ግዥና እና ንብረት አስተዳደር የሚመራባቸውን ሰነዶች ጠብቀው የተከናወኑ መሆኑን ለማረጋገጥ የግዥ ኦዲት ማድረግ ፤

፲ ለግዥ አፈጻፀም እና ንብረት አስተዳደር የሚያገለግል የመረጃ ማሰራጫ እና ክምችት ማቋቋም ፣ማጎልበት፣መጠበቅ እና ወቅታዊነቱ የተጠበቀ እንዲሆን ማድረግ፤

፲፩ የተቋም እና የሰው ሀይል አቅም ለማጎልበት የሚያስችል የአቅም ግንባታ ፖሊሲና እቅድ እንዲኖር ማድረግ፤

፲፪ የሙያና ከሙያ ጋር በተያያዙ አግባብነት ባላቸው ጉዳዮች ላይ የተሰማሩ ሆነው በመንግስት ግዥ እና ንብረት አስተዳደር ለመሳተፍ ፍላጎት ካላቸው አካላት ጋር ተቋማዊ ግንኙነት መፍጠር እና ማዳበር፤

፲፫ ስለመንግስት ግዥ አፈጻፀም እና ንብረት አስተዳደር ጥናት ማካሄድ፣የአቅም ግንባታ ትብብር እንዲኖር ማድረግ፤

8. maintain a list of suppliers being suspended from public procurement by reason of having seriously neglected their obligations under a public procurement contract, or having provided false information about their qualifications or having committed the acts referred to in Article 16(3) and 32(2) of this Proclamation and dissiminate such information to procurement bodies of the region and federal procurement and property administration agency.
9. Conduct procurement audit to ensure that procurement and property administration activities of public bodies are in accordancewith this Proclamation and other documents governing public procurement and property administration;
10. Set up, develop, maintain and update a data base that covers the entire spectrum of public procurement and property administration;
11. Develop policies and maintain an operational planon capacity building of the institution and human resource development;
12. Establish and develop institutional linkages with entities working for the development of a profession and related matters who have an interest to participate in public procurement and property administration;
13. Conduct research on public procurement execution and property administration and establish cooperation in the area of capacity building;

፲፬ ይህን አዋጅና በአዋጁ መሰረት የሚወጡ ደንቦችና መመሪያዎች እንዲሁም በቢሮው የተሰጡት ሌሎች ተግባሮች በትክክል ስራ ላይ መዋላቸውን ማረጋገጥ፤

፲፭ ከመንግስት መስሪያ ቤቶች የሚቀርብለትን መረጃ መሰረት በማድረግ የመንግስት ግዥና ንብረት አስተዳደር ስርዓት በሚገባ የሚሰራ ስለመሆኑ ለቢሮው የየሩብ አመትና አመታዊ ሪፖርት ማቅረብ፣ቢሮው በሚጠይቀው ዝርዝር መሰረት በእያንዳንዱ የመንግስት መስሪያ ቤት ስለተከናወነው ግዥ አይነት እና መጠን እንዲሁም ንብረት አስተዳደር ጉዳዮች ልዩ መረጃዎችን መስጠት፤

፲፮ በዚህ አዋጅ በመንግስት ግዥ አፈጻፀምና ንብረት አወጋገድ ላይ በእጩ ተወዳዳሪዎች የሚቀርቡ አቤቱታዎችን እንዲያይ ለተቋቋመው ውሳኔ ሰጪ ቦርድ የጽህፈት ቤትና የቴክኒክ ድጋፍ አገልግሎት መስጠትና የቦርዱን ውሳኔዎች ተግባራዊነት መከታተል፤

፲፯ በፌደራል መንግስት ግዥ አፈጻፀም ላይ እንዳይሳተፉ የታገዱ እጩ ተወዳዳሪዎች በክልሉ መንግስት መስሪያ ቤቶች ግዥ እንዳይሳተፉ ማድረግ፤

፲፰ በክልሉ መንግስት መስሪያ ቤቶች አገልግሎት ላይ ለሚውሉ ዋና ዋና ቋሚ ንብረቶች ደረጃ ማውጣት፣ አፈጻፀሙን መከታተል::

14. Ensure the proper implementation the provisions of this Proclamation, regulations and directives to be issued in accordance with this Proclamation and other functions given to it by the Bureau;

15. submit quarterly and annuall report to the Bureau regarding the overall functioning of the public procurement and property administration system based on information provided to it by public bodies and provide special data up on the request of the bureau regarding the nature and volume of public procurement handled by each entity; as well as on matters of property administration;

16. Provide office facilities and technical support for the board established by this Proclamation to review complaints of candidates in public procurement and disposal of public property and follow up the implementation of the decisions of the board;

17. Cause any candidate suspended from participating on procurements of the federal government not to participate in public procurements of the region;

18. Set a standard for major items of fixed assets used for public bodies of the region and follow-up adherence to such standards.

## ፲፮ የኤጀንሲው ስልጣን

ኤጀንሲው ስራውን ለማከናወን የሚከተሉት ስልጣን ይኖሩታል፡-

፩ ማናቸውም የመንግስት መስሪያ ቤት ወይም አቅራቢ ህግ ከሚያዘው ውጪ ግዥ ስለመፈጸሙ፣ግዥ በትክልል ስላለማከናወኑ፣የግዥውን አሰራር በትክክል ስላለመፈፀሙ ወይም ስለመመሳጠሩ ጥቆማ የቀረበ እንደሆነ ከግዥው አፈጻፀም ጋር የተያያዙ መረጃዎች፣ሰነዶች፣ መዝገቦች እና ሪፖርቶች እንዲቀርቡለት የማዘዝ፤

፪ ምስክሮችን የመጥራት፣ምስክሮችና ግዥው የሚመለከታቸው ወገኖች ቃላቸውን በመሀላ እንዲሰጡ ፣የሂሳብ መዝገብ ፣ፕላን ፣ሰነድ እንዲቀርብለት የማድረግ ፤

፫ ከገበያ ጋር የማይጣጣም ዋጋ በሚያቀርቡ እና ሌሎችንም የዚህን አዋጅና በቢሮው የሚወጡትን የደንብ እና የመመሪያ ድንጋጌዎችን የሚቃረኑ ተግባራትን የሚፈጸሙ እጩ ተወዳዳሪዎች ፣አቅራቢዎች ወይም በመንግስት ንብረት ማስወገድ ሂደት ተሳታፊዎች ላይ በቀረበ አቤቱታ መነሻነት ማስጠንቀቂያ የመስጠት፣ለተወሰነ ወይም ላልተወሰነ ጊዜ በመንግስት ግዥ ወይም የንብረት ማስወገድ ሂደት እንዳይሳተፉ የማገድ ፤

## 16. Powers of the Agency

In the exercise of its functions, the Agency shall have the power to:

1. Order any information, documents, records and reports to be presented in respect of any aspect of the public procurement process where a breach, wrongdoing, mismanagement or collusions has been reported against any public body or supplies;

2. Summon witnesses, call for the production of books of accounts, plans, documents and examine witnesses and parties concerned on oath;

3. Warn or suspend candidates, suppliers or persons involved in the disposal of public property for a definite or indefinite period of time from participating in public procurement or disposal of public property where it proves that they have offered a price higher than the market and committed an act in breach of the provisions of this Proclamation and the regulation and directives to be issued by the Bureau;

፬ በመንግስት ግዥ እና ንብረት አስተዳደር አፈጻፀም ላይ በራሱ ፕሮግራም ወይም በሚደርሰው ጥቆማ መነሻነት ኦዲት ማካሄድ ወይም እንዲካሄድ ማድረግ፤

፭ በቂ ምክንያት ያለ መሆኑን ሲረዳ በዚህ አዋጅና በግዥ መመሪያው ከተፈቀዱ የግዥ ስርዓቶች ውጪ ግዥ ለመፈጸም ከመንግስት መስሪያ ቤቶች በሚቀርቡ ጥያቄዎች መሰረት እንዲፈጸም መፍቀድ፡፡

## ፲፯ የኤጀንሲው ድርጅታዊ አቋም

**ኤጀንሲው ፡-**

፩ በመንግስት የሚሾም አንድ ዋና ዳይሬክተር እና ምክትል ዋና ዳይሬክተር፤

፪ ሌሎች አስፈላጊ ሰራተኞች፤ ይኖሩታል፡፡

## ፲፰ የዋናው ዳይሬክተር ስልጣንና ተግባር

፩ ዋናው ዳይሬክተር የኤጀንሲው ዋና ስራ አስፈጻሚ ሆኖ ከቢሮው በሚሰጠው አጠቃላይ መመሪያ መሰረት የኤጀንሲውን ስራዎች ይመራል፣ ያስተዳድራል፡፡

፪ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ ፩ ላይ የተጠቀሰው ጠቅላላ አገላለጽ እንደተጠበቀ ሆኖ ዋናው ዳይሬክተር፡-

ሀ. በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፲፭ እና ፲፮ የተመለከቱትን የኤጀንሲውን ስልጣንና ተግባሮች ስራ ላይ ያውላል ፤

4. conduct audit on its own program or cause audit to be conducted where it receives allegations of misconduct warranting such audit on a process of public procurement and property administration;
5. upon the request of public bodies, exceptionally and when it is justified on sound grounds, may permit the use of a procedure which is not consistent with the procedures laid down by this Proclamation or the procurement directive.

## 17**. Organization of the Agency**

The Agency shall have:

1. A Director General and Deputy Director General to be appointed by the state; and
2. The necessary staff.

## 18**.Powers and Duties of the Director General**

1. The Director General shall be the chief executive officer of the Agency and shall, subject to the general directives of the Bureau, direct and administer the activities of the Agency.
2. Without prejudice to the generalities of the provisions of sub-article (1) of this Article, the Director General shall:

a) exercise the powers and functions of the Agency specified under Articles 15 and 16 of this Proclamation;

ለ. በክልሉ ሲቪል ሰርቪስ ህግ መሰረት የኤጀንሲውን ሰራተኞች ይቀጥራል፣ያስተዳድራል፣ያሰናብታል፤

ሐ. የኤጀንሲውን የስራ ፕሮግራምና በጀት አዘጋጅቶ ያቀርባል፣ሲፈቀድም ስራ ላይ ያውላል፤

መ. የኤጀንሲውን የስራ ክንውን እና የሂሳብ ሪፖርት አዘጋጅቶ ያቀርባል፤

ሠ. ከሶስተኛ ወገኖች ጋር በሚደረጉ ግንኙነቶች ሁሉ ኤጀንሲውን ይወክላል፡፡

፫ ዋናው ዳይሬክተር ለኤጀንሲው የስራ ቅልጥፍና በሚያስፈልግ መጠን ስልጣንና ተግባሩን በከፊል ለኤጀንሲው ሰራተኞች በውክልና ሊያስተላልፍ ይችላል፡፡

b) employ, administer and dismiss personnel of the Agency in accordance with the Civil Service law of the region ;

c) prepare the work program and budget of the Agency and implement the same upon approval;

d) prepare and submit performance and financial report of the Agency;

e) represent the Agency in all its relations with third parties.

3. The Director General may delegate part of his powers and duties to the employees of the Agency to the extent necessary for the effective management of the functions of the Agency.

## ፲፱ <u>የምክትል ዋና ዳይሬክተር ስልጣንና ተግባር</u>

፩ ምክትል ዋና ዳይሬክተሩ ከዋናው ዳይሬክተር በሚሰጠው መመሪያ መሰረት የኤጀንሲውን ተግባራት ማቀድ፣ በማደራጀት ፣ በመምራትና በማስተባበር ዋና ዳይሬክተሩን ያግዛል፡፡

፪ ዋና ዳይሬክተሩ በማይኖርበት ጊዜ ለዋና ዳይሬክተሩ የተሰጡትን ስልጣንና ተግባራት ምክትል ዋና ዳይሬክተሩ ያከናውናል፡፡

## 19. **<u>Powers and Duties of the Deputy Director General</u>**

1. Subject to directions given from the Director General, the Deputy Director General shall assist the Director General in planning, organizing, directing and coordinating the activities of the Agency.

2. The Deputy Director General shall act on behalf of the Director General in his absence.

## ፳ <u>የበጀት ምንጭ</u>

የኤጀንሲው በጀት በክልሉ መንግስት የሚመደብ ይሆናል፡፡

## 20. **<u>Source of Budget</u>**

The budget of the Agency shall be allocated by the regional state.

## ፳፩ <u>የሂሳብ መዛግብት</u>

፩ ኤጀንሲው ትክክለኛና የተሟሉ የሂሳብ መዛግብት ይይዛል፡፡

፪ የኤጀንሲው የሂሳብ መዛግብት እና ሌሎች ገንዘብ ነክ ሰነዶች በዋናው ኦዲተር ወይም በዋናው ኦዲተር በሚሰየም ኦዲተር በየአመቱ ይመረመራሉ፡፡

## ምዕራፍ ሶስት

## <u>መሠረታዊ የግዥ ድንጋጌዎች</u>

## ፳፪ <u>የግዥ ዕቅድ</u>

፩ የመንግስት መሥሪያ ቤቶች በበጀት ዓመቱ የሚፈጽሙትን ግዢ የሚያሳይ ቢሮው በሚያወጣው መመሪያ ላይ የሚገለጹትን ዝርዝር ጉዳዮች ያካተተ ዓመታዊ የግዢ ዕቅድ ማዘጋጀት ይኖርባቸዋል፡፡

፪ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ ፩ መሠረት የተዘጋጀው የግዢ ዕቅድ በመስሪያ ቤቱ ኃላፊ ፀድቆ ለሚመለከታቸው የመስሪያ ቤቱ የሥራ ሂደቶችና ለኤጀንሲው በየዓመቱ እስከ ሀምሌ ፴ መላክ ይኖርበታል፡፡

## ፳፫ <u>የግዥ ሰነዶች</u>

፩ የመንግሥት መሥሪያ ቤቶች ከመንግሥት ግዥ ጋር የተያያዙ መዝገቦችን እና ሰነዶችን ግዥው ከተፈጸመበት ቀን አንስቶ ቢሮው በሚያወጣው መመሪያ ላይ እስከሚገለፀው ጊዜ ድረስ ማቆየት አለባቸው፡፡ በዚህ ዓይነት የሚያዙት መረጃዎች የሚከተሉትን ይጨምራሉ፡-

## 21. **<u>Books of Accounts</u>**

1. The Agency shall keep complete and accurate books of account.
2. The books of accounts and other financial documents of the Agency shall be audited annually by the Auditor General or by an auditor designated by him.

## **<u>CHAPTER THREE</u>**

## **<u>BASIC PROCUREMENT PROCEDURES</u>**

## 22. **<u>Procurement Plan</u>**

1. Public bodies shall have to prepare an annual procurement plan showing their procurement for the concerned budget year and containing such details as are stated in the directive to be issued by the Bureau.
2. The procurement plan to be prepared by public bodies in accordance with sub-article (1) of this Article, shall have to be approved by the head of the concerned public body concerned and communicated to the relevant departments of the public body and the Agency until Hamle 30 of each year.

## 23.**<u>Records of Procurement</u>**

1. Public bodies shall have to maintain records and documents regarding their public procurement starting from the date of procurement conclusion to a for such period of time as is determined by the directive to be issued by the Bureau . Such information shall include the following:

ሀ. የሚገዙት ዕቃዎች፣ የግንባታ ሥራዎች ወይም አገልግሎቶች አጭር መግለጫ፤

ለ. የጨረታ ማስታወቂያ፤

ሐ. የጨረታ መወዳደሪያ ሀሣብ ያቀረቡ አቅራቢ-ዎች ስምና አድራሻ እንዲሁም በጨረታው አሸናፊ የሆኑ ተጫራቾች ስምና አድራሻ፤

መ. ለጨረታ ግምገማ የተዘጋጀውን መስፈርት እና ተፈጻሚ የተደረገበትን ሁኔታ፣ የጨረታ ግምገማ፣ የውድድሩን አፈፃፀም፣ ከተወዳ ዳሪዎች የቀረበውን የመወዳደሪያ ሀሣብ እና የዋጋ ማቅረቢያ የሚያሳይ አጭር መግለጫ፤

ሠ. አቤቱታ ቀርቦ ከሆነ የውሳኔ አሰጣጥ ሂደቱን የሚያሣይ መረጃ፣ እና

ረ. ከግልጽ ጨረታ ውጪ ሌሎች የግዥ ሥርዓቶችን መከተል የተመረጠበትን ምክንያት፡፡

፪ የግዥው ሂደት ተጠናቆ ከአሸናፊው ጋር ውል ከተፈረመ ወይም በማናቸውም ምክንያት ውሉ ከተቋረጠ በኂላ የግዥውን ዝርዝር አፈፃፀም የሚያሣየው መረጃ በጨረታው እጩ ተሳታፊ የሆኑ ተወዳዳሪች ሲጠይቁ እንዲያዩት መደረግ አለበት፡፡ ይሁን እንጂ በህግ ሥልጣን ከተሠጠው አካል ወይም ፍርድ ቤት ካልታዘዘ እና በፍርድ ቤቱ በተሰጠው ትዕዛዝ በተመለከተው መሠረት ካልሆነ በስተቀር ግዥ ፈፃሚው አካል የሚከተሉትን መረጃች መስጠት የለበትም፡-

a) a brief description of the goods,constriaction works or services to be procured;

b) the invitation to bid;

c) the names and addresse of suppliers being submitted bid, proposal or quotations, and the name and address of the winning suppliers;

d) the evaluation criteria being stipulated and applied to the bid and a summary of the evaluation and comparison of bids, proposals and quotations received;

e) information on the proceeding of any decision rendered where a complaint against a procurement process is lodged;

f) the grounds for using a procurement procedure other than open bidding.

2. The record concerning any proceeding shall, on request, and once the proceedings have resulted in a contract or have otherwise been terminated, be made available to candidates who participated in the proceedings. However, except when ordered to do so by a competent court or other body authorized by law and subject to the conditions of such an order, the pblic body shall not disclose:the following information to any body

ሀ. የመረጃው ይፋ መሆን በሕግ የማይፈቀድ፣ የሕግ አፈጻጸምን የሚያሰናክል፣ የሕዝብን ጥቅም የሚቃረን፣ የተዋዋዮችን ሕጋዊ የንግድ ጥቅም እንዲሁም ቀና ውድድርን የሚጎዳ ከሆነ፤

ለ. በዚህ አንቀጽ በንዑስ አንቀጽ ፩ /መ/ በተመለከተው መሠረት በማሳጠር የተዘጋጀውን ሰነድ ካልሆነ በስተቀር ከተጫራቾች የቀረበውን የመወዳደሪያ ሀሣብ ከመመርመር እና ከመገምገም ተግባር ጋር የተያያዙ መረጃዎችን እና ተጫራቾች ያቀረቡዋቸውን የመወዳደሪያ ሀሣቦች እና የጨረታ ሰነዶች ይዘት የሚገልፁ መረጃ-ዎች፡፡

## ፳፬ አድልዎ ያለማድረግ

በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፳፭ የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ ማንኛውም ዕጩ ተወዳዳሪ በዜግነት፣ በዘር ወይም ከመወዳደሪያ መስፈርቶች ጋር ባልተያያዙ ሌሎች ምክንያቶች በመንግሥት ግዥ አፈጻፀም ሂደት በማንኛውም ዕጩ ተወዳዳሪ ላይ አድልዎ ሊደረግ አይችልም፡፡

## ፳፭ ልዩ አስተያየት

፩ ቢሮው በሚያወጣው መመሪያ መሰረት በጨረታ ግምገማ ወቅት በኢትዮጵያ ለተመረቱ ዕቃዎች፣ በኢትዮጵያ ኩባንያዎች ለሚከናወኑ የግንባታ ዘርፍ ስራዎች እና በኢትዮጵያ ኩባንያዎች ለሚከናወኑ የምክር አገልግሎት ስራዎች ልዩ አስተያየት ይደረግላቸዋል፡፡

a) information if its disclosure would be contrary to law, would impede law enforcement, would not be in the public interest, would prejudice legitimate commercial interest of the parties or would inhibit fair competition;

b) information relating to the examination and evaluation of bids, proposal or quotations and the actual content of bid, proposals or quotations, other than in the summary record form referred to in sub- article (1)(d) of this Article.

## 24. Non-discrimination

Without prejudice to the provisions of Article 25 of this Proclamation, any candidate shall not be discriminated against in the proceeding of public procurement on the basis of nationality, race or any other criterion not having to do with their qualifications.

## 25. Preference

1. A preference margin shall, in accordance with the directive to be issued by the bureau, be given during evaluation for goods produced in Ethiopia, works carried out by Ethiopian companies and for consultancy services rendered by Etiopians

፪ በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ (፩) የተጠቀሰው እንደተጠበቀ ሆኖ አግባብ ባለው ሕግ መሠረት ለተቋቋሙ አነስተኛና ጥቃቅን ተቋማት መስተዳድር ምክር ቤቱ በሚያወጣው ደንብ መሰረት ተጨማሪ ልዩ አስተያየት ሊደረግላቸው ይችላል፡፡

፫ የዕቃዎች፣ አገልግሎቶች ወይም የግንባታ ሥራዎች ጥራትና ዋጋ ተመሳሳይ ሆኖ ተጫራቾች በግምገማ ዕኩል ነጥብ ሲያገኙ ለሀገር ውስጥ ምርቶች፣ አገልግሎቶች ወይም ኩባንያዎች ቅድሚያ ይሰጣል፡፡

፬ ለዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ ፩ አፈፃፀም ማናቸውም ዕቃ ከዋጋው ከ፴፭ መቶኛ በላይ በኢትዮጵያ ውስጥ የታከለ ከሆነ በኢትዮጵያ ውስጥ እንደተመረተ ይቆጠራል፡፡

## ፳፮ የግንኙነት ስልት

፩ በመንግሥት መስሪያ ቤቶችና በዕጩ ተወዳዳሪዎች መካከል የሚደረጉ ግንኙነቶች በጽሑፍ መደረግ አለባቸው፡፡ በጽሑፍ ያልተደረጉ ማናቸውም ግንኙነቶች በማከታተል በጽሑፍ መረጋገጥ አለባቸው፡፡

፪ ቢሮው የመረጃ ልውውጡን ትክክለኛነት እና በሚስጢር መጠበቁን ማረጋገጥ የሚያስችሉ ሥርዓቶች መዘርጋታቸውን እና በቴክኒክ ረገድ ተፈላጊ ሁኔታዎች መሟላታቸውን ሲያረጋግጥ ከጽሑፍ በተጨማሪ ወይም በጽሑፍ ምትክ በኤሌክትሮኒክስ ዘዴ ግንኙነት ማድረግ የሚያስችል መመሪያ ሊያወጣ ይችላል፡፡

2. With out prejudice to the preference provided for in sub-article (1) of this Article, further preference of such-margin as to be determined by the directive to be issued by the executive council may be allowed for small and micro-enterprises established in accordance with the pertinent law.

3. Where in the evaluation of bids for procurement of goods, services or construction works equal percentage points are resulted for bidders offering similar price and quality, preference shall be given to local goods, services or companies.

4. For the purpose of sub-article (1) of this Article, any good to which more than 35% of the value added occurs in Ethiopia, it shall be considered as being produced in The Ethiopia .

## 26. Form of Communications

1. Communications between candidates and public bodies shall be in writing. Any communications not made in written form shall be subsequently referred to and confirmed in writing.
2. Subject to necessary safeguards with regard to authenticity and confidentiality, and when technical conditions so permit, the Bureau may issue a directive to determine the extent by which communication by electronic means may be used in addition to or instead of writing.

## ፳፯ ቋንቋ

፩ ዓለም አቀፍ ተጫራቾች የሚሳተፉበት ግዢ ካልሆነ በስተቀር የአገር ውስጥ ተጫራቾች ብቻ ለሚሳተፉበት ክልላዊ ጨረታ የጨረታ ሰነድ የሚያዘጋጀውና ጨረታው የሚካሄደው በአማርኛ ቋነቋ ነው፡፡ ሆኖም ለግዢ አካሄድ አመቺ መሆኑ ከታመነበት የተሟላ ወድድርን እንደማይገድብ ተረጋግጦ የአገር ውስጥ ተጨራቾች ለሚሳተፉበት የአገር ውስጥ ጨረታ፣ የጨረታ ሰነድ እና የመጫረቻ ሰነድ በእንግሊዘኛ ቋንቋ እንዲዘጋጁ የመንግሥት መስሪያ ቤቱ ሊፈቅድ ይችላል፡፡

፪ ለዓለም አቀፍ ግዢ ጨረታ ማስፈፀሚያ የሚዘጋጁት ማናቸውም ሰነዶች በእንግሊዘኛ ቋንቋ መሆን ይኖርባቸዋል፡፡

## ፳፰ የዕጩ ተወዳዳሪዎች ብቃት

፩ በማንኛውም የመንግሥት ግዥ ለመሳተፍ ዕጩ ተወዳዳሪዎች ከዚህ በታች የተዘረዘሩትን እና የመንግሥት መሥሪያ ቤቶች ከግዥው ልዩ ባህርይ በመነሳት የሚያወጧቸውን ሌሎች መስፈርቶች ማሟላት አለባቸው፡-

ሀ. በሚገቡት ውል መሠረት ለመፈፀም የሚያስችል የሙያና የቴክኒክ ብቃት፣ የፋይናንስ አቅም፣ መሣሪያ እና ሌሎች የመገልገያ ሥፍራዎች፣ ግዥው በሚፈፀምበት ተግባር የሥራ አመራር ችሎታ፣ መልካም ዝና እና የሰው ኃይል ያላቸው፤

## 27.**Language**

1. Except where a procurement proceeding involves international bidders, for regional bids in which only local bidders participate, the bid document shall be prepared and the bid process shall be conducted in the Amharic language. However, if it is found convenient to the procurement process, the concerned public body may authorize the use of English language in the preparation of bid documents and bid proposals in a national bid in which only local bidders participate, provided that such an act is not prejudicial to fair competition.

2. For procurement to be conducted by means of international competitive bidding, all documents shall have to be prepared in English language.

## . 28**. Qualification of Candidates**

1. In order to participate in public procurement, candidates shall be required to qualify the following criteria and such other criteria, as the public body considers appropriate under the circumstances:

[

a) that they possess the necessary professional and technical qualifications and competence,financial resources, equipment and other physical facilities, managerial capability in the procurement object, reputation, and the personnel, to perform the contract;

ለ. ውል ለመፈፀም የሚያስችል የሕግ ችሎታ ያለው፤

ሐ. በዕዳ ያልተያዘ፣ ያልከሠረ ወይም የሥራ እንቅስቃሴውን ያላቋረጠ፣ የንግድ ሥራ እንቅስቃሴው ያልታገደ፣ ወይም በእነዚህ ምክንያቶች ተከሶ በክርክር ላይ ያልሆነ፤

መ. ቢሮው በሚያወጣው መመሪያ የተመለከተው እንደተጠበቀ ሆኖ ፣በአቅራቢዎች ዝርዝር ውስጥ የተመዘገበ፤

ሠ. በመንግሥት ግዥ እንዳይሳተፍ ታግዶ የነበረ ከሆነ የታገደበት ጊዜ ያጠናቀቀ፣

ረ የታደሰ የንግድ ስራ ፍቃድ ያለውና በአገሪቱና በክልሉ የግብር ሕጎች በተደነገገው መሠረት የግብርና የታክስ ግዴታውን የተወጣ፤

ሰ የባንክ ሂሣብ ያለው፡፡

፪ የመንግሥት መስሪያ ቤቱ ዕጩ ተወዳዳሪዎች በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ ፩ የተዘረዘሩት መስፈርቶችን የሚያሟሉ መሆኑን ለማረጋገጥ አስፈላጊ የሆኑ የሰነድ መረጃዎች ወይም ሌሎች መረጃዎችን እንዲያቀርቡ መጠየቅ ይችላል፡፡

፫ በዚህ አንቀጽ መሠረት ዕጩ ተወዳዳሪዎች እንዲያሟሉ የሚጠበቁት መስፈርቶች በጨረታ ሰነድ ወይም የተጫራቾችን የመወዳደሪያ ሀሣብ ለመጠየቅ በሚዘጋጁ ሰነዶች ውስጥ መመልከት ያለባቸው ሲሆን፣ በሁሉም ተጫራቾች ላይ በእኩልነት ተፈፃሚ መሆን አለባቸው፡፡

b) that they have the legal capacity to enter into the contract;

c) that they are not insolvent, in receivership, bankrupt or being wound up, their business activities have not been suspended, and they are not the subject of legal proceedings for any of the foregoing;

d) subject to the directives to be issued by the Bureau, that they are registered in the suppliers list;

e) that the period for which they were suspended from participating in public procurement is over;

f) that they have renewed trade license and fulfilled his tax obligations in accordance with the federal and the region tax laws;

g) that they have a bank account.

2. The public body may require candidates to provide such appropriate documentary evidence or other information as it may deem useful to satisfy itself that the candidates are qualified in accordance with the criteria referred to in sub-article (1) of this Article.

3. Any requirement established pursuant to this Article shall be set forth in the bid documents or other documents for solicitation of proposals, and shall apply equally to all candidates.

፬ የመንግሥት መስሪያ ቤቱ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ ፫ መሠረት የሚቀርቡትን ሰነዶች እና የመመዘኛ መስፈርቶችን መሠረት በማድረግ የዕጩ ተወዳዳሪዎችን ብቃት መገምገም አለበት፡፡

፭ የመንግሥት መስሪያ ቤቱ ብቃት ያላቸው መሆኑን ለማስረዳት ሀሰተኛ መረጃ የያዙ ሰነዶችን ያቀረቡ ዕጩ ተወዳዳሪዎች ወይም ብቃታቸውን ለማረጋገጥ ያቀረቡት መረጃ መሠረታዊ ስህተት ያለበት ወይም ያልተሟላ መሆኑ በማናቸውም ጊዜ የተረጋገጠ ዕጩ ተወዳዳሪዎች ከጨረታ ውጪ እንዲሆኑ ያደርጋል፡፡

## ፳፱ የቴክኒክ ፍላጎት መግለጫ

፩ ስለግዢው ምንነት ትክክለኛና የተሟላ መግለጫ እንዲኖር እንዲሁም ዕጩ ተወዳዳሪዎች ፍትሀዊና ግልጽ በሆነ ሁኔታ መወዳደር የሚችሉበትን ሁኔታ ለማመቻቸት ግዢ ፈፃሚ አካላት የሚገዙዋቸውን ዕቃዎች፣ የግንባታ ሥራዎች ወይም አገልግሎቶች ባህርይ የሚያሣይ የቴክኒክ ፍላጎት መግለጫ ማዘጋጀት አለባቸው፡፡

፪ የቴክኒክ ፍላጎት መግለጫው የመንግሥት መስሪያ ቤቱ ሊገዛ የሚፈልገውን ዕቃ ጥራት፣ ጠቀሜታ፣ ተገቢ ጥንቃቄ፣ እንደአስፈላጊነቱ መለኪያውን፣ መለያውን፣ መጠሪያውን፣ አስተሻሸጉን፣ ምልክቱን ወይም የአመራረቱን ሂደት፣ ዘዴ እና ተፈላጊ የሆነውን ባህሪይ የሚያሟላ መሆኑ የሚረጋገጥበትን ሥርዓት የሚገልጽ መሆን አለበት፡፡

4. The public body shall evaluate the qualifications of candidates in accordance with the criteria and procedures set forth in the documents referred to in sub-article (3) of this Article.
5. The public body shall disqualify a candidate who submits a document containing false information for purposes of qualification;or it shall disqualify a candidate if it finds at any time that the information submitted concerning the qualifications of the candidate was materially inaccurate or incomplete.

## 29. Technical Specification

1. Technical specifications and descriptions laying down the characteristics of the goods,construction works or services to be procured shall be prepared for the purpose of providing a correct and complete description of the object of procurement and for the purpose of creating conditions of fair and open competition between all candidates.

2. The technical specifications shall clearly describe the public body’s requirements with respect to quality, performance, safety and where necessary dimensions, symbols, brand , packaging, marking and labeling or the processes and methods of production and requirements relating to conformity assessment procedures.

፫ በመንግሥት መስሪያ ቤቱ የሚዘጋጀው የቴክኒክ ፍላጎት መግለጫ እስከተቻለ ድረስ፡-

ሀ. በዲዛይን ወይም ባሕሪያትን በመዘርዘር ላይ ሳይሆን በጠቀሜታ ላይ፤

ለ. አገራዊ ደረጃ የወጣለት ሲሆን ደረጃውን ወይም ዓለም ዓቀፍ ተቀባይነት ያላቸውን ደረጃዎች ወይም የግንባታ ኮዶች መሠረት ያደረገ፤

ሐ. ሰፊ ውድድርን የሚጋብዝ እና ውድድርን ሊገድቡ የሚችሉ መግለጫዎች ያልተካተቱበት መሆን አለበት፡፡

፬ የመንግሥት መስሪያ ቤቱን ፍላጎት በትክክል ለመግለጽ አስቸጋሪ ካልሆነ ወይም ሌላ ዘዴ ካልታጣ በስተቀር የቴክኒክ መግለጫ የተለየ የንግድ ምልክት ወይም ስም፣ ፓተንት፣ ዲዛይን ወይም የተወሰነን አምራች ወይም አገልግሎት ሰጪ የሚጠቅስ መሆን የለበትም፡፡ አስገዳጅ ሁኔታ በሚያጋጥምበት ጊዜ «ወይም ተመሳሳዩን» የሚል ሐረግ በዕቃና አገልግሎት ዝርዝሩ ውስጥ መታከል ይኖርበታል፡፡

3/ Technical specification prescribed by public bodies shall, as far as possible:

a) be in terms of performance rather than design or descriptive characteristics;

b) be based on national standards, where such standard exist, or otherwise on internationally recognized standards or building codes;

c) inviting open competition and devoid of any statement having the effect of restricting competition.

4/ There shall be no requirement or reference in the technical specifications to a particular trademark or name, patent, design or type, specific original producer or service provider, unless there is no sufficiently precise or intelligible way of describing the procurement requirements of the public body and provided that words such as “or similar” are included in the specifications.

## ፴ ጨረታን፣ የመወዳደሪያ ሀሣብን እና ማስታወቂያ በመለጠፍ የሚፈፀም ግዢ ውድቅ ስለማድረግ

፩ የመንግሥት መስሪያ ቤቶች ከሚከተሉት በአንዱ ወይም ከአንድ በላይ በሆኑ ምክንያቶች ጨረታን፣ የመወዳደሪያ ሀሣብን እና ማስታወቂያ በመለጠፍ የሚፈፀም ግዥን ስምምነት ከመደረጉ በፊት በማናቸውም ጊዜ ሙሉ በሙሉ ወይም በከፊል ውድቅ ማድረግ ይችላሉ:-

ሀ. በግዢ አካሄዱ ላይ ውጤቱን ሊያዛባ የሚችል ስህተት መፈፀሙ ከተረጋገጠ፤

ለ. በስራ ዕቅድ መቀየር ምክንያት ወይም የመሥሪያ ቤቱን ፍላጎት ለማሟላት ሌላ የተሻለ አማራጭ በመፈጠሩ ምክንያት ግዢውን ማካሄድ ለመንግሥት መሥሪያ ቤቱ የተሻለ ቴክኒካል ወይንም ኢኮኖሚያዊ ጥቅም የሌለው መሆኑ ሲረጋገጥ፤

ሐ. የቀረቡት ተጫራቾች በጨረታ ሰነዱ ላይ የተቀመጠውን ዝቅተኛ መስፈርት የማያሟሉ ሲሆን፤

መ. በጨረታ የቀረበ ዝቅተኛ ዋጋ በወቅቱ ካለው የገበያ ዋጋ የተጋነነ ልዩነት ሲኖረው እና የመንግሥት መሥሪያ ቤቱ ድጋሚ ጨረታ በማውጣት የተሻለ ዋጋ የሚገኝ መሆኑ ሲገመት፤

ሠ. በጨረታ አሸናፊ የሆነው ተጫራች የሰጠው ዋጋ የግዥ ፈጻሚ መስሪያ ቤቱ ለግዢው ከያዘው በጀት በላይ ሲሆን እና ባለበጀት መስሪያ ቤቱ የበጀቱን ልዩነት ከሌላ ምንጭ ማሟላት የማይችል ሲሆን፤

## 30. Rejection of Bids, Proposals and Quotations

1) Public bodies may ,for one or more of the following reasons, reject in whole or in part bids, proposals or quotations at any time prior to the conclusion of procurement contract where:

a) there is proof of error in the procurement proceeding which could affect the outcome of the bid;

b) it is ascertained that the procurement has no use in enabling the public body to obtain a better technical or economic advantage as a result of a change of work plan or another alternative representing a better option to meet the requirement of the public body;

c) bidders fail to meet the minimum criteria set forth in the bid document;

d) the minimum price offered in the bid does not match with the market price circulated and the public body expected that it can get a better price advantage by re-advertising the bid;

e) the price offered by the successful bidder exceeds the budgetary allocation made for the procurement and the public body cannot make up for the deficiency from any other source;

ረ ዕጩ ተወዳዳሪዎች የግዥ አካሄዱን ለማዛባት በመመሳጠራቸው በቂ ውድድር አለመደረጉ ሲረጋገጥ፡፡

፪ የመንግሥት መስሪያ ቤቶች ከዚህ በላይ በተመለከተው መሠረት ጨረታን፣ የመወዳደሪያ ሀሣብን፣ ማስታወቂያ በመለጠፍ የሚፈፀም ግዥ ሙሉ በሙሉ ወይም በከፊል ሲሠርዙ ምክንያቱን የሚገልጽ ማስታወቂያ ለዕጩ ተወዳዳሪዎ-ች ወዲያውኑ እንዲደርስ ማድረግ አለባቸው፡፡ ኖም የምክንያቶቹን አግባብነት እንዲያስረዱ አይገደዱም፡፡

፫ ጨረታውን ውድቅ የማድረጉ ውሣኔ የተሰጠው ጨረታው ከመከፈቱ በፊት ከሆነ የመጫረቻ ሰነዶቹ ሳይከፈቱ ለዕጩ ተወዳዳሪዎች መመለስ አለባቸው፡፡

፬ የመንግሥት መስሪያ ቤቶች ከዚህ በላይ በንዑስ አንቀጽ ፩ በተመለከተው መሠረት ጨረታን ፣የመወዳደሪያ ሀሣብን፣ ማስታወቂያ በመለጠፍ የሚፈፀም ግዥ ውድቅ በማድረጋቸው ምክንያት ምንም ዓይነት ተጠያቂነት አይኖርባቸውም፡፡

## ፴፩ የኤሌክትሮኒክስ ግዥ

ቢሮው ግዢው ወጪ ቆጣቢ፣ ግልፅ እና ዘመናዊ እንዲሆን ለማድረግ ሂደቱ በኤሌክትሮኒክስ ዘዴ እንዲፈጸም ሊያደርግ ይችላል፡፡ ይህንን ሥራ ላይ ማዋል እንዲቻል:-

f) it is proved that the bidding is not sufficiently competitive as a result of connivance among candidates.

2) Public bodies shall have to give notice to candidates forth with disclosing the reasons for rejecting bids, proposals or quotations wholly or partially in accordance with sub article (1) of this Article. However, they shall not be dictated to justify the reasons.

3) If the decision to reject the bid results before the opening the bid , the bids received shall be returned unopened to the candidates submitting them.

4) The public bodies shall incur no liability towards candidates solely by virtue of its invoking sub-article (1) of this Article.

## 31. Electronic Procurement

To achieve economc, transparent and modernized public procurement, the bureau may authorize the use of electronic means as a method of procurement. In order to implement this:

ሀ. ኤጀንሲው ክልሉ ከሚገኝበት የዕድገት ደረጃ ተመጣጣኝ የሆነ ግዥን በኤሌክትሮኒክስ የመረጃ ልውውጥ ዘዴ የመፈፀም አሠራርን ከሚመለከተው አካል ጋር ጥናት በማድረግ ያቀርባል፤

ለ. ኤጀንሲው በመንግሥት መስሪያ ቤቶች፣ አቅራቢዎች እና በተቆጣጣሪ አካሎች አሰራሩን ለመተግበር የሚያስችል አቅም መፈጠሩን ያረጋግጣል፤

ሐ. ቢሮው የቀረበውን በኤሌክትሮኒክስ የመረጃ ልውውጥ ዘዴ ግዢን የመፈፀም አሰራር በመመርመር እና አጠቃላይ የመንግሥት መስሪያ ቤቶች እና የአቅራቢዎች አሰራር እና አቅም ግዢን በኤሌክትሮኒክስ የመረጃ ልውውጥ ለመፈፀም ዝግጁ ነው ብሎ ሲያምን ተገቢውን የአሠራር ሥርዓት በመዘርጋት ሥርዓቱ በተወሰኑ ወይም በሁሉም የመንግስት ግዥዎች ላይ ተግባራዊ እንዲሆን ሊያደርግ ይችላል፡፡

## ፴፪ <u>የመንግሥት ግዥ እና ንብረት አስተዳደር ሥነ-ምግባር</u>

ዝርዝር አፈጻፀማቸው ቢሮው በሚያወጣው መመሪያ የሚገለፅ ሆኖ በግዥና ንብረት አስተዳደር ሥራ ላይ የተሠማሩ ሠራተኞች የሚከተሉትን የሥነ-ምግባር መርሆዎች ተከትለው ተግባራቸውን ያከናውናሉ፡-

a) the Agency shall conduct a study and submit proposal on a system of conducting procurement by means of electronic exchange of information which is appropriate to the level of development of the country;

b) the Agency shall ensure that public bodies, suppliers and supervising entities develop the capacity required to implement the system;

c) upon due consideration of the proposed system of effecting procurement by means of electronic exchange of information and where he is satisfied that the overall system and capacity of public bodies and suppliers allows the carrying out of procurement through electronic exchange of information, the Bureau may authorize the implementation of the electronic system in all or certain public procurement proceedings by establishing the appropriate framework for the operation of the proposed electronic system.

## 32. **<u>Rules of Ethics in Public Procurement and Property Administration</u>**

Subject to the details to be specified in the directive to be issued by the Bureau, personnel engaged in public procurement or property administration shall be guided with the following rules of ethics in the discharge of their duties:

ሀ. የተፈጠረ ወይንም ሊፈጠር የሚችል የጥቅም ግጭት የማሳወቅ እና ራስን ከሂደቱ የማግለል፤

ለ. ለዕጩ ተወዳዳሪዎች እና አቅራቢዎች እኩል የመወዳደር እና የመፈፀም እድል የመስጠት፤

ሐ. በሥራ አጋጣሚ ያወቃቸውን የመንግሥት መስሪያ ቤቱን እና የእጩ ተወዳዳሪዎችን ወይም የአቅራቢዎችን መረጃ በሚስጥር መጠበቅ፤

መ. ስጦታ ወይም የሥራ ዕድል ወይም የገንዘብ ዋጋ ያለውን ነገር ወይም አገልግሎት አለመቀበል፤

ሠ. በሥራ ሂደት ያወቃቸውን ሊፈጠሩ የታሰቡ ወይንም የተፈጠሩ የሙስና ተግባራትን ለህግ አስፈጻሚ አካላት የማሳወቅ እና ሙስናን እና ብልሹ አሰራርን ለመዋጋት የሚደረገውን ጥረት የማገዝ፤

ረ ለህዝብ ሀብትና ንብረት ተቆርቋሪ መሆን::

፪ ማንኛውም ዕጩ ተወዳዳሪ ወይም አቅራቢ የመንግሥት የግዥ አፈጻፀም እና ንብረት አወጋገድን ሊያዛባ ከሚችል ከማንኛውም ተግባር ራሱን ማግለል አለበት፣ በዚህ አዋጅ ምዕራፍ አሥራ አምስት የተመለከተው እንደተጠበቀ ሆኖ፡-

ሀ. የመንግሥት መስሪያ ቤቱን ኃላፊ ወይም ሠራተኛ ተግባር ወይም ውሣኔ ለማዛባት ወይም ከግዥው አፈጻፀም እና ንብረት አወጋገዱ ጋር በተያያዘ መስሪያ ቤቱ ሊከተለው የሚገባውን አሠራር ለማስለወጥ በመደለያ መልክ በቀጥታ ወይም በተዘዋዋሪ መንገድ ማናቸውንም ዓይነት ስጦታ አለመስጠት ወይም ስጦታ ለመስጠት ቃል አለመግባት ወይም የሥራ ዕድል ወይም ሌላ ማናቸውንም የገንዘብ ዋጋ ያለውን ነገር ወይም አገልግሎት አለመስጠት፤

a) the obligations to notify any actual or possible conflict of interest and isolate oneself from any processes involving such conflict;

b) to give candidates and suppliers equal opportunity of competition and performance;

c) keep in secret any confidential information concerning the public body, candidate or supplier which he/she came to know on account of his/her duty;

d) to reject any gift or offer of an employment opportunity or anything of monetary value or service;

e) to report to the law enforcement agencies any intended or completed action of corruption and contribute to the effort to fight corruption and malpractice;

f) demonstrate concern to public resource and property.

2) Any candidate or supplier shall have to refrain from any act contravening the process of public procurement and property disposal. Without prejudice to the provisions of Chapter Fifteen of this Proclamation, any candidate or supplier shall have the responsibility:

a) with an intention to influence the decision or action of the head or staff member of the public body or persuade the public body to change its established practice of procurement and property disposal, not to give directly or indirectly gifts of any kind in the form of inducement, not to promise to give gifts, not to offer employment opportunity or anything of monetary value or service;

ለ. የመንግሥት ግዢ አፈጻፀም ወይንም ንብረት አወጋገድ ለማዛባት በማሰብ የሐሰት ማስረጃ አለማቅረብ ወይንም መግለፅ የነበረበትን መረጃ አለመደበቅ፤

ሐ. ተገቢ ያልሆነ ጥቅም ለማግኘት በማሰብ ከሌላ ዕጩ ተወዳዳሪ ጋር በመመሳጠር የሐሰት ውድድር አለማድረግ፤

መ. በሥራ ሂደት ያወቃቸውን ሊፈጠሩ የታሰቡ ወይንም የተፈጠሩ የሙስና ተግባራትን ለሕግ አስፈጻሚ አካላት የማሳወቅ እና ሙስናን እና ብልሹ አሰራርን ለመዋጋት የሚደረገውን ጥረት የማገዝ ኃላፊነት አለበት፡፡

## ፴፫ የግዥ ዘዴዎች

፩ በመንግሥት ግዢ አፈጻፀም የሚከተሉት የግዢ ዘዴዎች ስራ ላይ ይውላሉ፡-

ሀ. ግልጽ ጨረታ፣

ለ. በመወዳደሪያ ሃሣብ መጠየቂያ የሚፈፀም ግዢ፣

ሐ. በሁለት ደረጃ ጨረታ የሚፈፀም ግዥ፣

መ. ውስን ጨረታ፣

ሠ. ማስታወቂያ በአከባቢ በመለጠፍ የሚፈጸም ግዢ፣

ረ. ከአንድ አቅራቢ የሚፈፀም ግዥ፡፡

፪ በዚህ አዋጅ በተፈቀደው ሁኔታ ካልሆነ በስተቀር የመንግሥት መሥሪያ ቤቶች ማናቸውንም ግዢ በግልፅ የጨረታ ዘዴ መፈፀም አለባቸው፡፡

b) with an intention to mislead a procurement proceeding not to present a falsified document or not to withhold information he/she should have disclosed;

c) not to connive with another candidate in an act of false competition in order to get unfair advantages;

d) to report to the law enforcement agencies any intended or completed action of corruption which he came to know during the procurement proceedings and contribute to the effort to fight corruption and malpractice.

## 33. Methods of Procurement

1) The following methods shall be used in public procurement:

a) Open Bidding;

b) Request for Proposals;

c) Two stage Tendering;

d) Restricted Tendering;

e) Request for Quotation;

f) Direct Procurement.

2) Except as otherwise provided in this Proclamation, public bodies shall use open bidding as the preferred procedure of procurement.

፫ የመንግሥት መስሪያ ቤቶች ከግልጽ ጨረታ ውጪ በሌሎች የግዥ ዘዴዎች ግዥ መፈፀም የሚችሉት በዚህ አዋጅ የተገለጹት ሁኔታዎች ከተሟሉ ብቻ ይሆናል፡፡

፬ በዚህ አዋጅ ወይም በግዥ መመሪያው የተዘረጉ የግዥ ሥርዓቶችን ለመሸሽ ግዥ ፈፃሚ የመንግሥት መስሪያ ቤቶች በአንድነት ሊፈፀሙ የሚገባቸውን የዕቃ፣ የግንባታ ወይም የአገልግሎት ግዢዎች መከፋፈል የለባቸውም፡፡

## ፴፬ <u>የመንግስትና የግል ሽርክና</u>

ቢሮው የመንግስትና የግል ሽርክና የሚመሠረትበትን ሁኔታ እና የሽርክናውን ዝርዝር አፈጻጸም የሚወስን መመሪያ ያወጣል፡፡

## ምዕራፍ አራት

## <u>የግልፅ ጨረታ አፈጻፀም</u>

## ፴፭ <u>የጨረታ ማስታወቂያ</u>

፩ የጨረታ ማስታወቂያ የጨረታ ሰነዱ በተዘጋጀበት ቋንቋ በሚታተም እና አገራዊ ሽፋን ባለው ጋዜጣ ቢያንስ አንድ ጊዜ መውጣት አለበት፡፡

፪ የመንግሥት መስሪያ ቤቱ አስፈላጊ ሆኖ ሲያገኘው የጨረታ ማስታወቂያው በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ ፩ ከተጠቀሰው በተጨማሪ በብሔራዊ ሬድዮ፣ በቴሌቪዥን፣ በድህረ ገጽ ወይም በሌላ አገራዊ ሽፋን ባለው መገናኛ ብዙሃን ሊያስነግር ይችላል፡፡

3) Public bodies may use a method other than open bidding only where conditions for the use of such other method stipulated under this Proclamation are satisfied;

4) Public bodies shall not split procurement requirements for a given quantity of goods, works or services with the intention of avoiding the preferred procurement procedure stated under this Proclamation or in the procurement-directive.

## 34.<u>Public Private Partnership</u>

The Bureau may issue directive prescribing the rules governing the formation of Public Private Partnership and the modes of implementation of such partnership.

## CHAPTER FOUR

## <u>PROCEDURE OF OPEN BIDDING</u>

## 35.<u>Advertisements</u>

1) Invitation to bid shall be advertised in at least one times in a national news paper of general circulation which is published in the language the bidding document is prepared.

2) Where the public body finds it necessary, it may, in addition to the medium mentioned in sub article (1) of this Article, advertise the bid on a national radio , television,Website or any other mass medium having national circulation.

፫ ለዕጩ ተወዳዳሪዎች ለጨረታ ማቅረቢያ የሚሰጠው ጊዜ በግዥ መመሪያ ከሚወሰነው አነስተኛ የቀን ብዛት ያነሰ መሆን የለበትም፡፡

## ፴፮ <u>የጨረታ ጥሪ</u>

የጨረታ ጥሪ ከሚከተሉት በተጨማሪ በኤጀንሲው የሚወጣውን መደበኛ የጨረታ ሰነድ መሠረት በማድረግ መዘጋጀት አለበት፡-

ሀ. የግዢ ፈፃሚውን አካል ስምና አድራሻ፤

ለ. የዕቃውን፣ የግንባታ ሥራውን እና የአገልግሎቱን አጭር መግለጫ፤

ሐ. የጨረታውን ሰነድ ለማግኘት መሟላት ያለባቸውን ቅድመ-ሁኔታዎች እና የጨረታ ሠነዱ የሚገኝበትን ቦታ፤

መ. የጨረታ መወዳደሪያ ሀሣብ የሚቀርብበትን ቦታ እና የማቅረቢያውን የመጨረሻ ጊዜ፤

ሠ. ጨረታው የሚከፈትበት ቦታ እና ጊዜ እንዲሁም ተጫራቾች ወይም ተወካዮች ጨረታው ሲከፈት መገኘት የሚችሉ መሆኑን የሚገልጽ ማሳሰቢያ፡፡

## ፴፯ <u>የጨረታ ሠነድ</u>

በተጫራቾች መካከል የሚደረገው ውድድር በተሟላ፣ ገለልተኛና ተጨባጭ መሠረት ባለው ሁኔታ እንዲካሄድ ለማድረግ የጨረታው ሰነድ በኤጀንሲው የተዘጋጀውን መደበኛ የጨረታ ሰነድ መሰረት በማድረግ በቂ መረጃ በያዘ መልኩ የተዘጋጀ መሆን አለበት፡፡ በተለይም ሰነዱ የሚከተሉትን ሊያካትት ይገባል፡-

3) The time allowed for preparation of bids shall not be less than the minimum number of days stated in the procurement directives.

## 36. <u>Invitation to Bid</u>

Apart from containing the following particulars, the invitation to bid shall be prepared in accordance with the standard bidding document to be developed by the Agency:

a) the name and address of the public body;

b) a brief description of the goods, works or services to be procured;

c) the means and conditions for obtaining the bidding documents and the place from which they may be obtained;

d) the place and deadline for the submission of bids;

e) the place and time for opening of bids, along with an announcement that bidders or their representatives are allowed to attend at the opening of bids.

## 37. <u>Bidding Documents</u>

The bidding documents shall be ppepared based on the standard bidding document stipulated by the agency and contain sufficient information to enable competition among the bidders to take place on the basis of complete, neutral and objective terms. In particular, bidding documents shall include:

ሀ. የመጫረቻ ሰነድ ለማዘጋጀትና ለማቅረብ አስፈላጊ የሆኑ መመሪያዎችን፤

ለ. የመጫረቻ ሠነዱን ማስረከቢያ የመጨረሻ ቀን፣ የመጫረቻ ሰነዱ የሚላክበትን አድራሻ፣ የጨረታው ሰነድ የሚከፈትበትን ቀን፣ ሰዓት እና ቦታ፣ እንዲሁም የተጫራቾች ወኪሎች በጨረታው መክፈቻ ሥነ-ሥርዓት ላይ ሊገኙ የሚችሉ መሆኑን የሚገልጽ መረጃ፤

ሐ. የጨረታ መወዳደሪያ ሀሣብ ማቅረቢያ ቅጾች፣ እንዲሁም አግባብነት እስካለው ድረስ የጨረታ ማስከበሪያ ቅጾች፤

መ. ከዋናው የመጫረቻ ሰነድ ጋር መቅረብ ያለባቸውን ተጨማሪ ኮፒዎች፤

ሠ. የውሉን አጠቃላይ እና ልዩ ሁኔታ፤

ረ. እንደአግባብነቱ ዕቃውን ለማቅረብ ወይም ሥራውን ለማጠናቀቅ ይወስዳል ተብሎ የሚገመተውን የጊዜ ገደብ ጨምሮ ተፈላጊውን የዕቃና አገልግሎት ዝርዝር፤

ሰ. ተጫራቹ በጨረታው ለመሳተፍ ብቃት ያለው መሆኑን ለማረጋገጥ የሚያቀርባቸውን መረጃዎች ዓይነት እንዲሁም የፋይናንስ አቋሙንና ሕጋዊነቱን ለማረጋገጥ ማቅረብ ያለበትን መረጃ፤

ሸ. ጨረታው ፀንቶ የሚቆይበትን ጊዜ፤

ቀ. ጨረታውን ለመገምገም እና በጨረታው አሸናፊ የሆነውን ለማስታወቅ የሚያገለግሉ መስፈርቶችን እና ለእያንዳንዱ መስፈርት የተሰጠውን ነጥብ፤

a) instructions for the preparation and submission of bids;

b) information about the final date for receipt of bids, the address to which bids must be sent, the date, hour and place of opening, as well as an announcement that bidders and information that may allow their representatives to attend the opening ceremony;

c) bid submission forms and, where applicable, forms of bid security to be provided;

d) the number of copies to be submitted with the original bid;

e) the general and specific conditions of the contract;

f) specification of requirements, including time limit for delivery or completion of the task, as appropriate;

g) evidence to be provided by the bidder to demonstrate its qualifications as well as its fiscal and legal standing;

h) the period during which the bid remains in force;

(i) the criteria and the points given to each criterion for evaluation of bids and award of the contract;

በ. ግዢውን የሚፈጽመው የመንግሥት መስሪያ ቤት የጨረታው አሸናፊ ይፋ ከመደረጉ በፊት በማናቸውም ጊዜ ጨረታውን ሙሉ በሙሉ ወይም በከፊል የመሠረዝ መብት ያለው መሆኑን፤

ተ. ቢሮው በሚያወጣው መመሪያ በልዩ ሁኔታ ለተፈቀዱ ግዢዎች በውል አፈጻፀም ወቅት የዋጋ ማስተካከያ ሊደረግ የሚችል ስለመሆኑ እና የዋጋ ማስተካከያው የሚደረግበትን ሁኔታ እና አፈጻፀሙን፡፡

## ፴፰ የጨረታ ሰነድ ሽያጭ

፩ የጨረታ ሰነድ የመሸጫ ዋጋ ለጨረታው ሰነድ ዝግጅት እና ሠነዱን ለዕጩ ተወዳዳሪዎች ለማቅረብ ከወጣው ወጪ ባልበለጠ መተመን ይኖርበታል፡፡

፪ የጨረታ ሰነዱ ጨረታው ከወጣበት ጊዜ ጀምሮ ጨረታው እስከሚዘጋበት ጊዜ ድርስ ባሉት የሥራ ቀናት እና በጨረታ ማስታወቂያው በተገለጸው አኳኋን ለዕጩ ተወዳዳሪዎች እንዲደርስ መደረግ አለበት፡፡

፫ የመንግሥት መሥሪያ ቤቱ አግባብ ሆኖ ሲያገኘው የጨረታ ሰነዱ በነፃ እንዲሰጥ ሊፈቅድ ይችላል፡፡

## ፴፱ በጨረታ ሰነድ ላይ ስለሚደረግ ማሻሻያ

፩ የመንግሥት መሥሪያ ቤቶች በራሳቸው ወይም የጨረታ ሰነድ ከገዙ ዕጩ ተወዳዳሪዎች በሚቀርቡ ጥያቄዎች መነሻ የመጫረቻ ሰነድ ማቅረቢያ ጊዜ ገደብ ከማለፉ በፊት የጨረታ ሰነዶችን ይዘት ለማሻሻል ይችላሉ፡፡

(j) a reservation to the effect that the public body may reject the bids wholly or partly at any time prior to the notification of award; and

(k) the price adjustments that may be made during contract implementation and the conditions and the manner under which such price adjustments can be made to special procurements prescribed by the directive to be issued by the Bureau.

## 38. Provision of Bidding Documents

1) Bid documents shall be made available to candidates at a price not exceeding the cost of reproduction and delivery of such documents to candidates.

2) The bidding document shall be delivered to candidates on working days between the date of publication of the invitation to bid and the closing date of the bid and in the manner specified in the invitation to bid.

3) Where it deems to be appropriate, the public body may make the bidding document to be available to candidates free of charge.

## 39. Modifications to Bidding Documents

1) At any time prior to the deadline for submission of bids, the public body may, on its own initiative or in response to an inquiry by a candidate having purchased the contents bidding documents, modify the bidding documents

፪ የተደረገው ማሻሻያ በጽሑፍ ተዘጋጅቶ የጨረታ ሰነዶችን ለገዙ ዕጩ ተወዳዳሪ-ዎች ሁሉ በተመሳሳይ ጊዜ መላክ አለበት፡፡

፫ የመንግሥት መሥሪያ ቤቱ የጨረታ ሰነዱን ይዘት ማሻሻል አስፈላጊ ሆኖ ያገኘው እና በማሻሻያው የተመለከቱ ማስተካከያዎችን ለማድረግ በቂ ጊዜ የሌለ መሆኑን የተረዳ እንደሆነ ዕጩ ተወዳዳሪዎች ማሻሻያውን መሠረት አድርገው የጨረታ ሰነዱን ለማዘጋጀት በቂ ጊዜ እንዲኖራቸው ለማድረግ የግዥውን ባሕርይ መሠረት በማድረግ የጨረታውን ማቅረቢያ ጊዜ ለተወሰኑ ቀናት ሊያራዝም ይችላል፡፡

## ፵ የጨረታ ማስከበሪያ

፩ የመንግሥት መሥሪያ ቤቶች በሚያዘጋጁት የጨረታ ሰነድ ተጫራቾች ከመጫረቻ ሰነዶቻቸው ጋር የጨረታ ማስከበሪያ የማቅረብ ግዴታ እንዳለባቸው መግለፅ አለባቸው፡፡ የጨረታ ማስከበሪያው መጠን በጨረታው ኃላፊነት በተሞላው ሁኔታ የማይሳተፉትን ለማስቀረት የሚያስችል መሆን አለበት፡፡

፪ በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀጽ ፩ የተገለፀው ቢኖርም የጨረታ ማስከበሪያ ማስያዝ የሚያስፈልግባቸው የግዢ አይነቶች እና የጨረታ ማስከበሪያው መጠን ቢሮው በሚያወጣው መመሪያ ይወሰናል፡፡

2) Any modification shall be communicated promptly to all candidates having purchased the bid documents at the same time.

3) If the public body considers it necessary to modify the bidding documents and if it determines that there is no enough time to incorporate the modification, it may postpone the closing date by a number of days, depending on the procurement object, which is sufficient to enable the bidders to take the addendum into account in preparing their bids.

## 40. Bid Security

1) Public bodies shall include in the bidding documents a condition that bids must be accompanied by a bid security. The amount of such bid security shall be sufficient to discourage irresponsible bidders.

2) Notwithstanding the provision of sub-article (1) of this Article, procurement in respect of which bid security is required and the amount of bid security thereof, is to be prescribed by the directive to be issued by the Bureau.

፫ የጨረታ ማስከበሪያው ፀንቶ በሚቆይበት ጊዜ ውስጥ ተጫራቹ ራሱን ከውድድሩ ካገለለ ወይም አሸናፊውን ተጫራች በሚመለከት አሸናፊነቱ ከተገለፀለት በኂላ ውሉን ለመፈረም ፈቃደኛ ሆኖ ካልተገኘ ወይም እንዲያቀርብ የተጠየቀውን የውል ማስከበሪያ ካላቀረበ የጨረታ ማስከበሪያው ውርስ ይደረጋል፡፡

3/ A bid security will be forfeited if a bidder withdraws his bid within the validity period thereof or in the case of a successful bidder, if the bidder repudiates the contract or fails to furnish performance security, if so required.

## ፵፩. <u>የመጫረቻ ሰነድ ስለማቅረብና ስለመቀበል</u>

## 41.<u>Submission and Receipt of Bids</u>

፩ የመጫረቻ ሰነድ በጽሑፍ ተዘጋጅቶና ተፈርሞበት በታሸገ ኤንቨሎፕ ውስጥ ሆኖ በጨረታ ማስታወቂያው ከተመለከተው የጊዜ ገደብ በፊት በተገለጸው ቦታ ገቢ መደረግ አለበት፡፡

1/ Bids shall be submitted in writing, signed and in a sealed envelope, to the place and before the deadline stated in the invitation to bid.

፪ የመጫረቻ ሰነዱ ትልቅ በመሆኑ በጨረታ ሳጥን ውስጥ ሊቀመጥ የማይችል ከሆነ የመጫረቻ ሰነዱን በመንግሥት መሥሪያ ቤቱ የግዥ ተግባርን የሚያከናውነው ሥራ ሂደት ተረክቦ ገቢ የተደረገበትን ቀንና ሰዓት የሚያሳይ ማረጋገጫ ለእጩ ተወዳዳሪው መስጠት አለበት፡፡

2/ work process responsible to carry out procurement shall give a receipt to the bidder indicating the time and date on which the bid document was submitted, where it becomes impossible to put the bid document in a bid box due to its large size.

፫ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ ፪ የተገለጸው እንደተጠበቀ ሆኖ የመጫረቻ ሰነዱን ለማቅረቢያ ከተወሰነው ጊዜ በኂላ የቀረበ ሰነድ ተቀባይነት አይኖረውም፡፡

3/ Without prejudice to the provisions of sub-article (2) of this Article, a bid document recieved after the deadline for submission shall be unacceptable .

## ፵፪ ጨረታን ስለመክፈት

፩ የመንግሥት መሥሪያ ቤቱ በጨረታ ሰነዱ የተመለከተው የመጫረቻ ሰነድ ማቅረቢያ የተወሰነው የጊዜ ገደብ እንደተጠናቀቀ ወዲያውኑ የመጫረቻ ሰነድ ከማቅረቢያ የጊዜ ገደብ በፊት የቀረቡ የመጫረቻ ሰነዶችን መክፈት አለበት።

፪ የተጫራቹ ስም እና በእያንዳንዱ የመጫረቻ ሰነድ የቀረበው የመጫረቻ ዋጋ፣ የተሰጠ ቅናሽ እና የመንግሥት መሥሪያ ቤቱ እንደ ግዢው ሁኔታ ተጫራቾች አንፃራዊ ደረጃቸውን ለማወቅ ይረዳቸዋል ብሎ የሚያምንባቸውን ሌሎች መረጃዎች ከፍ ባለ ድምፅ መነበብ እና መመዝገብ እንዲሁም ተጫራቾች በጠየቁ ጊዜ የተመዘገበውን ዝርዝር እንዲያገኙ መደረግ አለበት።

፫ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ ፪ የተደነገገው ቢኖርም የቴክኒክና የፋይናንስ መወዳደሪያ ሀሳብ በሁለት ፖስታ የቀረበ በሚሆንበት ጊዜ የመጫረቻ ዋጋው የሚነበበው የቴክኒክ ግምገማው ከተጠናቀቀ በኋላ ይሆናል።

## ፵፫ የመጫረቻ ሰነዶችን ስለመመርመር እና ስለመገምገም

፩ ጨረታውን ለመመርመርና ግምገማውን ለማከናወን የሚረዳ ሆኖ ሲገኝ፣ የመንግሥት መሥሪያ ቤቱ ተጫራቾች ባቀረቡት የመጫረቻ ሰነድ ላይ ማብራሪያ እንዲሰጡ ሊጠይቅ ይችላል። ሆኖም የዋጋ ለውጥን ጨምሮ የመጫረቻ ሰነዱ ላይ መሠረታዊ ለውጥ የሚያስከትል ሀሣብ ማቅረብ ወይም መፍቀድ አይቻልም።

## 42. Opening of Bids

1/ At the time stipulated in the bidding document for opening of bids, which should follow immediately after the deadline for submission of bids, the public body shall open all bids received before the deadline.

2/ The name of the bidder and the total amount of each bid, discounts offered and any such information as the public body deems necessary to let the bidders know their relative rank shall be read out aloud and recorded and a copy of the record shall be made available to any bidder on request.

3/. Notwithstanding the provisions of sub – article (2) of this Article, the envelope containing the price offered by the bidder shall be read after the evaluation of the technical proposal where technical and financial proposals are submitted in two separate envelops.

## 43. Examination and Evaluation of Bids

1) The public body may request bidders for clarification of their bids in order to assist the examination and evaluation of bids; however, no change in the substance of the bid, including changes in price, shall be offered or permitted.

፪ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ ፩ የተመለከተው እንደተጠበቀ ሆኖ የመንግሥት መሥሪያ ቤቱ በጨረታ ምርመራው ወቅት የተገኙ የሂሣብ ስህተቶችን ለማረም ይችላል፡፡ ግዥ ፈፃሚው አካል እነዚህን ማስተካከያዎች የመጫረቻ ሰነዱን ላቀረበው ተጫራች በአፋጣኝ መግለጽ አለበት፡፡

፫ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ ፬ የተመለከተው እንደተጠበቀ ሆኖ’ የመንግሥት መሥሪያ ቤቱ ጨረታው የተሟላ ነው ብሎ ሊቀጥል የሚችለው በጨረታው ሰነድ የተመለከቱትን ተፈላጊ ሁኔታዎች ሙሉ በሙሉ የሚያሟላ ሆኖ ሲያገኘው ነው፡፡

፬ በጨረታው ሰነድ ከተዘረዘሩት ባህሪያት፣ የውል ቃሎች፣ ሁኔታች እና ሌሎችም ተፈላጊ ነጥቦች ጋር በተወሰነ ደረጃ ልዩነት ቢኖረውም መሠረታዊ የሆነ ለውጥ እና ልዩነት እስከሌለው ድረስ ወይም የጨረታውን ቁም ነገር ሳይለውጥ ሊታረም የሚችል ጥቃቅን ስህተት ወይም ግድፈት ቢኖረውም ግዥ ፈፃሚው አካል ጨረታውን እንደተሟላ አድርጎ ሊቀበል ይችላል፡፡ ማናቸውም ልዩነት እስከተቻለ ድረስ በአሀዝ ተገልጾ በጨረታ ግምገማ እና ውድድር ወቅት ከግምት ውስጥ መግባት አለበት፡፡

፭ ማናቸውም የመንግሥት መሥሪያ ቤት ከዚህ በታች የተዘረዘሩትን የማያሟሉ ተጫራቾችን አሸናፊ አድርጎ መምረጥ የለበትም፡-

2) Notwithstanding subarticle (1) of this Article, the public body may correct arithmetical errors that are discovered during the examination of bids. The public body shall give prompt notice of any such correction to the bidder that submitted the bid.

3) Without prejudice to sub-article (4) of this Article, the public body may regard a bid as responsive only if it conforms to salient requirements set forth in the bidding documents.

4) The public body may regard a bid as responsive even if it contains minor deviations that do not materially alter or depart from the characteristics, terms, conditions and other requirement set forth in bidding documents or if it contains errors or oversights that are capable of being corrected without touching on the substance of the bid. Any such deviations shall be quantified, to the extent possible, and appropriately taken account of in the evaluation and comparison of bids.

5) Any public body shall not award a contract to bidders when:

ሀ. ተጫራቹ በአንቀጽ ፳፰ (፩) የተጠቀሱትን መስፈርቶች ማሟላት የማይችል ሆኖ ሲገኝ፣

ለ. ተጫራቹ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ ፪ መሠረት የተደረገውን የሂሣብ ማስተካከያ የማይቀበል ሆኖ ሲገኝ፣

ሐ. የቀረበው የመጫረቻ ሰነድ በጨረታ ሰነዱ የተመለከቱትን ሁኔታዎች የማያሟላ ሆኖ ሲገኝ፣

፮ የመንግሥት መሥሪያ ቤቱ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ ፰ በተደነገገው መሠረት አሸናፊውን ተጫራች ለመምረጥ በጨረታ ሰነዱ በተመለከተው የግምገማ መስፈርት መሠረት ተፈላጊውን ያሟሉ የመጫረቻ ሰነዶችን መገምገምና ማወዳደር አለበት፡፡ በጨረታ ሰነድ ያልተመለከተ የማወዳደሪያ መስፈርት በጥቅም ላይ ሊውል አይችልም፡፡

፯ ማናቸውም ተጫራች በመጫረቻ ሰነዱ ከተመለከተው ውጪ በጨረታው አሸናፊ ለመሆን ያቀረበውን የመጫረቻ ዋጋ እንዲለውጥ ወይም ያቀረበውን የመወዳደሪያ ሐሳብ እንዲያሻሽል ወይም ይህንን ለመፈፀም ግዴታ እንዲገባ ሊጠየቅ ወይም ሊገደድ አይችልም፡፡

፰ በጨረታ አሸናፊ ሆኖ የሚመረጠው፡-

ሀ. በጨረታ ግምገማ የቴክኒክ መመዘኛዎችን ማሟላቱ የተረጋገጠ እና አነስተኛ ዋጋ ያቀረበ ተጫራች፤

a) the bidder has failed to quality the requirement, in the manner provided in Article 28(1) of this Proclamation,

b) the bidder does not accept a correction of an arithmetical error made pursuant to sub-article (2) of this Article;

c) the bid is not responsive

6) In the process of selecting the successful bidder, the public body shall consider substantially responsive bids for further evaluation and comparison, as defined in sub- article (8) of this Article in accordance with the criteria set forthin the bidding documents. No criterion shall be used that has not been set forth in the bidding documents.

7) No bidder may be requested or obliged to change the price offered in his bid or otherwise modify his proposal or to assume obligation to do so except as set forth in the bidding document.

8) The successful bid shall be:

a) The bid that is found to be responsive to the technical requirements and with the lowest evaluated price;

ለ. የመንግሥት መሥሪያ ቤቱ በጨረታው ሰነድ ውስጥ አሸናፊው ተጫራች የሚመረጥበትን መስፈርት የገለፀ ከሆነ፣ በጨረታ ሰነዱ የሰፈረውን የጨረታውን ኢኮኖሚያዊ እሴት የሚወስነውን መስፈርት መሠረት በማድረግ በሚካሄድ ግምገማ የተሻለ ኢኮኖሚያዊ ጠቀሜታ ያለው የጨረታ ሰነድና ዝቅተኛ ዋጋ ያቀረበው ተጫራች አሸናፊ ይሆናል፡፡ሆኖም መስፈርቱ በተጨባጭ ሁኔታ ላይ የተመሠረተ፣ በአሃዝ ሊገለፅ የሚችል ሆኖ በግምገማው ሂደት አንፃራዊ ክብደት የሚሰጠው እና እስከተቻለ ድረስ በገንዘብ የሚገለጽ መሆን አለበት፡፡

b) if the public body has so stipulated in the bidding documents, the bid offering better economic advantage ascertained on the basis of factors affecting the economic value of the bid which have been specified in the bidding documents, which factors shall, to the extent practicable, be objective and quantifiable, and shall be given a relative weight in the evaluation procedure or be expressed in monetary terms wherever practicable;

ሐ. ቢሮው በሚያወጣው ዝርዝር መመሪያ በሚወሰነው መሰረት በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ ፰ በፊደል (ሀ) ወይም (ለ) መሰረት የተመረጠው ተጫራች ህጋዊነት፣ የፋይናንስ እና የቴክኒክ አቅም በመጫረቻ ሰነድ ላይ በተቀመጠው መሰረት መሆኑ በድሕረ ግምገማ ሲረጋገጥ፣

c) where it is ascertained in post evaluation of bids that the legal, financial and technical standing of the candidate selected as the successful bidder in accordance with paragraph (a) or (b) of this sub-article conforms to the requirements stated in the bidding document.

፱ የመንግስት መስሪያ ቤቱ የግምገማውን ውጤት በአጭሩ የሚገልጽ የግምገማ ሪፖርት ማዘጋጀት አለበት፡፡

9) The public body shall prepare an evaluation report, containing a summaryof the examination and evaluation of bids

## ፵፬ በሚስጥር ስለሚያዙ አሠራሮች

ጨረታው ከተከፈተበት ጊዜ አንስቶ ከጨረታ ምርመራ፣ ከማብራሪያ፣ ከግምገማ እና አሸናፊውን ተጫራች በሚመለከት ከቀረበው የውሣኔ ሃሣብ ጋር የተያያዙ መረጃዎች በሚስጢርነት መጠበቅ ያለባቸው ሲሆን፤ አሸናፊው ተጫራች እስከሚገለጽ ድረስ ለተጫራቾች ወይም ከሥራው ሂደት ጋር ግንኙነት ለሌላቸው ሰዎች መገለጽ የለባቸውም።

## 44. Process to be Confidential

After the opening of bids, information relating to the examination, clarification, and evaluation of bids and recommendations for award shall be kept confidential and not be disclosed to bidders or other persons not officially concerned with this process until the award of the contract is announced.

## ፵፭ ከአሸናፊ ተጫራች ጋር ድርድር ስለሚደረግባቸው ጉዳዮች

፩ የመንግሥት መሥሪያ ቤቱ ከአሸናፊው ተጫራች ጋር የጨረታ ሰነዱ ላይ ባልተጠቀሱ የውል አፈጻፀም ጉዳዮች ላይ ድርድር ሊያደርግ ይችላል።

፪ በአንቀጽ ፶፩ ላይ በተጠቀሰው ከአንድ አቅራቢ በቀጥታ ለሚፈፀም ግዢ ካልሆነ በስተቀር አሸናፊው ተጫራች ባቀረበው ዋጋ እና ከዋጋ ጋር ግንኙነት ባላቸው ጉዳዮች ላይ የመንግሥት መስሪያ ቤቱ ከአሸናፊው ተጫራች ጋር ድርድር ማድረግ አይችልም።

## 45. Matters subject for Negotiation with the Successful Bidder

1) The public body may negotiate with the successful bidder on matters of contract performance not dealt within the bidding document.

2) Except in a single source procurement provided for in Article 51 of this Proclamation the public body may not negotiate on the price offered by the successful bidder and on other issues related to price.

## ፵፮ አሸናፊነትን ስለመግለጽና ውል ስለመፈራረም

፩ የመንግሥት መሥሪያ ቤቶች ከተጫራቹ የቀረበው የመጫራቻ ሰነድ ፀንቶ የሚቆይበት ቀን ከማለፉ በፊት በጨረታው አሸናፊ ለሆነው ተጫራች አሸናፊነቱን መግለጽ አለባቸው፡፡ የአሸናፊነት መግለጫ ማስታወቂያው ውሉ የሚፈረምበትን ቀን የሚገልጽ ይሆናል፡፡ በጨረታው ተሸናፊ ለሆኑ ተጫራቾችም የአሸናፊውን ስም እና የተሸነፉበትን ምክንያት የሚገልጽ ማስታወቂያ በደብዳቤ ሊደርሳቸው ይገባል፡፡

፪ በመንግሥት መሥሪያ ቤቱ እና በአቅራቢው መካከል ውል ተመስርቷል የሚባለው በሁለቱ ተዋዋይ ወገኖች ስምምነት የተደረሰባቸውን ጉዳዮች በሙሉ የሚይዘው የውል ሰነድ ሲፈረም ይሆናል፡፡

፫ የመንግሥት መሥሪያ ቤቱ ለተሸናፊዎቹ ተጫራቾች ተሸናፊነታቸውን የሚገልፀው ማስታወቂያ ከመድረሱ እና ቢሮው በሚያወጣው መመሪያ ላይ የተመለከተው የጊዜ ገደብ ከማለፉ በፊት የግዢውን ውል መፈረም የለበትም፡፡

፬ የመንግሥት መሥሪያ ቤቱ የውል አስተዳደርን በሚመለከት ሊከተል የሚገባው አሠራር ቢሮው በሚያወጣው መመሪያ ይወሰናል፡፡

## 46. Notification of Award and Signing of Contract

1) Prior to the expiry of the period of bid validity, the public body shall notify the successful bidder that its bid has been accepted. The notification of award shall specify the time within which the contract must be signed. The unsuccessful bidders shall also be informed as to who the successful bidder is and why they have lost the bid.

2) The existence of a contract shall be confirmed through the signature of a contract document incorporating all agreements between the parties.

3) The contract shall not be signed by the public body prior to the receipt of the notice by the unsuccessful bidder and before the period specified in the directive to be issued by the bureau has lapsed.

4) The procedures that public body has to follow in administering the contract shall be prescribed by a directive to be issued by the bureau.

## ፵፯ የውል ማስከበሪያ

አቅራቢው በውሉ መሠረት ባለመፈጸሙ በግዥ ፈፃሚው አካል ላይ ለሚደርሰው ጉዳት ማካካሻ የሚውል የውል ማስከበሪያ ለመስሪያ ቤቱ መስጠት አለበት፡፡ የውል ማስከበሪያ የሚጠየቅባቸው የግዢ ዓይነቶች፣የውል ማስከበሪያው ዓይነትና መጠን ቢሮው በሚያወጣው መመሪያ ይወሰናል፡፡

## ፵፰ የቅድሚያ ክፍያ

፩ በመንግሥት ግዢ አፈጻፀም ለአቅራቢው የሚሰጠው የቅድሚያ ክፍያ መጠን እና አፈጻፀም ቢሮው በሚያወጣው መመሪያ መሰረት ተፈጻሚ ይሆናል፡፡

፪ የቅድሚያ ክፍያ ሊፈፀም የሚችለው አቅራቢው በቅድሚያ ክፍያ መልክ ከሚወስደው ገንዘብ መጠን ጋር እኩል የሆነ ዋስትና ሲያቀርብ ይሆናል፡፡

## ምዕራፍ አምስት

## ውስን ጨረታ

## ፵፱ በውስን ጨረታ ለመጠቀም መሟላት ያለባቸው ሁኔታዎች

የመንግሥት መሥሪያ ቤቶች በውስን ጨረታ ግዥ መፈፀም የሚችሉት የሚከተሉት ሁኔታዎች ሲሟሉ ብቻ ነው፡-

፩ ዕቃው፣ የግንባታ ዘርፍ ሥራው ወይም አገልግሎቱ ከተወሰኑ አቅራቢዎች ብቻ የሚገኝ መሆኑ ሲረጋገጥ፤

## 47. Contract Security

A supplier shall provide the public body with a contract security to make good any damage the public body may sustain as a result of default by the supplier under the contract. The type of procurement for which contract security is required and the type and amount of contract security shall be determined by a directive to be issued by the bureau.

## 48. Advance Payment

1) The amount of advance payment that may be allowed to suppliers in public procurement and the manner in which it is made available shall be determined by the directive to be issued by the bureau.
2) Advance payment may be effected only where a supplier furnishes guarantee in an amount equal to the advance payment

.

## CHAPTER FIVE

## RESTRICTED TENDERING

## 49. Conditions for use of Restricted Tendering

Public bodies may use restricted tendering as a method of procurement only where the following conditions are satisfied:

1) it is a ascertained that the required object of procurement is available only with limited suppliers;

፪ የግዥው መጠን ቢሮው በሚያወጣው መመሪያ ከተቀመጠው የገንዘብ መጠን ያልበለጠ ሲሆን፤ ወይም

፫ ዝርዝር አፈጻፀሙ በመመሪያ የሚገለፅ ሆኖ በተደጋጋሚ ጨረታ ወጥቶ ተወዳዳሪ ያልተገኘ ሲሆን፡፡

## ፶ የውስን ጨረታ አፈጻፀም

የውስን ጨረታ ሥርዓቶች ከግልፅ ጨረታ ጋር ተመሳሳይ ሲሆኑ የሚከተሉትን ልዩ አሠራሮች ይከተላል፡-

፩ በዚህ አዋጅ በአንቀፅ ፵፱(፩) መሠረት ዕቃው፣ የግንባታ ዘርፍ ሥራው፣ የምክር ወይም ተፈላጊው ሌላ አገልግሎት የሚገኘው ከተወሰኑ አቅራቢዎች ብቻ ሲሆን የጨረታው ጥሪ ለነዚህ አቅራቢዎች በሙሉ ይላካል፤

፪ የውስን ጨረታው የሚካሄደው በዚህ አዋጅ በአንቀፅ ፵፱(፪) ወይም (፫) ላይ በተጠቀሰው ምክንያት ከሆነ የጨረታ ጥሪው እስከተቻለ ድረስ በአቅራቢዎች ዝርዝር ውስጥ ከተመዘገቡት አቅራቢዎች መካከል የሚከተሉትን መሠረት በማድረግ ይፈፀማል፡-

ሀ. አመራረጡ በአቅራቢዎች ዝርዝር ውስጥ ለተመዘገቡት ፍትሐዊ የሆነ ዕድል የሚያስገኝ መሆን ይኖርበታል፣

ለ. ጥሪ የሚደረግላቸው ዕጩ ተወዳዳሪዎች ብዛት ውጤታማ ውድድር እንዲኖር ለማድረግ የሚያስችል መሆኑ መረጋገጥ ያለበት ሲሆን፣ እስከተቻለ ድረስ የተወዳዳሪዎች ቁጥር ከ፭ ማነስ የለበትም፤

2) the cost of procurement does not exceed the threshold specified in respect of restricted tendering in the directive to be issued by the bureau; or

3) subject to the directive to be issued by the bureau, where a repeated advertisement of the invitation to bid fails to attract bidders in respect of a procurement.

## 50. Procedure for Restricted Tendering

Restricted tendering procedures are the same as those applied in open tendering, except that:

1) Where the goods, works, consultancy, or any other object of procurement is available only with limited suppliers in accordance with Article 49(1) of this Proclamation, the invitation to bid shall be sent to all such suppliers;

2) if restricted tendering is used for the reason stated in Article 49 sub-articles(2) or (3) of this Proclamation, the invitation to bid shall, as far as possible, be sent to limited suppliers chosen from among those registered in the suppliers list on the basis of the following consideration:

a) any selection shall allow opportunities for suppliers on the list,

b) the number of suppliers to whom the invitation to bid is sent shall be such that it is sufficient to ensure effective competition and shall not as far as possible be less than five competitors.

፫ ለመጫረቻ ሰነድ ዝግጅት የሚፈቀደው ጊዜ ለዚህ የግዥ ዘዴ በግዥ መመሪያው ከተወሰነው አነስተኛ ቀን ብዛት ያነሰ ሊሆን አይችልም፡፡ ሆኖም ለጨረታው ጥሪ የተደረገላቸው ተጫራቾች በሙሉ የመጫረቻ ሰነዳቸውን ከጨረታው መዝጊያ ቀን በፊት ካስገቡ የመንግሥት መስሪያ ቤቱ ለተጫራቾች በቂ የቅድሚያ ማስታወቂያ በመስጠት ጨረታውን በጨረታ ማስታወቂያ ላይ ከተቀመጠው ቀን አስቀድሞ ሊከፍት ይችላል፤

፬ የመንግሥት መስሪያ ቤቱ በውስን ጨረታ ግዢ የሚፈፅመው በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፵፱(፩) ላይ በተገለፀው ምክንያት ሲሆን የጨረታ ማስከበሪያ ማቅረብ የሚያስፈልግ መሆን ያለመሆኑን ይወስናል፡፡

## ምዕራፍ ስድስት

## <u>ከአንድ አቅራቢ የሚፈፀም ግዥ</u>

### ፶፩ <u>ከአንድ አቅራቢ ግዥ ለመፈፀም መሟላት ያለባቸው ሁኔታዎች</u>

፩ የመንግስት መሥሪያ ቤቶች ከአንድ አቅራቢ ግዥ መፈፀም የሚችሉት የሚከተሉት ሁኔታዎች ሲሟሉ ብቻ ነው፡-

ሀ. ዕቃው፣ የግንባታ ዘርፍ ሥራው፣ የምክር ወይም ተፈላጊው ሌላ አገልግሎት የሚገኘው ከአንድ ዕጩ ተወዳዳሪ ብቻ በመሆኑ ምክንያት ማወዳደር የማይቻል መሆኑ ሲረጋገጥ፤

3) the time allowed for preparation of bids shall not be less than the minimum number of days stated in the procurement directive for this method of procurement. However, if all suppliers invited to participate in the bid have submitted their bids before the closing date, the public body may open the bid ahead of schedule by giving bidders prior notice;

4) if the public body uses restricted tendering for the reason stated on Article 49(1) of this Proclamation, it shall determine whether it is necessary to require the candidates to submit bid security.

## <u>CHAPTER SIX</u>

## <u>DIRECT PROCUREMENT</u>

### 51. <u>Conditions for the Execute of Direct Procurement</u>

1) Public bodies may use direct procurement only where the following conditions are satisfied:

a) When it is proved impossible to make competitions for technical reasons the goods, works consultancy or other required services can be supplied or provided only by one candidate;

ለ. ለዕቃዎች፣ ወይም ለተገጣሚዎች ተጨማሪ መለዋወጫ ዕቃዎችን ወይም ተጨማሪ አገልግሎቶችን ከመጀመሪያው አቅራቢ መግዛት ሲፈለግ፣ ወይም ከሌላ አቅራቢ ግዢው ቢፈጸም የሚገዛው ተገጣሚ መሣሪያ ወይም አገልግሎት ግዢ የመንግሥት መሥሪያ ቤቱ ከሚጠቀምበት መሣሪያ ወይም አገልግሎት ጋር የማይጣጣም ሆኖ በመገኘቱ ከመጀመሪያ አቅራቢ መለዋወጫዎችን፣ አገልግሎቶችን ወይም ተገጣሚዎችን መግዛት አስፈላጊ ሲሆን፤

ሐ. በግዥ መመሪያ የሚደረገው ገደብ እንደተጠበቀ ሆኖ፣ ያልታሰቡ ሁኔታዎች በማጋጠማቸው ምክንያት በመጀመሪያው ውል ውስጥ ያልተካተቱ ተጨማሪ የግንባታ ዘርፍ ሥራዎች ማሰራት አስፈላጊ ሆኖ የተገኘ እንደሆነ እና በቴክኒክ ወይም በኢኮኖሚ ምክንያቶች እነዚህን ተጨማሪ የግንባታ ሥራዎች ከመጀመሪያው ውል ነጥሎ ማሰራት የማይቻል ሆኖ ሲገኝ፤

መ. በግዥ መመሪያ የሚደረገው ገደብ እንደተጠበቀ ሆኖ፣ አሸናፊው ከተመረጠ በኋላ በተፈረመ ውል የመጀመሪያው ግዥ የተከናወነባቸው ዓይነት ተመሳሳይ ሥራ-ዎች ወይም አቅርቦቶች በድጋሚ እንዲሠሩ ወይም እንዲቀርቡ ማድረግ በማስፈለጉ ተጨማሪ ውል መፈፀም አስፈላጊ ሲሆን፤

b) for additional deliveries of goods by the original supplier which are intended either as parts of replacement for existing supplies, services or installations or as the extension of existing supplies, services or installation where a change of supplies would compel the public body to procure equipment or services not meeting requirements of interchangeability with already existing equipment or services;

c) within limits defined in the procurement directive, when additional works, which have been not included in the initial contract have, through unforeseeable circumstances, become necessary since the separation of the additional works from the initial contract would be difficult for technical or economic reasons;

d) without prejudice to the limits prescribed in the procurement directives, for new works consisting of the repetition of similar works which conform to a basic project of which an initial contract has been awarded on the basis of open or restricted bidding;

ሠ. በግዥ መመሪያ የሚደረገው ገደብ እንደተጠበቀ ሆኖ፣ የመጀመሪያው የምክር ወይም ሌሎች አገልግሎቶች ውል አጥጋቢ በሆነ ሁኔታ መጠናቀቁ እና ውሉ እንዲራዘም ማድረግ ቁጠባንና ቅልጥፍናን የሚያስገኝ መሆኑ በመረጋገጡ አገልግሎቱን መቀጠል አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ፤

ረ በጣም አስቸኳይ ከመሆኑ የተነሣ ከባድ ችግር የሚፈጥርና በመስሪያ ቤቱ ሥራ አፈፃፀም ላይ ጉዳትን የሚያስከትል በመሆኑ ምክንያት በመስሪያ ቤቱ የበላይ ኃላፊ የተፈቀደ ግዥ፤

ሰ ዝርዝር አፈጻፀሙ ቢሮው በሚያወጣው መመሪያ የሚወሰን ሆኖ የመንግሥት መስሪያ ቤቶች ለሚኖራቸው የተለየ የግዥ ፍላጎት ማሟያ ከገበያ በለቀማ ግዥ መፈፀም የሚያስገድዱ ሁኔታዎች ሲፈጠሩ፤

ሸ ለአጭር ጊዜ የሚቆይ እና ለመንግሥት መስሪያ ቤቱ ልዩ ጥቅም በሚያስገኝ ሁኔታ የሚፈፀም የዕቃ ግዥ ሲሆን ነው፡፡ ይህ ንዑስ አንቀጽ የሚያገለግለው በመደበኛ አቅራቢነት ያልተሰማሩ ሰዎች ለሚሸጧቸው ዕቃዎች ሲሆን በመደበኛ አቅራቢነት ከተሰማሩ አቅራቢዎች አዘውትረው የሚፈፀሙ ግዥ-ዎችን አይጨምርም፡፡

፪ የመንግሥት መስሪያ ቤቶች በግዥ መመሪያው ከሚወሰን የገንዘብ መጠን ያልበለጡ ጥቃቅን ግዥዎችን ከአንድ አቅራቢ በሚፈፀም የግዥ ዘዴ በመጠቀም መግዛት ይችላሉ፡፡

e) without prejudice to the limits prescribed in the procurement directives, for continuation of consultant services, where the original contract has been satisfactorily performed and the continuation is likely to lead to gains in economy and efficiency;

f) the head of the public body has determined that the need is one of pressing emergency in which delay would create serious problems and therefore injurious to the performance of that public body;

g) where situations arise in which shopping becomes necessary to meet the special procurement needs of public bodies. The manner of implementation of this provision shall be prescribed by the directive to be issued by the bureau;

h) for purchase of goods made under exceptionally advantageous conditions which only arise in the very short term. This provision is intended to cover unusual disposals by firms, which are not normally suppliers. It is not intended to cover routine purchases from regular suppliers.

2) Public bodies may use direct procurement when the contract price does not exceed an amount stated in the procurement directive.

፫ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ ፩ /ሰ/ እና ፪ መሠረት ከአንድ አቅራቢ በቀጥታ ለሚፈፀሙ ግዥዎች ውል መዋዋል አስፈላጊ አይሆንም፡፡

፬ የመንግሥት መሥሪያ ቤቶች ይህ የግዥ ዘዴ በዕጩ ተወዳዳሪዎች መካከል ውድድር እንዳይኖር ወይም በዕጩ ተወዳዳሪዎች መካከል ልዩነት ለመፍጠር ታስቦ ጥቅም ላይ ያልዋለ መሆኑን የማረጋገጥ ኃላፊነት አለባቸው፡፡

## ፶፪ ከአንድ አቅራቢ የሚከናወን ግዥ አፈጻፀም

፩ የመንግሥት መስሪያ ቤቶች በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፶፩/፩/ በተደነገገው መሠረት ከአንደ አቅራቢ ግዥ ለመፈፀም ሲፈልጉ ግዥውን መፈፀም ያስፈለገበትን ምክንያት እና የሚገዛው ዕቃ ወይም አገልግሎት ጥራት፣ ብዛት፣ የማቅረቢያ ጊዜና ሁኔታዎች የሚያብራራ መግለጫ ማዘጋጀትና ዋጋን ጨምሮ ከአቅራቢው ጋር በግልፅ መደራደር አለባቸው፡፡ በዚህ አዋጅ በአንቀጽ ፶፩/፫/ የተገለፀው እንደተጠበቀ ሆኖ ድርድሩ ከተካሄደ በኂላ ግዥ ለመፈፀም የሚደረሰው ስምምነት በሁለቱ ተዋዋይ ወገኖች በሚፈረም ውል መረጋጥ አለበት፡፡

3) It shall not be necessary to conclude a contract in respect of direct procurements effected in accordance with sub-articles (1) (g) and (2) of this Article.

4) Public bodies shall ensure that this method is not resorted to with a view to avoiding possible competition or in a manner which would constitute a means of discrimination among candidates.

## 52. Procedure for Direct Procurement

1) When the public body engages in direct procurement according to Article 51(1) of this Proclamation, it shall prepare a description of its needs and any special requirements as to quality, quantity, terms and time of delivery, and shall be free to negotiate on price and conditions of offer with the sole candidate. Without prejudice to the provisions of sub-article (3) of Article 51 of this Proclamation, any agreement reached to conduct the procurement shall be confirmed by a contract signed by both parties.

፪ ከአንድ አቅራቢ በቀጥታ ለሚፈፀም ግዥ ድርድር የማድረጊያ አትኩሮተ-ነጥቦች ዝርዝር በመንግሥት መስሪያ ቤቱ የበላይ ሀላፊ ፀድቆ ለተደራዳሪዎች ሊሰጥ ይገባል፡፡

## ምዕራፍ ሰባት
## በመወዳደሪያ ሀሳብ መጠየቂያ የሚፈፀም ግዥ

### ፶፫ በመወዳደሪያ ሀሣብ መጠየቂያ ግዥ ለመፈፀም መሟላት ያለባቸው ሁኔታዎች

የመንግሥት መስሪያ ቤቶች በመወዳደሪያ ሀሳብ መጠየቂያ ግዥ መፈፀም የሚችሉት ለምክር አገልግሎት ወይም ከውሉ ጠቅላላ ዋጋ ውስጥ የምክር አገልግሎቱ ዋጋ ከ፶ በመቶ በላይ ለሚሆን ግዥ ነው፡፡

### ፶፬ በመወዳደሪያ ሀሳብ መጠየቂያ የሚከናወን ግዥ አፈጻፀም

፩ የምክር አገልግሎቱ የሚጠይቀው ወጪ በመመሪያ ከሚወሰነው የገንዘብ መጠን በላይ ከሆነ ዕጩ ተወዳዳሪዎች የሚመረጡት በውድድሩ ተሳታፊ ለመሆን የሚፈልጉ ሀሳባቸውን እንዲገልጹ በማስታወቂያ ከተጋበዙ በኂላ ይሆናል፡፡

፪ የመወዳደሪያ ሀሳብ መጠየቂያ ከሦስት ላላነሱ እና ከሰባት ላልበለጡ በመንግሥት መሥሪያ ቤቱ ለሚመረጡ ዕጩ ተወዳዳሪዎች መላክ ይኖርበታል፡፡

፫ የመወዳደሪያ ሀሳብ መጠየቂያ ቢያንስ የሚከተሉትን መረጃዎች መያዝ አለበት፡-

2) The salient points to focus on in the negotiation of contracts for direct procurements shall be approved by the head of the concerned public body and communicated to the negotiators.

## CHAPTER SEVEN
## REQUEST FOR PROPOSALS

### 53. Conditions for the Execut of Request for Proposal

Public bodies may engage in procurement by means of request for proposals when it seeks to obtain consultancy services or contracts for which the component of consultancy services represents more than 50% of the amount of the contract.

### 54. Procedure for Request for Proposals

1) The selection of candidates for consultancy services above a threshold to be determined by a directive shall be made after inviting candidates to submit expression of interest.

2) Requests for proposals shall be addressed to not less than three and not more than seven candidates selected by the public body.

3) A request for proposals shall contain at least the following information:

ሀ. የመንግሥት መስሪያ ቤቱን ስምና አድራሻ፤

ለ. የሚፈለገውን አገልገሎት የሚያሳይ የማጣቀሻ ፅሑፍ፤

ሐ. የጥቅም ግጭት ሊያስከትል የሚችል የምክር አገልግሎት በሚሆንበት ጊዜ ለዚህ ዓይነቱ ውድድር የሚቀርቡ ዕጩ ተወዳዳሪዎች ከምክር አገልግሎቱ በማስከተል ከምክር አገልግሎቱ ጋር በተያያዘ ከሚከናወኑ የዕቃ አቅርቦትና የግንባታ ሥራዎች ራሳቸውን ማግለል የሚገባቸው መሆኑን የሚገልፅ ማሳሰቢያ፤

መ. የመወዳደሪያ ሀሳቦችን መገምገምያ `መስፈርቶችን፣ ለዋጋና ለሌሎች መስፈርቶች የሚሰጠውን ነጥብ፣ መስፈርቶቹ የመወዳደሪያ ሀሳብ በሚገመገምበት ወቅት ጥቅም ላይ የሚውሉበትን አኳኋን ፤

ሠ. የመወዳደሪያ ሀሳብ የሚቀርብበትን ቦታና የመጨረሻ ቀን፡፡

፬ ዕጩ ተወዳዳሪዎች የመወዳደሪያ ሀሳብ ለማዘጋጀት የሚያስችላቸው በቂ ጊዜ ሊሰጣቸው የሚገባ ሲሆን፣ የጊዜ ገደቡ በግዥ መመሪያ ይወሰናል፡፡

፭ የመንግሥት መሥሪያ ቤቱ አንደኛ ሆኖ ከተመረጠው ዕጩ ተወዳዳሪ ጋር በመወዳደሪያ ሀሳቡ ውስጥ የተመለከተውን የአገልግሎቱን ባህሪ፣ መጠን እና አደረጃጀት የሚመለከት ድርድር ማድረግ ይችላል፡፡

a) the name and address of the procuring entity;

b) Description of the services required, normally through terms of reference;

c) in the case of consultancy assignments which may involve potential conflicts of interest, a reminder that candidates for such assignments must exclude themselves from procurement of goods and works which may follow as a result of or in connection with the consultancy agreement;

d) the criteria for evaluating the proposals, the relative weight to be given to price and other criteria, and the manner in which they will be applied in the evaluation of proposals;

e) Place and deadline for the submission of proposals.

4) Candidates shall be given adequate time in which to prepare their proposals; such time frame shall be determined by the procurement directive.

5) The public body may negotiate with the first ranked candidate with respect to the nature, volume and organization of the services included in their proposals.

፯ የመንግሥት መስሪያ ቤቱ ከዕጩ ተወዳዳሪዎች መካከል በአሸናፊነት ሊመርጥ የሚችለው በመወዳደሪያ ሀሳብ መጠየቂያ ሰነድ በተመለከተው የመገምገሚያ መስፈርት መሠረት በሚካሄደው ግምገማ ያቀረበው የመወዳደሪያ ሀሳብ ይበልጥ ጠቃሚ ሆኖ የተገኘውን ዕጩ ተወዳዳሪ ነው፡፡

6) Any award by the public body shall be made to the candidate whose proposal is most advantageous, determined in accordance with the criteria and procedures for evaluating proposals set forth in the request for proposals.

## ምዕራፍ ስምንት

## በአካባቢ ማስታወቂያ በመለጠፍ የሚፈፀም ግዥ

### ፶፭ በአካባቢ ማስታወቂያ በመለጠፍ ለሚፈፀም ግዥ መሟላት ያለባቸው ሁኔታዎች

የመንግሥት መስሪያ ቤቶች በአካባቢ ማስታወቂያ በመለጠፍ ግዥ ለመፈፀም የሚችሉት ግዥው በቢሮው በሚወጣው የግዥ መመሪያ ከሚወስነው የገንዘብ መጠን ያልበለጡ እና የሚገዙትም ለገበያ የተዘጋጁ ዕቃዎች ወይም የታወቀ ገበያ ያላቸው የግንባታ ዘርፍ ሥራዎች ወይም አገልግሎቶች ሲሆኑ ነው፡፡

### ፶፮ በአካባቢ ማስታወቂያ በመለጠፍ የሚካሄድ ግዥ አፈጻፀም

፩ የመንግሥት መስሪያ ቤቶች የሚቻል እስከሆነ ድረስ አቅራቢዎች በቀላሉ ማየት በሚችሉት ቦታና ለመንግሥት ግዥና ንብረት ማስወገድ የሚዘጋጁ ማስታወቂያዎችን ለመለጠፍ እንዲያገለግሉ የተዘጋጁ ማስታወቂያ መለጠፊያ ቦርዶች ላይ ተወዳዳሪዎች እኩል ዕድል አግኝተው መወዳደር በሚችሉበት ሁኔታ መለጠፍ አለባቸው፡፡

## CHAPTER EIGHT

## ADVERTISED PROCUREMENT

### 55. Conditions for ADVERTISED PROCUREMENT

Public bodies may engage in procurement by means of request for quotations for the purchase of readily available goods or for procurement of works or services for which there is an established market, so long as the estimated value of the contract does not exceed an amount stated in the procurement directive to be issued by the Bureau .

### 56. Procedure for Request of Quotations

1/ public bodies shall, as much as possible, post a request of quotation in a visible notice board where the supplier can see and having used for public procurement and disposal advertisement in a manmer that enable the candidates to compete on equal opportunity.

፪ ማስታወቂያ በመለጠፍ ለሚፈፀመው ግዥ በመስሪያ ቤቱ ተዘጋጅቶ ለአቅረቢዎች የሚሰጠው መጠየቂያ የሚቀርበውን ዕቃ ወይም፣ የግንባታ ሥራ፣ ወይም የምክር ወይም ሌላ አገልግሎት ጥራት፣ ብዛት፣ የማቅረቢያ ውል ቃሎች እና ጊዜ እንዲሁም ሌሎች የመንግሥት መሥሪያ ቤቱን ፍላጎቶች ዝርዝር የሚገልፅ መሆን አለበት።

፫ ግዥ ፈፃሚው የመንግስት መስሪያ ቤት ለዕጩ ተወዳዳሪዎች ከመስሪያ ቤቱ የወሰዱትን መጠየቂያ ለማዘጋጀት የሚያስችል በቂ ጊዜ ሊሠጣቸው ይገባል።የመንግሥት መሥሪያ ቤቱ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ ፪ የተዘረዘሩትን ተፈላጊ ሁኔታዎች አሟልቶ እና አነስተኛ ዋጋ ላቀረበ ተወዳዳሪ የግዥ ትዕዛዝ ይሰጣል።

## ምዕራፍ ዘጠኝ

## በሁለት ደረጃ ጨረታ የሚፈፀም ግዥ

### ፶፯ በሁለት ደረጃ ጨረታ ግዥ ለመፈፀም መሟላት ያለባቸው ሁኔታዎች

የመንግሥት መስሪያ ቤቶች በሁለት ደረጃ ጨረታ ግዥን ለመፈፀም የሚችሉት የሚከተሉት ሁኔታች ተሟልተው ሲገኙ ብቻ ነው:-

፩ ለሚገዙት ዕቃችና አልግሎቶች በቂ ዝርዝር ማዘጋጀት በመስሪያ ቤቱ ደረጃ የማይቻል ሆኖ ሲገኝ ወይም አገልግሎቶችን በሚመለከት ባህሪያቸውን ለይቶ ለማሳየት የማይቻል በሚሆንበት ጊዜ እና የመስሪያ ቤቱን የግዥ ፍላጎት በከፍተኛ ደረጃ ለማሟላት የሚያስችል መፍትሔ ለመፈለግ፤

2) In cases where procurements are made using request for quotation, The request shall contain a clear statement of the requirements of the public body as to quality, quantity, terms and time of delivery of the goods, works, consultancy or other services as well as other special requirements.

3) The public body shall give adequate time to candidates in which to prepare their quotations. A purchase order shall be placed with the candidate who meets the requirements of the public body stipulated in sub- article (2) of this Article.

## CHAPTER NINE

## TWO -STAGE BIDDING

### 57. Conditions for the Execute of Two-Stage Bidding

Public bodies may engage in procurement by means of two-stage bidding:where the following conditions fulfilled

1) when it is impossible for the public body to formulate detailed specifications for the goods or works and in the case of services, to identify their characteristics and, in order to obtain the most satisfactory solution to its procurement needs;

፪ ግዥው የሚካሄደው በገበያ ላይ ሊውሉ የሚችሉ ዕቃዎችን ለማምረት ወይም የምርምር እና የልማት ወጪዎችን ለመተካት እስካልሆነ ድረስ የመንግሥት መስሪያ ቤቱ የምርምር፣ የሙከራ፣ የጥናት እና የልማት ሥራዎችን ለማከናወን የሚያስችል ውል መፈፀም ሲፈልግ፤

፫ ጨረታ እንዲወጣ ተደርጎ በሚገዙ ዕቃዎች፣ የግንባታ ዘርፍ ሥራዎች፣ የምክርና ሌሎች አገልግሎቶች ባህሪይ ወይም ተፈጥሮ ግልፅ አለመሆን ምክንያት ዕጩ ተወዳዳሪዎች በጨረታው ያልቀረቡ እንደሆነ ወይም የቀረቡት ተጫራቾች ውድቅ ሲደረጉ እና ይኸም የሆነው መስሪያ ቤቱ የተሟላ ዝርዝር ማዘጋጀት ባለመቻሉ መሆኑ ሲታመን፤

፬ የሚገዙ ዕቃዎች፣ የግንባታ ዘርፍ ሥራዎች፣ የምክርና ሌሎች አገልግሎቶች ባሕሪይ ወይም ተፈጥሮ አስመልክቶ ከዕጩ ተወዳዳሪዎች ጋር ድርድር ማድረግ ሲያስፈልግ፡፡

## ፶፰ የሁለት ደረጃ ጨረታ አፈጻፀም

፩ ጨረታው የሚከናወነው በሁለት ደረጃ የጨረታ ዘዴ ሲሆን፤በመጀመሪያ ዙር ዕጩ ተወዳዳሪዎች ዋጋን ያልጨመረ የመወዳደሪያ ሀሣብ እንዲያቀርብ ጥሪ ይደረጋል፡፡ በጨረታው ሰነድ ከቴክኒክ ጋር ግንኙነት ያላቸውን መግለጫ-ችዎች፣ ጥራት ወይም የዕቃውን ወይም የአገልግሎቱን ሌሎች ባህሪያት እንዲሁም የአቅርቦቱን ውል ቃሎችና ሁኔታዎች ሊይዝ የሚገባ ሲሆን፣ አግባብነት እስካለው ድረስ የዕጩ ተወዳዳሪዎችን የሙያ እና የቴክኒክ ችሎታ እንዲገልጹ የሚጠየቅ ሊሆን ይችላል፡፡

2) when the public body seeks to enter into a contract for the purpose ofresearch, experiment, study or development, except where the contract includes the production of goods in quantities sufficient to establish their commercial viability or to recover research and development costs;

3) where bid proceedings are initiated but no bids aresubmitted as a result of the nature of the object of procurement not being clearly described or where all bids are rejected due to failure on the part of the public body concerned to draw up a clear and complete specification;

4) when it is necessary for the public body to negotiate with the suppliers regarding the technical character and the nature of the required goods, works, or the consultancy or other services.

## 58. Procedure for Two-Stage Bidding

1) The solicitation documents shall call upon suppliers to submit, in the first stage of the two-stage bidding proceedings, initial tenders containing their proposals without a tender price. The solicitation documents may solicit proposal relating to the technical, quality or other characteristics of the goods, works or services as well as to contractual terms and conditions of supply, and where relevant the professional and technical competence and qualifications of the suppliers.

፪ የመንግሥት መሥሪያ ቤቱ በመጀመሪያ ዙር የቀረቡትን የመወዳደሪያ ሐሳቦች ከግዥ ፍላጎቱ አንጻር በመገምገም ተቀባይነት ያለው የመወዳደሪያ ሐሳብ ያቀረቡ ተጫረቾችን ይለያል፡፡ በዚህ ወቅት የመንግሥት መስሪያ ቤቱ እንደአስፈላጊነቱ ከዕጩ ተወዳዳሪዎች ጋር ስላቀረቡት የመወዳደሪያ ሐሳብ የተወዳዳሪዎችን የጨረታ መረጃ እና የባለቤትነት መብት ጠብቆ ውይይት ሊያደርግ ይችላል፡፡

፫ የመንግሥት መሥሪያ ቤቱ በመጀመሪያ ዙር የቀረቡትን የመወዳደሪያ ሐሳቦች ከግዥ ፍላጎቱ አንጻር በመገምገም ፍላጉቱን በተሻለ ሊያሟላ የሚችል አንድ ወጥ የሆነ ዝርዝር ያዘጋጃል፡፡ የተዘጋጀውን ዝርዝር በመጀመሪያ ዙር ተቀባይነት ያለውን የመወዳደሪያ ሐሳብ ላቀረቡ ተጫረቾች በማሳወቅ ተጫራቾች ዋጋን ጨምሮ በተሻሻለው ዝርዝር መሰረት የመጫረቻ ሐሳባቸውን እና የጨረታ ማስከበሪያ እንዲያቀርቡ ይጋብዛል፡፡

፬ በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ 3 ላይ በተገለፀው መሠረት መስሪያ ቤቱ አዲስ ዝርዝር ሲያዘጋጅ በመጀመሪያው የጨረታ ሰነድ ውስጥ ከተቀመጡት ማናቸውም የዕቃው ወይም የአገልግሎቱ የቴክኒክ ወይም የጥራት ባህሪያት እና ሰነዶቹን ለመገምገም እና ለማወዳደር እንዲሁም አሸናፊውን ለመምረጥ ከተቀመጡት መስፈርቶች ውስጥ ማናቸውንም ለመሰረዝ ወይም ለማሻሻል ወይም ከዚህ አዋጅ ጋር የሚስማሙ አዳዲስ ባህርያትንና መስፈርቶችን ለመጨመር ይችላል፡፡ እንደዚሁ ያሉት ማናቸውም ስረዛዎች፣ ማሻሻያዎች ወይም ጭማሪዎች የመጨረሻ የመወዳደሪያ ሐሳብ እንዲቀርብ በሚተላለፍ ጥሪ ለተጫራቾች መገለጽ አለባቸው፡፡

2) The public body shall identify responsive bids by evaluating the proposals submitted by the bidders at the first stage of the bid proceeding against its requirements. The public body may, without prejudice to their intellectual property rights at this stage, hold discussion with the candidates on the content of their proposals.

3) The public body shall draw up a specification which is more appropriate to its requirements on the basis of the evaluation against the requirements of the proposals submitted to it at the first stage of the bid proceeding. It shall then proceed to communicate the revised specification to the candidates who submitted responsible bids at the first stage and invite such candidates to submit proposals on the basis of the revised specification.

4) In formulating the revised specification in accordance with sub article (3) of this Article, the public body may delete or modify any aspect, originally set forth in the solicitation documents of the technical or quality characteristics of the goods, works or services to be procured and any criterion originally set forth in those documents for evaluating and comparing bids and for ascertaining the successful bids and may add new characteristics or criteria that conform with this Proclamation. Any such deletion, modification or addition shall be communicated to suppliers in the invitation to submit final bids.

፭ በተሻሻለው ዝርዝር መሠረት በሁለተኛው ዙር ጨረታ መሳተፍ ያልፈለጉ ተጫራቾች ራሳቸውን ከውድድሩ ማግለል ይችላሉ፡፡

፮ የመንግሥት መሥሪያ ቤቱ በሁለተኛ ዙር የቀረቡ የመጫረቻ ሠነዶችን በዚህ አዋጅ አንቀፅ ፵፫ በተደነገገው መሠረት በመገምገም አሸናፊውን ይለያል፡፡

፯ ጨረታውን ያወጣው የመንግሥት መሥሪያ ቤት በጨረታው ግምገማ ከፍተኛ ውጤት ካገኘው አቅራቢ ጋር ከዋጋ በስተቀር በሌሎች ጉዳዮች ላይ ድርድር ሊያደርግ ይችላል፡፡

5) A supplier not wishing to participate in the second stage of tendering in accordance with the reformulated specification may withdraw from the proceeding.

6) The public body shall evaluate the bids submitted at the second stage to ascertain the successful bidder pursuant to the provisions of Article 43 of this Proclamation.

7) The public body may engage in negotiation with the first ranking bidder concerning any aspect of its bid, except price.

## ምዕራፍ አስር
## በዓለም አቀፍ ውድድር የሚፈፀም ግዥ

### ፶፱ ዓለም አቀፍ ግዥ

1 አለም አቀፍ ግልጽ የጨረታ ዘዴ ጥቅም ላይ ሊውል የሚችለው የውጭ ኩባንያዎች በጨረታ ተሳታፊ እንዲሆኑ ካልተደረገ በአገር ውስጥ ግልጽ ጨረታ ውጤታማ የሆነ ውድድር ሊኖር እንደማይችል የታመነበት ወይም ግዥው ቢሮው በሚያወጣው መመሪያ ከተመለከተው የገንዘብ መጠን በላይ ሲሆን ነው፡፡

2 በዚህ አንቀጽ ንዑስ (፩) እንደተመለከተው ግዥው ቢሮው በሚያወጣው መመሪያ ከተመለከተው የገንዘብ መጠን በላይ ቢሆንም ምርቱ ወይም አገልግሎቱ በአገር ውስጥ ብቻ የሚገኝ መሆኑ ከተረጋገጠ ግዥው በአገር ውስጥ ግልጽ ጨረታ ሊካሄድ ይችላል፡፡

## CHAPTER TEN
## INTERNATIONAL COMPETITIVE BIDDING

### 59. Open International Bidding

1) Open international bidding shall be used whenever in national open bidding an effective competition cannot be obtained unless foreign firms are invited to bid or for procurements above a threshold level for national bidding to be determined by a directive to be issued by the bureau.

2) A procurement may be effected by means of national competitive bidding notwithstanding sub –article(1) of this article that the cost of the procurement exceeds the threshold established in the directive to be issued by the bureau for national bidding if it is ascertained that the required object of procurement is available only locally.

፫ ዓለም አቀፍ ግዥ በዚህ አዋጅ ምዕራፍ አራት የተጠቀሱትን እና ከዚህ በታች የተዘረዘሩትን ስርዓቶች መከተል አለበት፡-

ሀ. የጨረታው ማስታወቂያ እና የጨረታ ሰነዶች የዓለም አቀፍ ንግድ መገልገያ በሆነው በእንግሊዘኛ መዘጋጀት አለባቸው፤

ለ. የጨረታ ማስታወቂያው በተዘጋጀበት በእንግሊዘኛ ቋንቋ በሚታተም ፣በቂ ስርጭት ባለው እና ዓለም አቀፍ ውድድርን በሚጋብዝ ጋዜጣ እንዲሁም በመመሪያ ላይ በሚገለጸው መሰረት በኤጀንሲው ድረ ገጽ ላይ እንዲወጣ መደረግ አለበት ፤

ሐ. የመጫረቻ ሰነድ የማቅረቢያው ጊዜው የጨረታ ማስታወቂያው ለእጩ ተወዳዳሪዎች እንዲደርስ ለማድረግ እና እጩ ተወዳዳሪዎች የመወዳደሪያ ሀሳባቸውን አዘጋጅተው ለማቅረብ የሚያስፈል ጋቸውን በቂ ጊዜ የሚፈቅድ መሆን ያለበት ሲሆን፤ ቢሮው በሚያወጣው መመሪያ ከሚወሰነው ጊዜ ሊያንስ አይችልም፤

መ. የእቃና የአገልግሎት ዝርዝር ከአገር ውስጥ ደረጃ ጋር የሚጣጣም ሆኖ እስከተቻለ ድረስ በዓለም አቀፍ ደረጃዎች ወይም በዓለም አቀፍ ንግድ በስፋት የሚሰራበትን ደረጃ መሰረት ያደረገ መሆን አለበት፤

3) Open international bidding shall respect the provisions of Chapter Four of this Proclamation as well as the following procedures:

a) the invitation to bid and the bid documents shall be in the English language;

b) the invitation to bid shall be advertised in a news paper published in English language which has world wide circulation and attracts foreign competition as well as on the Agency's website in the manner prescribed in the directive;

c) the time allowed for submission of bids shall be sufficient for the invitation to reach candidates and for enabling them to prepare and submit bids. In any case it shall not be less than the time prescribed by the directive to be issued by the bureau;

d) technical specifications of the goods, works and services shall be compatible with national requirements, and conform as far as possible with international standards or standards widely used in international trade;

ሠ. ዕጩ ተወዳዳሪዎች የመጫረቻ ዋጋቸውን እንዲሁም የሚያቀርቡትን ማናቸውንም የዋስትና ሰነድ በኢትዮጵያ ብር ወይም በሰነዱ በተመለከተው እና በአለም አቀፍ ንግድ በስፋት በሚሰራበት የገንዘብ አይነት እንዲያቀርቡ መፈቀድ አለበት፤

ረ አጠቃላይ እና ልዩ የውል ቃሎችና ሁኔታዎች በአለም አቀፍ ንግድ የሚሰራባቸው መሆን ይኖርባቸዋል፡፡

፬ ቢሮው በሚያወጣው መመሪያ ላይ የሚቀመጠው ገደብ እንደተጠበቀ ሆኖ ለየግዥ ዘዴው የተቀመጡ ሁኔታዎች ሲሟሉ እና የውጪ ኩባንያዎች እንዲሳተፉ ካልተደረገ ውጤታማ የሆነ ውድድር ሊኖር እንደማይችል ሲታመንበት የመንግስት መስሪያ ቤቶች በውስን ጨረታ፣ በመወዳደሪያ ሀሳብ መጠየቂያ፣ ማስታወቂያ በመለጠፍ በሚፈፀም ግዥ ወይም ከአንድ አቅራቢ በሚፈፀም ግዥ ዘዴ በመጠቀም ግዢውን በዓለም አቀፍ ውድድር መፈፀም ይችላሉ፡፡

## ምዕራፍ አስራ አንድ
## ልዩ ግዥ

### ፷ ከፍተኛ ግዥዎች

፩ ክልላዊ ጠቀሜታ ያላቸውን ከፍተኛ ግዥዎች እንዲሁም ከአንድ በላይ በሆኑ የክልሉ መንግሥት መስሪያ ቤቶች የሚፈለጉ አቅርቦቶችን ግዥ እንዲሁም የሚወገዱ ንብረቶችን ሽያጭ የሚፈፅም አካል የክልሉ መስተዳደር ምክር ቤት በሚያወጣው ደንብ ይቋቋማል፡፡ ቢሮው በሚቋቋመው አካል አማካይነት የሚፈፀሙትን ግዥዎች ዓይነት ይወስናል፡፡

e) candidates shall be permitted to express their bids, as well as any security documents to be presented by them in Ethiopian Birr, or in a currency widely used in international trade and stated in the bidding documents;

f) general and special conditions of contract shall be of a kind generally used in international trade.

4) Without prejudice to the threshold to be established in the directive to be issued by the bureau and provided that conditions for using other methods of procurement than open bidding are satisfied, public bodies may conduct procurement through international competitive bidding by means of restricted tendering, request for proposals, request for quotation or direct procurement where it is ascertained that it is impossible to carry out effective procurement without the participation of foreign companies.

## CHAPTER ELEVEN
## SPECIAL PROCUREMENT

### 60. Large Value Procurement

**1**) There shall be established a central body, which shall be in charge of the execution of large value procurements having regional significance procurements of supplies for which a demand is shown by more than one public body and sale of public property to be disposed off, by a regulation to be issued by the executive of the region.the bureau shall determine the type of procurement to be carried out by the centeral body.

፪ የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ ፩ ድንጋጌ ቢኖርም ከአንድ በላይ በሆኑ መንግሥት መስሪያ ቤቶች የሚፈለጉ አቅርቦቶችን ግዥ እንዲሁም የሚወገዱ ንብረቶችን ሽያጭ የሚፈፅም አካል የክልሉ መስተዳደር ምክር ቤት በሚያወጣው ደንብ እስኪቋቋም ድረስ በቢሮው ሥር የተደራጀው የጋራ ግዥና ንብረት ማስወገድ ሥራ ሂደት ይፈጽማል፡፡

## ፷፩ የማዕቀፍ ስምምነት አፈፃፀም

፩ የመንግሥት መስሪያ ቤቶች ላላቸው ተመሳሳይ የግዥ ፍላጎት ወይም አንድ የመንግሥት መስሪያ ቤት በተወሰነ ጊዜ ውስጥ በተደጋጋሚ ለሚኖረው የግዥ ፍላጎት ግዥን በማዕቀፍ ስምምነት መፈፀም ይቻላል፡፡

፪ ከአንድ በላይ በሆኑ መስሪያ ቤቶች በተወሰነ ጊዜ ውስጥ ለሚከናወኑ ተመሳሳይ አቅርቦቶች የማዕቀፍ ስምምነት በሚከተለው ሁኔታ ይፈፀማል፡-

ሀ. ኤጀንሲው የመንግሥት መስሪያ ቤቶች የሚኖራቸውን ተመሳሳይ ፍላጎት በማጥናት የዕቃና አገልግሎቶች ዝርዝር ያወጣል፣ በየጊዜውም ያዳብራል፣

ለ. የመንግሥት መስሪያ ቤቶች በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ ፪/ሀ/ በተመለከተው ዝርዝር ውስጥ ለተካተቱት ዕቃና አገልግሎቶ ች የሚኖራቸውን ፍላጎት ትንበያ አዘጋጅተው ግዥውን እንዲያከናውን ሥልጣን ለተሠጠው አካል ያሳውቃሉ፡፡

2) notwithstanding the provisions of sub-article 1 of this article , until a body, which execute procurement of supply and sell of disposed property required by more than one public body, established based on a regulation to be issued by executive council, co-procurement and property disposal work process, which organized under the bureau,shall execute the functions of procurement and property disposal

## 61. Procedure of Framework Contract

1) Framework contracts may be used to fulfill similar procurement requirements of various public bodies or recurrent procurement requirements of a public body.

2) The following procedure of framework contract shall be followed to meet similar procurement requirements of public bodies within a given time frame:

a) The Agency shall undertake a survey of the similar requirements of public bodies, issue a list of goods and services constituting such requirements and update the list regularly;

b) public bodies shall prepare a forecast of their requirements of goods and services falling under the list mentioned in sub-article (2) (a) of this Article and communicate the same to the body authorized to conduct large procurements;

ሐ. በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፷/፩/ መሠረት የሚቋቋመው አካል በዚህ አዋጅ በተመለከተውና ቢሮው በሚያወጣው መመሪያ ላይ በሚገለፀው ዝርዝር መሠረት የማዕቀፍ ስምምነት ይፈፅማል፣ ያስተዳድራል፡፡

መ. የመንግሥት መሥሪያ ቤቶች የተፈፀመውን የማዕቀፍ ስምምነት መሠረት በማድረግ ዕቃው ወይም አገልግሎቱ በተፈለገ ጊዜ የግዥ ትዕዛዝ በማስተላለፍ ግዥያቸውን ይፈፅማሉ፡፡

ሠ. የመንግሥት መስሪያ ቤቶች ለማዕቀፍ ስምምነት አቅራቢው የግዥ ትዕዛዝ የሚያስተላልፉት የማዕቀፍ ስምምነት ከተፈፀመበት ዋጋ፣ የክፍያና ሌሎች የአፈጻፀም ሁኔታዎች ጋር በተጣጣመ ሁኔታ ይሆናል፡፡

፫ በግዥ ትዕዛዝ ላይ በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፴፯ በፊደል ተራ /ተ/ በተመለከተው ሁኔታ ካልሆነ በስተቀር ከማዕቀፉ ስምምነቱ የነጠላ ዋጋ ወይም መሠረታዊ በሆኑ ሌሎች የስምምነቱ የውል ሁኔታዎች ላይ ለውጥ ማድረግ አይፈቀድም፡፡ ሆኖም በማዕቀፍ ስምምነቱ ያልተካተቱ እና በማዕቀፍ ስምምነቱ ላይ መሰረታዊ ለውጥ የማያስከትሉ ጉዳዮች ላይ የመንግሥት መሥሪያ ቤቱ እና የማዕቀፍ ስምምነቱ አቅራቢ በሚያደርጉት ስምምነት ይወሰናሉ፡፡

c) the body to be established in accordance with Article 60(1) of this Proclamation shall conclude and administer framework contracts in the manner prescribed herein and the directive to be issued by the bureau;

d) public bodies shall on the basis of the framework contract signed by the central body of procurement conclude the procurement by making order with the suppliers of goods and services that they require;

e) the order that public bodies place with the suppliers for goods and services of their requirements under the frame work contract shall confirm to the terms of the framework contract regarding price, terms of payment and other matters related to the execution of procurement.

3) Except in cases provided for in Article 37 paragraph (k) of this Proclamation, public bodies shall not be allowed to vary unit prices and such other fundamental terms of the framework contract when placing order for goods and services. However, the public body and the supplier may agree on terms that have not been dealt with in the framework contract or that do not materially affect the frame work contract.

፬ የማዕቀፍ ስምምነት የሚፈፀመው በግልፅ ጨረታ የግዥ ዜዴ ሆኖ እስከ ሦስት ዓመት ድረስ ፀንቶ ሊቆይ ይችላል፡፡

፭ አንድ የመንግሥት መስሪያ ቤት በተደጋጋሚ ለሚኖረው የግዥ ፍላጎት ግዥን በማዕቀፍ ስምምነት ሊፈፅም የሚችለው በቢሮው በሚወጣ መመሪያ የተመለከተውን የዕቃ ወይም የአገልግሎቱ ዋጋ የሚወሰንበት ግልፅ መስፈርት መሠረት በማድረግ ይሆናል፡፡

## ምዕራፍ አስራ ሁለት
## የመንግሥት ንብረት አስተዳደር

### ፷፪ አጠቃላይ

ቢሮው በሚያወጣው መመሪያ መሰረት እያንዳንዱ የመንግሥት መሥሪያ ቤት የበላይ ኃላፊ የመንግሥት ንብረት በአግባቡ የመያዝ እና የመጠቀም፣ አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ የማስወገድ ተግባር መከናወኑን ማረጋገጥ አለበት፡፡

### ፷፫ ንብረትን ስለመያዝ

፩ ማናቸውም የመንግሥት ንብረት በባለቤትነት የመያዝ ብቸኛ ዓላማ የፀደቁትን የመሥሪያ ቤቱን ፕሮግራሞች ለማስፈፀም እና አገልግሎቱን በማፋጠን ውጤታማና ብቁ ለማድረግ መሆን አለበት፡፡

4) The framework contract shall be awarded through open bidding procedure and may remain valid for three years.

5) In procuring goods and services under a framework contract to fulfill their recurrent requirements, public bodies shall have to adhere to the criterion of fixing prices of goods and services to be determined in the directive to be issued by the bureau.

## CHAPTER TWELVE
## PUBLIC PROPERTY DMINISTRATION

### 62. General

The head of each public body shall ensure that property at the disposal of the public body is properly handled, used and where necessary, disposed off in accordance with the directive to be issued by the bureau.

### 63. Acquisition

1) All acquisitions of public property shall be for the sole purpose of facilitating the delivery and maintenance of approved programs as efficiently and effectively as possible.

፪ ቢሮው በማናቸውም የክልሉ መንግሥት መስሪያ ቤት ሥር ያልሆኑትን የክልሉን መንግሥት ንብረቶች በመንግሥት ንብረትነት ይይዛል፣ ያስተዳድራል፣ ተገቢ ሆኖ ሲገኝ እንዲወገዱ ያደርጋል፡፡

2) The bureau shall account for, administer and where necessary, dispose off property of the region state which are not administered by any other public body

## ፷፬ አጠቃቀም እና ጥገና

፩ የመንግሥት መሥሪያ ቤት የግዥና ንብረት አስተዳደር የሥራ ሂደት ባለቤት እና የመሥሪያ ቤቱ የበላይ ኃላፊ ማናቸውም የመንግሥት ንብረት የመሥሪያ ቤቱን ኃላፊነት ውጤታማ በሚያደርግ መልኩ አገልግሎት ላይ መዋሉን ማረጋገጥ አለባቸው፡፡

፪ የመንግሥት መሥሪያ ቤት የበላይ ኃላፊ ቢሮው በሚያወጣው መመሪያ መሠረት የመንግሥት ንብረት ኢኮኖሚያዊና ውጤታማ በሆነ መንገድ አገልግሎት እንዲሰጥ ተገቢ የጥገና እና የእንክብካቤ ሥርዓት መዘርጋት አለበት፡፡

## 64. Use and Maintenance

1) Heads of public bodies shall ensure that all public property is used as productively as possible in carrying out of the responsibilities of the public bodies.

2) Heads of public bodies shall establish a proper maintenance system for all public property to ensure that it will operate as economically and effectively as possible in accordance with the directive to be issued by the bureau.

## ፷፭ የመንግሥት ንብረት አስተዳደር

፩ የመንግሥት መሥሪያ ቤት የበላይ ኃላፊ የመንግሥት ንብረት ለማስተዳደር የሕይወት ዘመን ሥርዓትን ይከተላል፡፡

## 65. Management of Public Property

1) The heads of public bodies shall adopt a life- time approach to the management of public property.

፪ የመንግሥት መሥሪያ ቤት የበላይ ኃላፊ የመንግሥት ንብረት ከተያዘበት እስከ ከአገልግሎት ውጪ እስከሆነበት ቀን ድረስ ንብረቱ አገልግሎት ያቋረጠበትን ጊዜ፣ የንብረቱ ዓይነት፣ ብዛቱን እና ያስከተለውን ወጪ የሚያሳይ ዝርዝር ተመዝግቦ መያዙን ማረጋገጥ አለበት፡፡

፫ የመንግሥት መሥሪያ ቤት የበላይ ኃላፊ የመሥሪያ ቤቱን ማናቸውንም ቋሚ ንብረት የመጠበቅ ኃላፊነት በመጀመሪያ ደረጃ ንብረቱን እንዲገለገሉበት ኃላፊነት ለተሰጣቸው ኃላፊዎች መሰጠቱን እና በቋሚ ንብረት መዝገብ የጠባቂዎች ዝርዝር እና በእነርሱ ጥበቃ ሥር ያሉት ቋሚ ንብረቶች የሚገኙበት ቦታ መስፈሩን ማረጋገጥ አለበት፡፡

፬ የመንግሥት መሥሪያ ቤት የበላይ ኃላፊ ወዲያውኑ ጥቅም ላይ የማይውሉ አላቂ ዕቃዎች በመስሪያ ቤቱ የሚመለከተው የንብረት ሥራ ሂደት በዕቃ ዝርዝር መዝገብ ውስጥ መካተታቸውንና ለጥበቃቸው ኃላፊ መመደቡን ማረጋገጥ አለበት፡፡

፭ ማናቸውም የመንግሥት ንብረት ቢያንስ በዓመት አንድ ጊዜ መቆጠር አለበት፡፡

፮ የመንግሥት ንብረት ትክክለኛ ዋጋ ለመወሠን ሳይቻል ሲቀር ግምቱ ቢሮው በሚያወጣው መመሪያ መሠረት ይሆናል፡፡

፯ ቢሮው በሚያወጣው ዝርዝር መመሪያ መሰረት የሚፈፀም ሆኖ በመንግሥት ቋሚ ንብረት ላይ የእርጅና ቅናሽ ይሰላል፡፡

2) Heads of public bodies shall ensure that items of public property are recorded as to date, description, quantity and cost from acquisition to the end of their life-time.

3) Heads of public bodies shall ensure that the custodial responsibility for each fixed asset acquired is assigned primarily to persons using such fixed assets and that names of the custodians, and the locations of the fixed assets under their custody are recorded in the register of fixed assets.

4) Heads of public bodies, shall ensure that supplies, not acquired for immediate consumption, shall form part of supply inventories and that custodial responsibility be assigned for such inventories.

5) All inventories of public property shall be physically verified against records at least annually.

6) Where the actual cost of public property is not determinable, its cost shall be estimated in accordance with the directive to be issued by the bureau.

7) Depreciation shall be calculated on fixed assets in accordance with the directive to be issued by the bureau.

## ፷፮ መጠበቅና መንከባከብ

ማናቸውም የመንግሥት መሥሪያ ቤት የበላይ ኃላፊ እና ሠራተኞች የመንግሥንትን ንብረት የመጠበቅና የመንከባከብ ኃላፊነት አለባቸው፡፡

## ፷፯ መሠረዝ

፩ የመንግሥት ንብረት ለሚገኝበት የመንግሥት መስሪያ ቤት ወይም ለሌላ የመንግሥት መስሪያ ቤት የማይጠቅምና ዋጋ የማያወጣ መሆኑ ሲረጋገጥ ቢሮው በሚያወጣው መመሪያ መሰረት ይሰረዛል፡፡

፪ የመንግሥት ንብረት ሲበላሽ፣ ከጥቅም ውጪ ሲሆን፣ ሲሰረቅ ወይም በማናቸውም ሌላ ተመሳሳይ ምክንያት ሲጎድል ወይም ሲጠፋ ከንብረት መዝገብ ይሰረዛል፡፡

፫ ማናቸውም የመንግሥት ንብረት ሲሰረዝ መግለጫውና የንብረቱ የመዝገብ ዋጋ ቢሮው በሚያወጣው መመሪያ መሠረት በመንግሥት ሒሳብ ሪፖርት ውስጥ ተጠቃልሎ መታየት አለበት፡፡

## ፷፰ ማስወገድ

፩ ዝርዝር አፈጻፀሙ ቢሮው በሚያወጣው መመሪያ የሚወሰን ሆኖ የመንግሥት መሥሪያ ቤት የበላይ ኃላፊ አገልግሎት የማይሰጡ ንብረቶች መወገዳቸውን ማረጋገጥ አለበት፡፡

## 66. Protection and Preservation

The heads and all employees of public bodies shall be responsible for the protection and preservation of public property.

## 67. Deletion

1) Where public property is considered to be of no use in the public body or elsewhere, and has no- scrap value, it shall be deleted in accordance with the directive to be issued by the bureau.

2) Deletion of public property shall be recorded when losses take place from inventory shortages, destruction, theft or any other reason.

3) The description and book value of all public property deleted shall be included in the public accounts in accordance with the directives to be issued by the bureau.

## 68. Disposal

1) Heads of public bodies shall ensure that fixed assets which are not useful to the organization are disposed off in the manner to be prescribed in the directive to be issued by the bureau.

፪ የተወገደ የመንግሥት ንብረት መግለጫና ንብረቱን በማስወገድ የተገኘው ገንዘብ በመንግሥት ሒሳብ ሪፖርት ውስጥ መጠቃለል አለበት፡፡

፫ በቢሮው በሚወጣ መመሪያ የሚወሰነው እንደተጠበቀ ሆኖ፣ የመንግሥት ንብረት በማስወገድ የተገኘ ገቢ ለመንግስት ግምጃ ቤት ገቢ መደረግ አለበት፡፡

## ምዕራፍ አሥራ ሶስት

## በመንግሥት ግዥ እና ንብረት አስተዳደር ላይ የሚቀርብ አቤቱታን የሚያጣራ ቦርድ ስለማቋቋም

### ፷፱ ስለቦርዱ መቋቋም

፩ በመንግሥት ግዥ አፈፃፀም እና ንብረት አወጋገድ ላይ የሚቀርቡ አቤቱታዎችን አጣርቶ ውሣኔ የሚሰጥ የአቤቱታ አጣሪ ቦርድ ከዚህ በኋላ “ቦርድ” እየተባለ የሚጠራ በዚህ አዋጅ ተቋቁሟል፡፡

፪ ቦርዱ ተጠሪነቱ ለቢሮው ይሆናል፡፡

### ፸ የቦርዱ አባላት እና የሥራ ዘመን

፩ የቦርዱ አባላት ከንግዱ ማሕበረሰብ፣ አግባብነት ካላቸው የመንግሥት መሥሪያ ቤቶች እንዲሁም ከመንግሥት የልማት ድርጅቶች የተውጣጡ ይሆናሉ፡፡

2) The description and amount received from all public property disposed off shall be included in the public accounts.

3) Without prejudice to the provisions of the directive to be issued by the bureau, concerning the matter, proceeds from the disposal of public property shall be deposited into the account of the central treasury.

## CHAPTER THIRTEEN

## ESTABLISHMENT OF THE BOARD REVIEWING COMPLAINTS ON PUBLIC PROCUREMENT AND PROPERTY ADMINISTRATION

### 69. Establishment of the Board

1) A body (hereinafter referred to as the "Board") is hereby established which reviews and decides on complaints lodged with regard to public procurement and property disposal proceedings.

2) The Board shall be accountable to bureau.

### 70. Board Members and Terms of Service

1) The Board shall be drawn from persons representing the private business sector, the relevant public bodies and public enterprises.

፪ ኤጀንሲው የአቤቱታ አጣሪ ቦርድ ፀሐፊ በመሆን ያገለግላል፡፡

፫ ቢሮው የቦርዱን አባላት ይሰይማል፡፡ ለቦርድ አባላት የሚከፈለውን አበል መጠን እና የክፍያ አፈፃፀም ይወስናል፡፡

፬ የቦርዱ አባላት የሥራ ዘመን ሦስት ዓመት ይሆናል፡፡ ሆኖም የተሰጠውን ኃላፊነት በአግባቡ ያልተወጣ አባል በማንኛውም ጊዜ ከሥራ ዘመኑ መጠናቀቅ በፊት በሌላ አባል ሊተካ ይችላል፡፡

## ፸፩ የቦርዱ ሥልጣንና ተግባር

፩ ቢሮው ቦርዱ ሥራውን የሚያከናውንበትን ሥርዓት፣ ቦርዱ የሚኖረውን ስልጣን እና ኃላፊነት የያዘ ዝርዝር መመሪያ የሚከተሉትን አጠቃላይ ሁኔታዎች በጠበቀ መልኩ አዘጋጅቶ ሥራ ላይ ያውላል፡-

ሀ/ ቦርዱ ከዕጩ ተወዳዳሪዎች ወይም ከአቅራቢዎች የሚቀርቡ አቤቱታዎችን መርምሮ ውሣኔ ይሰጣል፤

ለ/ ቦርዱ ሥራውን ለማከናወን እንዲረዳው አግባብ ያላቸው ሠነዶች እንዲቀርቡ እንዲሁም የሚመለከታቸው አካላት ሠራተኞች ወይም ኃላፊዎች ቀርበው እንዲያስረዱ ሊያዝ ይችላል፤

2) The Agency shall serve as the secretariat of the Board.

3) The bureau shall appoint the members of the Board. He shall determine the amount of allowance to be paid to the members of the Board and the mode of payment.

4) The term of service of members of the Board shall be three years. However, any member of the Board failing to properly discharge his duty maybe replaced at any time before his term of service expires.

## 71. Powers and Duties of the Board

1) The bureau shall issue and implement a directive setting for the procedure the Board has to follow in the exercise of its powers and duties; such directive shall adhere to the following general rule.

a) the Board shall review and decide on complaints from candidates or suppliers;

b) the Board may in the exercise of its function require the production of relevant documents and the testimony of officials and employees of the concerned bodies;

ሐ/ ቦርዱ አቤቱታ በማጣራት ሂደት ተገቢ ሆኖ ሲያገኘው ከመንግሥታዊ ወይም መንግሥታዊ ካልሆኑ አካላት ሙያዊ እገዛ መጠየቅ እና ማግኘት ይችላል፡፡

፪ ቦርዱ የጽሕፈት ቤት አገልግሎት እና የቴክኒክ ድጋፍ ከኤጀንሲው ያገኛል፡፡

፫ ዝርዝር አፈፃፀሙ ቢሮው በሚያወጣው መመሪያ የሚገለፅ ሆኖ ቦርዱ የቀረበለትን አቤቱታ መርምሮ ከሚከተሉት ተገቢ ነው ብሎ የሚያምነውን ውሣኔ ሊሰጥ ይችላል፡-

ሀ/ አቤቱታ የቀረበበት የግዥ ሂደት እንዲስተካከል ወይም እንዲቋረጥ የማዘዝ፤

ለ/ የቀረበው አቤቱታ ተገቢ ሆኖ ካልተገኘ ውድቅ የማድረግ፡፡

፬ የቦርድ አባላት ተግባራቸውን በተሟላ ሥነ-ምግባር ማከናወን ያለባቸው ሲሆን በሥራቸው አፈፃፀም የተፈጠረ ወይም ሊፈጠር የሚችል የጥቅም ግጭትን የማሳወቅ እና ራሳቸውን ከሂደቱ የማግለል ኃላፊነት አለባቸው፡፡

## ምዕራፍ አሥራ አራት

## በመንግሥት ግዥ አፈጻፀም እና ንብረት አወጋገድ ሂደት ስለሚቀርብ አቤቱታ

### ፸፪ ጠ ቅ ላ ላ

፩ የዚህ ምዕራፍ ድንጋጌዎች እንደተጠበቁ ሆነው፣ ግዥውን በሚፈፅመው ወይም ንብረቱን በሚያስወግደው የመንግሥት መስሪያ ቤት የተከናወነው ወይም ሳይከናወን የቀረው ተግባር ይህንን አዋጅ እና የአፈጻፀም መመሪያዎቹን ይጥሳል ብሎ የሚያምን ዕጩ ተወዳዳሪ ለመስሪያ ቤቱ የበላይ ኃላፊ ወይም በደረጃ ለቦርዱ አቤቱታ ሊያቀርብ ይችላል፡፡

c) the Board may also seek professional assistance from governmental or non-governmental entities where it finds such assistance to be useful in reviewing and deciding on a complaint submitted to it.

2) The Agency shall provide the Board with office facility and technical assistance.

3) Upon deliberation on a complaint submitted to it, the Board may give one of the following decisions, which it deems to be appropriate, with the details to be prescribed in the directive to be issued by the bureau:

a) that the procurement proceeding in respect of which a complaint was lodged be rectified or terminated;

b) to dismiss the case where in its judgment the complaint is unfounded.

4) The members of the Board shall discharge their duty in a perfectly ethical manner. They have the obligation to report any potential or actual conflict of interest they may come across in the exercise of their functions and to exclude themselves from any proceeding involving such conflict.

## CHAPTER FOURTEEN

## COMPLAINTS THAT MAY BE LODGED WITH REGARD TO PROCEEDINGS OF PUBLIC PROCUREMENT AND PROPERTY DISPOSAL

### 72. General

1) Without prejudice to the provisions of this Chapter, a candidate shall be entitled to submit a complaint to the head of the public body or to the Board against an act or omission of the public body with regard to a public procurement or property disposal proceeding where he believes that such an act or omission violates this Proclamation or the directives.

፪ ከዚህ በታች የተዘረዘሩት በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ ፩ በተደነገገው መሠረት አቤቱታ ሊቀርብባቸው አይችልም፡-

ሀ. በዚህ አዋጅ በተደነገገው መሠረት የሚከናወን የግዥ ዘዴዎች ምርጫ፤

ለ. በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፴ መሠረት ጨረታን፣ የመወዳደሪያ ሀሣብን ወይም በአካባቢ ማስታወቂያ በመለጠፍ የሚፈፀም ግዥን ውድቅ ማድረግ፤

ሐ. የመንግሥት መሥሪያ ቤቱ ንብረቱን ለማስወገድ በመረጠው የማስወገጃ ዜዴ፤

መ. በመንግሥት ንብረት አያያዝ እና አጠቃቀም ላይ፡፡

፫ የመንግሥት መስሪያ ቤቱ በጨረታው አሸናፊ ከሆነው ተወዳዳሪ ጋር የግዥ ውል ከፈረመ በኋላ፣ ሂደቱ ከዚህ ደረጃ እስከሚደርስ ድረስ በመሥሪያ ቤቱ በተከናወኑ ወይም ሣይከናወኑ በቀሩ ተግባራት ምክንያት የሚቀርቡ አቤቱታዎች በመስሪያ ቤቱ ወይንም በቦርዱ ሊታዩ አይችሉም፡፡

፬ በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ /፫/ የተደነገገው ተፈጻሚ የሚሆነው የሚከተሉት ሁኔታዎች ሲሟሉ ነው፡-

2) No complaint may be lodged in accordance with sub- article (1) of this Article in respect of the following matters:

a) the selection of procurement method pursuant to this Proclamation;

b) the rejection of bids, proposals or quotations pursuant to Article 30 of this Proclamation;

c) the selection of method of property disposal of the public body;

d) the handling and usage of public property.

3) Complaints against an act or omission of a public body pertaining to a proceeding leading to an award may not be brought before the head of that public body or the Board after the contract has been signed with the successful bidder.

4) The provision of sub- article (3) of this Article shall apply where the following conditions are satisfied:

ሀ. ቢሮው በሚያወጣው መመሪያ ላይ በሚቀመጠው ጊዜ ገደብ ውስጥ ለመንግሥት መሥሪያ ቤቱ አቤቱታ ባለመቅረቡ ውል የተፈረመ ከሆነ፤

ለ. አቤቱታ ቀርቦ የመንግሥት መሥሪያ ቤቱ ምላሽ የሰጠ እና ቢሮው በሚያወጣው መመሪያ ላይ አሸናፊው ከተገለፀ በኋላ ውል ለመፈረም የተቀመጠው ጊዜ ገደብ በመጠናቀቁ ውል የተፈረመ ከሆነ፤

፭ በመንግሥት ግዥ እና ንብረት ማስወገድ ላይ ስለሚቀርብ አቤቱታ እና ዝርዝር አፈጻፀም ቢሮው በሚያወጣው መመሪያ ይወሰናል፡፡

## ፸፫ ለመንግሥት መሥሪያ ቤት የበላይ ኃላፊዎች ስለሚቀርቡ አቤቱታዎች

፩ በመንግሥት መሥሪያ ቤቱ በተከናወነ ወይም ሳይከናወን በቀረ ተግባር ምክንያት የሚቀርብ አቤቱታ በመጀመሪያ ደረጃ መቅረብ ያለበት ለመሥሪያ ቤቱ የበላይ ኃላፊ ይሆናል፡፡

፪ ዕጩ ተወዳዳሪው አቤቱታውን ሊያቀርብ የሚችለው ለአቤቱታው መሠረት የሆነውን ውሣኔ ካወቀበት ወይም ማወቅ ይገባው ከነበረበት ቀን ጀምሮ በ፭ የሥራ ቀን ጊዜ ውስጥ ይሆናል፡፡

a) where the contract has been signed without a complaint being filed with the public body within the time limit prescribed in the directive;

b) where the public body responds to the complaint lodged and a contract is signed because of the expiration of the time limit for the signing of contract after the award without the candidate pursuing its complaint further.

5) The procedure to be followed in resolving complaints brought in regard to public procurement and property disposal and the detail shall be determined in accordance with the directive to be issued by the bureau.

## 73. Review of Complaints by the Head of the Public Body

1) A complaint against an act or omission by the public body shall in the first instance, be submitted to the head of the public body.

2) A candidate shall have to submit the complaint within five working days from the date he knew or should have known the circumstances giving rise to the complaint.

፫ አቤቱታው በሁለቱ ወገኖች መካከል በሚደረግ ስምምነት ካልተፈታ በስተቀር የመንግሥት መሥሪያ ቤቱ የበላይ ኃላፊ የግዥውን ወይም የንብረት ማስወገዱን ሒደት ማገድ እና አቤቱታው ከቀረበበት ቀን አንስቶ በ፲ የሥራ ቀናት ጊዜ ውስጥ፣ ውሣኔው የተሰጠበትን ምክንያት ወይም አቤቱታው ተቀባይነት ያገኘ ከሆነ የሚወስደውን የማስተካከያ እርምጃ በመጥቀስ የጽሑፍ ውሣኔ መስጠት አለበት።

፬ የመንግሥት መሥሪያ ቤቱ የበላይ ኃላፊ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ ፫ በተወሰነው ጊዜ ውስጥ ውሣኔ ካልሰጠ ወይም ተወዳዳሪው በመንግሥት መሥሪያ ቤቱ የበላይ ኃላፊ ውሣኔ ያልረካ እንደሆነ የመንግሥት መሥሪያ ቤቱ ውሣኔ ለአቤቱታ አቅራቢው መግለፅ ከነበረበት የመጨረሻ ቀን ወይም ውሳኔ የሰጠ ከሆነም ውሳኔው ከተገለፀበት ቀን አንስቶ በሚቆጠር ፭ የሥራ ቀን ጊዜ ውስጥ ለቦርዱ ሊያቀርብ ይችላል።

## ፸፬ ለቦርዱ ስለሚቀርብ አቤቱታ

፩ ቦርዱ አቤቱታ ሲቀርብለት ወዲያውኑ አግባብ ላለው ግዥ ፈፃሚ አካል አቤቱታ የቀረበ መሆኑን የሚገልጽ ማስታወቂያ ይልካል። አቤቱታ የቀረበ መሆኑን የሚገልጽ ማስታወቂያ እንደተላከ ግዥ ፈፃሚው አካል ቦርዱ በጉዳዩ ላይ ውሣኔ እስከሚሰጥ ድረስ ማናቸውንም ቀጣይ እንቅስቃሴ ወዲያውኑ ማቆም አለበት።

3) Unless the complaint is resolved by mutual agreement, the head of the public body shall suspend the procurement or property disposal proceedings and shall, within 10 days after submission of the complaint, issue a written decision, stating the reasons, and, if the complaint is upheld, indicating the corrective measures to be taken.

4) If the head of the public body does not issue a decision within the time stated in sub-article (3) of this Article, or if the candidate is not satisfied with the decision of the head of the public body the candidate is entitled to submit a complaint to the Board within five working days from the date on which the decision has been or should have been communicated to the candidate by the public body.

## 74. Reviews by the Board

1) Upon receipt of a complaint, the Board shall promptly give notice of the complaint to the concerned public body . Such action automatically suspends further action by the public body until the Board has settled the matter.

፪ ቦርዱ የዕጩ ተወዳዳሪውን አቤቱታ ውድቅ ካላደረገው በስተቀር፡-

ሀ. ግዥ ፈፃሚው አካል ሕጉን ያልጠበቀ ተግባር እንዳያከናውን እና ውሣኔ እንዳይሰጥ ሊያግድ፤

ለ. አሸናፊውን ተጫራች ከመምረጥ ወይም ውል ከመፈረም ጋር ከተያያዙ ውሣኔዎች በስተቀር የመንግሥት መሥሪያ ቤቱ ሥራውን እንዲያከናውን፤

ሐ. ግዥ ፈጻሚው አካል ከሕግ ውጪ ያከናወነው ተግባር ወይም የሰጠው ውሣኔ በሙሉ ወይም በከፊል ቀሪ እንዲሆን፣ ውሳኔ ሊሰጥ ይችላል፡፡

፫ ቦርዱ በአቤቱታ ላይ ውሳኔ ከመስጠቱ በፊት ስለአቤቱታው ማወቅ ለሚገባቸው አካላት ማሳወቅ፣ ከእነዚህ አካላት የቀረበ መረጃ እና መከራከሪያ ሐሳብ ካለ ይህንኑን መመርመር አለበት፡፡

፬ ቦርዱ አቤቱታው ከቀረበለት ቀን አንስቶ በ፲፭ የሥራ ቀናት ውስጥ ለውሳኔው መሠረት የሆኑትን ምክንያቶች እና የተወሰዱትን የመፍትሔ እርምጃዎች በመጥቀስ ውሣኔ መስጠት አለበት፡፡

2) The Board, unless it dismisses the complaint, may:

a) prohibit the public body from acting or deciding unlawfully;

b) order the public body to proceed in a manner conforming to this Proclamation other than a decision to award or conclude a contract;

c) annul in whole or in part, an unlawful act or decision by the public body.

3) The Board shall, before taking any decision regarding a complaint, notify relevant bodies of the complaint and shall take into account information and arguments received from such bodies and from the public body.

4) The Board shall issue its decision within 15 working days of receiving the complaint, stating the reasons for its decision and remedies granted, if any.

## ፸፭ ለኤጀንሲው ስለሚቀርብ አቤቱታ

፩ በመንግስት ግዥ አፈጻፀም እና ንብረት አወጋገድ ሂደት የመንግስት መስሪያ ቤት ከእጩ ተወዳዳሪዎች ወይም ከአቅራቢዎች ወይም ከሚወገድ ንብረት ገዥዎች ህገወጥ የሆነ ወይም ህጋዊ የሆነ ጥቅሜን የሚጎዳ ድርጊት ተፈጽሞብኛል ብሎ ሲያምን በጨረታ ሰነዱ ወይም በውል ስምምነቱ መሰረት የሚወስዳቸው እርምጃዎች እንደተጠበቁ ሆኖ ጉዳዩን ለኤጀንሲው በጽሁፍ ያቀርባል፡፡

፪ ኤጀንሲው ከመንግስት መስሪያ ቤቶች አቤቱታ ሲቀርብለት አቤቱታ የቀረበ መሆኑን እና የአቤቱታውን ፍሬ ሀሳብ የሚገልጽ የፅሁፍ ማስታወቂያ አቤቱታ ለቀረበበት እጩ ተወዳዳሪ ወይም አቅራቢ ወይም የሚወገድ ንብረት ገዥ ይልካል፡፡

፫ ኤጀንሲው አቤቱታውን ለመመርመር እና ውሳኔ ለመስጠት ተገቢ ሆኖ ሲያገኘው ጉዳዩ የሚመለከታቸውን አካላት ጠርቶ ማነጋገር ወይም መረጃ መጠየቅ እና ማግኘት እንዲሁም ከማንኛውም አካል የሙያ ድጋፍ መጠየቅ እና ማግኘት ይችላል፡፡

፬ ኤጀንሲው የቀረበለትን አቤቱታ በተገቢው በመመርመር አቤቱታው በቀረበለት በ፲፭ የስራ ቀናት ጊዜ ውስጥ ውሳኔ ይሰጣል፡፡

፭ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ(፬ ) መሰረት ኤጀንሲው የሚሰጠው ውሳኔ ከሚከተሉት አንዱን ሊሆን ይችላል፡-

## 75. Review by the Agency

1) Where a public body believes that an unlawful act or an act prejudicial to its legitimate interest has been committed by candidates, suppliers or by buyers of disposed property, it shall without prejudice to the measures it is entitled to take against such persons in accordance with the bidding document or the contract, notify the matter in writing to the Agency.

2) the Agency shall, upon receipt of the complaint, send a written notice of the complaint and the content of such complaint to the candidate, the supplier or the buyer of disposed property against whom the complaint has been lodged.

3) Where the Agency finds it appropriate to the resolution of the complaint , it may call the concerned persons with the matter to appear in person and give evidence or seek professional assistance from any appropriate body.

4) The Agency shall review and give decision on the complaint within 15 working days of receipt of such complaint.

5) The decision to be rendered by the Agency in accordance with sub-article (4) of this Article may be one of the following

ሀ. ጥፋተኛ ሆኖ የተገኘውን እጩ ተወዳዳሪ ወይም አቅራቢ ወይም የሚወገድ ንብረት ገዥ በማንኛውም የመንግስት ግዥ እና ንብረት አወጋገድ ሂደት ለተወሰነ ወይም ላልተወሰነ ጊዜ እንዳይሳተፍ የማገድ፤

ለ. የፅሁፍ ማስጠንቀቂያ የመስጠት፤

ሐ. የቀረበውን አቤቱታ ውድቅ የማድረግ፡፡

፮ ኤጀንሲው ከመንግሥት መሥሪያ ቤቶች የሚቀርቡትን አቤቱታዎች የሚመረምርበትን እና ውሳኔ የሚሰጥበትን አሰራር የሚያሳይ የአፈጻጸም ማኑዋል በቢሮው ፀድቆ ሥራ ላይ ይውላል፡፡

## ምዕራፍ አስራ አምስት

## ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች

### ፸፮ ጥፋቶችና ቅጣቶች

፩ ይህንን አዋጅ ለመፈፀም በማናቸውም የመንግሥት መሥሪያ ቤት የተሾመ ወይም የተመደበ ሰው፡-

ሀ. በሕግ መሠረት ሊከፈለው ከሚገባ በስተቀር የተመደበበትን ሥራ በማከናወኑ ማናቸውንም ክፍያ የተቀበለ፤

ለ. ከመንግሥት መሥሪያ ቤት የግዥ አሠራር እና ንብረት አወጋገድ ጋር በተያያዘ የማጭበርበር ተግባር ፈፅሞ የተገኘ ወይም ሌላ ሰው እንዲያጭበረብር ሁኔታዎችን በማመቻቸት የተባበረ ወይም ያሴረ፤

a) suspend the candidate, supplier or buyer of disposed property for a definite or indefinite period for which it finds to be at fault from participation in any public procurement or property disposal;

b) give a written warning;

c) dismiss the complaint.

6) The bureau shall issue a directive that shows procedures to be followed by the agency in reviewing and deciding complaints submitted to it in accordance with this Article.

## CHAPTER FIFTEEN

## MISCELLANEOUS PROVISIONS

### 76. Offences and Punishment

1) Any person appointed to or employed by a public body in carrying out the provisions of this Proclamation who:

a) receives any payment for the performance of his official duty, except as provided by law;

b) defrauds a public body, conspires or colludes with any person to defraud the public body or provides an opportunity for any person to defraud the public body with regard to a public procurement or property disposal proceeding;

ሐ. ሕጉን የጣሰ ወይም በሌላ ማንኛውም ሰው ሕጉ እንዲጣስ ሆን ብሎ የፈቀደ፣

መ. በፈቃደኝነት በማናቸውም መንገድ ሀሰተኛ ሰነድ ላይ የፈረመ ወይም የመዘገበ ወይም ሀሰተኛ የምስክር ወረቀት የሰጠ፤

ከብር ፳፭ ሺህ /ከሃያ አምስት ሺህ ብር/ በማያንስና ከብር ፴፭ ሺህ /ሠላሣ አምስት ሺህ ብር/ በማይበልጥ የገንዘብ መቀጫና ከ፲ ዓመት በማያንስና ከ፲፭ ዓመት በማይበልጥ ፅኑ እስራት ይቀጣል።

፫ የዚህን አዋጅ ድንጋጌች ለማስፈፀም የተቀጠረ ማናቸውም የግዥ እና የንብረት አስተዳደር ባለሙያ በዚህ አዋጅ ይፋ እንዲሆን ከታዘዘው ዓይነት መረጃ በስተቀር፦

ሀ. ግዥውን በማስፈፀም ረገድ ባለው ሥልጣን ወይም ኃላፊነት ምክንያት ያወቀውን የሌላ ሰው ማናቸውንም መረጃ ለማናቸውም ሌላ ሰው ወይም የዚህ ሰው ወኪል ለሆነ ሰው አሳልፎ የሰጠ፤

ለ. በዚህ አዋጅ መሠረት የተሰጠውን ኃላፊነት ለመፈፀም ወይም የሥራ ግዴታውን ለመወጣት እንዲያስችል በመሥሪያ ቤቱ የሚገኘውን ማናቸውንም መረጃ በፍርድ ቤት ወይንም ስልጣን በተሰጠው አካል ትዕዛዝ ካልሆነ በስተቀር ለሦስተኛ ወገን አሳልፎ የሰጠው እንደሆነ፤

c) contravenes or intentionally permits any contravention of this Proclamation;

d) willfully makes or signs any false entry in any document or willfully makes or issue false certificates;

is liable on conviction to a fine not less than Birr 25,000 and not more than 35,000 and to a rigorous imprisonment for a term of not less than 10 years and not more than 15 years.

2) A procurement and property administration officer employed to carry out the provisions of this Proclamation, except such information required by this Proclamation to be official, who:

a) discloses to any person or that person's representative, any matter in respect of another person, that, may, in the exercise of the procurement officer's powers or the performance of the procurement officer's duties come to the procurement officer's knowledge;

b) permits any other person to have access to records in the possession or custody of the public body, except in the exercise of the procurement officer's powers or the performance of the procurement officer's duties under this Proclamation or by order of a court or any competent body;

ከብር ፲ሺህ /አስር ሺህ/ በማያንስ የገንዘብ መቀጫ እና ከ፪ /ሁለት/ ዓመት በማያንስ፣ ከ፭ /አምስት/ ዓመት በማይበልጥ እሥራት ይቀጣል፡፡

፫ የዚህን አዋጅ ድንጋጌዎች ሥራ ላይ ለማዋል የተቀጠረ ሠራተኛ ወይም ኃላፊ፡-

ሀ. በቀጥታ ወይም ቀጥተኛ ባልሆነ መንገድ የገንዘብ ወይም ሌላ ዓይነት ክፍያ ወይም ስጦታ እንዲደረግለት የጠየቀ ወይም የተቀበለ ለክፍያው ወይም ለስጦታው ተስፋ ወይም መያዣ የጠየቀ ወይም የተቀበለ፤ ወይም

ለ. በግዥ እና ንብረት አስተዳደር ተግባር ላይ ማጭበርበር ወይም ከዚህ አዋጅ ድንጋጌ-ዎች ጋር ወይም ከተሰጠው ኃላፊነት መልካም አፈፃፀም ጋር የሚቃረን ተግባር ለመፈፀም፣ ማድረግ የሚገባውን ከማድረግ ለመታቀብ፣ ተገቢ ያልሆነን ነገር ለመፍቀድ፣ በግዥ እና ንብረት አስተዳደር ላይ የሚፈፀምን የማጭበርበር ተግባር ለመደበቅ፣ ወይም በሚስጥር ለመተግበር ውል የገባ ወይም በሚገባው ውል ውስጥ በዚህ ተግባር መተባበሩን የሚያሣይ ስምምነት የሰጠ፤ከብር ከብር ፶ሺህ /ሃምሳ ሺህ/ የማይበልጥ የገንዘብ መቀጫ እና ከ፲ (አስር) ዓመት በማያንስ ከ፳ (ሃያ) ዓመት በማይበልጥ ጽኑ እሥራት ይቀጣል፡፡

commits an offence and is liable on conviction to a fine of not less than Birr 10,000 and to imprisonment for a term of not less than 2 years and not more than 5 years.

3) any person appointed to or employed by a public body to carry out the provisions of this Proclamation who:

a) directly or indirectly asks for or receives in connection with any of his duties, a payment or gift, whether pecuniary or otherwise, or promise or security for that payment or reward; or

b) enters into or acquiesces in an agreement to do or to abstain from doing, permit, conceal, or connive at any act or thing whereby the procurement or property disposal is or may be defrauded or which is contrary to the provisions of this Proclamation or to the proper execution of the procurement officer's duty; commits an offence and is liable on conviction to a fine of not less than 50,000 Birr and to imprisonment for a term of not less than ten (10) years and not more than twenty(20) years

፬/ ማንኛውም ሰው በመንግሥት ግዥ እና ንብረት አስተዳደር ላይ ለተሾመ ወይም ለተመደበ ሰው፡-

ሀ. የቀረበለትን ውሣኔ በመጠበቅ ላይ ያለውን ጉዳይ ወይም በሥራ ኃላፊነቱ ምክንያት ሊቀርብለት በሚችል ጉዳይ ላይ የሚሰጠውን ውሣኔ ወይም የሚወስደውን እርምጃ ለማዛባት ፤ ወይም

ለ. በመንግሥት ግዥ እና ንብረት አስተዳደር ላይ የማጭበርበር ድርጊት እንዲፈፀም ወይም ድርጊቱ ሊፈፀም እንዲረዳ ወይም እንዲተባበር ወይም ለድርጊቱ መፈፀም ሁኔታዎችን ለማመቻቸት እንዲስማማ፣ እንዲመሳጠር ወይም እንዲፈቀድ ለማድረግ በማሰብ ጉቦ ለመስጠት ቃል ከገባለት፣ ከቀረበለት ወይም ከሰጠው፤ከብር ፶ሺህ /ሃምሳ ሺህ/ ያላነሰ የገንዘብ መቀጫ እና ከ፲ ዓመት የማያንስ እና ከ፳ ዓመት በማይበልጥ ፅኑ እሥራት ይቀጣል፡፡

፭/ ማንኛውም ዕጩ ተወዳዳሪ ተገቢ ያልሆነ ጥቅም ለማግኘት በማሰብ የሐሰት ማስረጃ ካቀረበ ወይንም መግለፅ የነበረበትን መረጃ ከደበቀ ወይም ከሌላ ዕጩ ተወዳዳሪ ጋር በመመሳጠር የሐሰት ውድድር ማድረጉ ከታወቀ ጥፋተኛ ሆኖ መገኘቱ ሲረጋገጥ ከብር ፳ሺህ /ሃያ ሺህ/ ያላነሰ የገንዘብ መቀጫ እና ከ፭ /አምስት/ ዓመት የማያንስ እና ከ፲ ዓመት በማይበልጥ ፅኑ እሥራት ይቀጣል፡፡

4) any person who, promises, offers or gives any bribe to any person appointed to or employed in any public procurement and property administration with the intent:

a) to influence the decision or action of that person on any question or matter that is pending, or may be brought before him in his official capacity; or

b) to influence that person to commit, or aid or abet in committing any fraud on the procurement, and property administration or to connive at, collide in or allow or permit any opportunity for the commission of any such fraud;is guilty of an offence and liable on conviction to a fine of not less than Birr50,000 and to rigorous imprisonment for a term of not less than ten(10) years and not more than twenty (20) years,

5) Any candidate who, with the intention of deriving unlawful advantage, presents falsified documentary evidence or conceals any evidence which he should have disclosed or connives at an act of fake competition shall upon conviction be punishable with fine not less than 20,000 Birr and with rigorous imprisonment of not less than 5 years and not more than 10 years.

**፸፯ ደንብና መመሪያ የማውጣት ሥልጣን**

፩ ይህን አዋጅ ለማስፈጸም የክልሉ መስተዳድር ምክር ቤት እንደአስፈላጊነቱ ደንብ ሊያወጣ ይችላል፡፡

፪ ይህን አዋጅ እና በዚህ አዋጅ መሠረት የሚወጣውን ደንብ ለማስፈጸም ቢሮው መመሪያ ሊያወጣ ይችላል፡፡

፫ ኤጀንሲው ይህንን አዋጅና ቢሮው የሚያወጣውን የአፈጻፀም መመሪያ ተግባራዊ ለማድረግ የሚያስችል የግዥ አፈፃፀም እና ንብረት አስተዳደር ማኑዋል፣ መደበኛ የጨረታ ሰነድ፣ የግዥ አፈጻፀም እና የንብረት አስተዳደርን የሚመሩ ልዩ ልዩ ቅጾችን ያወጣል፡፡

**፸፰ የተሻሩና ተፈፃሚነት የማይኖራቸው ሕጎች**

፩ የደቡብ ብሔሮች ብሄረሰቦችና ሕዝቦች ክልል መንግሥት የግዥና ንብረት አስተዳደር አዋጅ ቁጥር ፻፳፱/፪፻፪ ተሽሮ በዚህ አዋጅ ተተክቷል፡፡

፪ ይህን አዋጅ የሚቃረን ማንኛውም ሕግ፣ደንብ፣ መመሪያ ወይም የአሠራር ልምድ በዚህ አዋጅ በተሸፈኑ ጉዳዮች ላይ ተፈፃሚነት አይኖረውም፡፡

## 77. Power to Issue Regulation and Directive

1) The executive council of the region may, where necessary, issue regulation for the implementation of this Proclamation;

2) The bureau may issue directive to implement this proclamation and the regulation to be issued in acconrdance with this proclamation.

3) The Agency shall, to impliment this proclamation and the directive to be issued by the bureau, issue procurement and property administration manuals, standard bid documents, and forms that are necessary to lead public procurement and property administration.

## 78. Repealed and Inapplicable Laws

1) The southern nations, nationalities and peoples regional state Public Procurement and property administration Proclamation No 129/2002 is hereby repealed and replaced by this Proclamation.

2) No law, regulation, directive or practices inconsistent with this Proclamation shall have effect with respect to matters provided for in this Proclamation;

## ፸፱ አዋጁ የሚፀናበት ቀን

ይህ አዋጅ በክልሉ ነጋሪት ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ የፀና ይሆናል፡፡

**ሀዋሳ ቀን ሐምሌ ፳፩/፪፻፬ ዓ/ም**

**ሽፈራው ሽጉጤ**

**የደቡብ ብሔር፣ ብሔረሰቦችና ሕዝቦች ክልል መንግስት ርዕሰ መስተዳድር**

## 79. Effective Date

This Proclamation shall enter into force up on the date of publication on Debub Negarit Gazeta.

**Done at Hawassa, this 28th day of July /2012**

**Shiferaw Shigute**
**Chief Executive of the Southern Nations, Nationalities and People's Regional State**